

© Safeguarding Religious Treasures of the Ethiopia Orthodox Church.

# ፈለገ ጥበብ




- ዘመንና የሰው ልጅ
- ሐዋርያነት
- ዘመነ ጽጌ
- መስቀልን የምናከብረው ሰላከበረን ነው
- ሰው የሚኖረው በእምነት ነው
- በሕይወቴ ዘመን የሚያስደስተኝና የማልረሳው ትዝታዬ

ዋጋ ብር 3.00

www.ethiopianorthodox.org

# በዘመናዊነት ፈረስ እየጋለበ ስለሆነ ጊዜ የለውም

ወጣትነት የእሳትነትና የስሜታዊነት ወቅት (የዕድሜ) ክልል ነው። ይህ የዕድሜ ክልል የሥነ ምግባር ጉድለት ጉልቶ የሚታይበት (የሚንጸባረቅበት) ለልዩ ልዩ ሱሶች (በመጠጥ፣ ስጫት ለሲጋራ፣ ለአሺሽና ለዝሙት) የሚጋለጡበት በአጠቃላይ የውል ፈለስና የዓላማ ቢስነት የዕድሜ ክልል ነው ብለው ደፍረው የሚናገሩ ወገኖች ጥቂት አይደሉም።

በእርግጥ እኛ ወጣቶች ስለ አንድ ነገር ረጋ ብለን ማሰብ ያለመቻላችንን ያህል አንድ ቦታ ረግተን መቀመጥ አንችልም። ያየነው ሁሉ ያምረናል። የሰማነው ሁሉ ይናፍቀናል በእጃችን ያለውን የትኛውም ቢሆን ከቁብ አናስገባውም ሁሌ ጊዜ የሌለንን ወይም ያልነበረንን እናልማለን የምንናገረው በችኮላ፣ በጉጉትና በናፍቆት ዙሪያ ነው ጨምተን በተሞና ብናስብበት ወይም በተንታቄ ብንይዘው ግን ዕድሜያችን ራሱ የእኛ እንቁ ነው።

በተለይ በክርስትና ሕይወት ውስጥ ብንኖር በስንፍና የምናሳልፈው ጊዜ አይኖረንም።

በቅዱሳት መጻሕፍት እንደምናነበው በወጣትነት ዘመናቸው ለእግዚአብሔር ሕግ ተገዢ ሆነው የኖሩ፣ በእምነታቸው ጽናት የተመሰከረላቸው ወጣቶች እጅግ ብዙ ናቸው። እነ ዳንኤል ሦስቱ አስራኤላውያን በባቢሎን የግዞት አገር እግዚአብሔርን ያመለኩ የነበሩት ወጣቶች ናቸው። ዳን.፩፣፯። በሐዲስ ኪዳንም ለሐዋርያነት ከተጠሩትና በእርድእትነት ያገለገሉ በነበሩት ውስጥ ወጣቶች ይገኙበታል። ማቴ.፲፣፩–፬ በአጠቃላይ ወጣቶች ያልተሳተፉበት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የለም።

በአሁን ዘመን ግን የወጣቱ ሕይወት ተበላሽቶ ነው የሚታየው። ለልዩ ልዩ ሱሶች፣ እንዲሁም ለልዩ ልዩ በሽታዎች እየተዳረገ ይገኛል። እንዲህ ውጥንቅጡ በወጣው የወጣቶች ሕይወትና ዘመን ውስጥ ምሳሌ ሆኖ ሌላውን መክሮ አስተምሮ የሚመልስ ሃይማኖቱ የጸና ምግባሩ የቀና እውነተኛ ክርስቲያን ወጣት ያስፈልጋል። በተለይ በሀገራችን ውስጥ እየታየ ያለው የወጣት ሕይወት ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ ከፋ ደረጃ እያሽቆለቆለ ስለሆነ የእውነተኞች ክርስቲያን ወጣቶች ምሳሌነትና ምክር ያሻዋል። ኢትዮጵያዊው ወጣት በብዙ መልኩ ከባህር ማዶ በመጡት ነገሮች በሚያየውና በሚሰማው ሁሉ ወኔው እየተሰለበ ነው። የራሱ ባሕሉን ባሕልና ሥርዓት ተወስዶ ለባሕሉ ለቋንቋውና ለሃይማኖቱ ባዳ እየሆነ ይገኛል። ለመሆኑ ወጣቱ ለእንደዚህ ዓይነቱ የተበላሸ ሕይወት የሚዳረገው ከምን በመነሳትና ምን በመሆን ከመፈለግ ነው? እዚህ ላይ ምክንያቶች ይሆናሉ ወይም ናቸው ብለን የምንገነዘባቸውን ነጥቦች አንስተን እንመለከታቸዋለን።

## ፩. የራስን ማንነት ጠንቅቆ ካለመረዳት

ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ማንነታቸውን ያውቁ አይመስሉም ኢትዮጵያ ከአገሮች ሁሉ በተለየ የምትታወቅበት የራሷ የሆኑ መለያዎች አሏት ሀገሪቱ ሀገረ እግዚአብሔር ሕዝቧም ሕዝበ እግዚአብሔር ነው። ሕዝቧ እንገዳ ተቀባይ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለበት ሕዝብ ነው። ከምንም በላይ ኢትዮጵያ የምትታወቀው የእምነት መጻሕፍ የታሪክና የቅርሳ ቅርስ ማዕከል በመሆኗ ነው። ስለዚህ የጥንት አባቶቻችን በኢትዮጵያዊነታቸው ኮርተው በሃይማኖታቸው ጽናትና በምግባራቸው ቀናነት ተመስክሮላቸው ኑረውበት አልፈዋል። እነዚህን አባቶች የተካ ትውልድ ግን ይህንን ሁሉ ያወቀ አይመስልም። የአባቶቹን ፈለግ አልተከተለም። የውጪ እምነት የውጪ ባህል፣ የውጪ ቋንቋ ፈላጊ ሆኖ የራሱን አሽቀንጥሮ ጥሎ ቅልውጥ ሂዷል። አሁን አሁን ኢትዮጵያዊ መልኩን እየጠፋ ይገኛል። «በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዥንጉርጉርነትን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን?» (ኤር.፲፫፣፳፫) ብሎ ትንቢት የተናገረው ነቢይ ዛሬ ኑሮ ቢመለከት ምንኛ ይቆጨበን ይሆን? የሃይማኖት መልካችንን፣ የባህል መልካችንን፣ የአለባበስ፣ የአመጋገብ፣ የአኗኗር መልካችንን ለውጠናል። እንደ እውነቱ ከሆነማ ይህቺ ሀገር እኮ ዘጠኙ ቅዱሳን ተሰድደው ያረፉባት፣ ገዳማዊ ሕይወትን ያስፋፉባት፣ በአገራቸው ዙሪያ የወንጌል ዘር የዘሩባት የቅዱሳን ማረፊያ ቅድስት ምድር ናት። ዳሩ ግን ጌታ በወንጌል «ዘነተ ገብረ ጸራዊ ጠላት ይህንን አደረገ» ማቴ.፲፫፣፳፰። ብሎ እንደ ጠቀሰው የዲያብሎስ መልእክተኞች የእውነት ተቃዋሚዎች የሞት ሐዋርያት መናፍቃን አገራችውን አስገብተው መርዛቸውን በመንዛት ላይ ይገኛሉ።

ስለዚህ ወጣቱ የማያውቀውን የውጪውን ዓለም ለማየት ከመናፈቁ በፊት ሌላው ዓለም የሚደነቅባቸውንና የሚንጎሰፈሰፍባቸውን የአገሩ ብርቅዬ ቦታዎችና ባህሉችን ቢያጤናቸው ምንኛ መልካም በሆነ። አባቱን አያውቅ...እንደሚባለው እንዳይሆንብን።

## ፪. የዓለማዊነት ጉጉት (ፍላጐት)

እዚህ ላይ ዓለማዊነት ስንል በመጀመሪያ የምንኖርባት ዓለም የሁለት ተቃራኒ ነገሮች መርካከሪያ መድረክ እንደሆነች ለማስታወስ እንወዳለን «ይኸውም የእውነትና የሐሰት፣ የብርሃንና የጨለማ፣ የክፋትና የደግነት» ነገር ግን እስኪፈረድበት ድረስ በዚህ ዓለም ላይ ስልጣና ያለው ዲያብሎስ ከእውነት ይልቅ ሐሰት፣ ከብርሃን ይልቅ ጨለማ...የሚስማማው ስለሆነ የራሱ የሆኑትን የጥፋት ደቀ መዛሙርት ለመሰብሰብ ሰዎችን ከእግዚአብሔር አንድነት ከምዕመናን ኅብረት ለመለየት በሚያደርገው የዘወትር ተረትና ፋሟ ሰዎች በተሳሳተ መንገድ እንዲሄዱና በዓለም ሲኖሩ በዓለም ፈቃድና ምኞት እንዲጠመዱ ይገፋፋቸዋል። (ዮሐ.፫፣፲፱)።

እዚህ ላይ በዓለም ውስጥ መኖር ኃጢአት ነው የሚል መንፈስ የለንም። ዓለም የእግዚአብሔር ፍጥረታት መኖሪያ ቤት ናትና ኢሳ.፵፩፣፶፰። ነገር ግን ክርስቲያኖች በተለይ ወጣቶች በዓለም ሲኖሩ ካላወቁበት ወጥመዱ ብዙ ነው። የዓለም ግብሩ (ሥራው) ለፈቃደ ሥጋ መገዛት ነው። ይህ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር መጣላት ነው። ፩ኛ ዮሐ.፪፣፲፭–፲፯፣ ያዕ.፩፣፲፩። የዓለም ሥራው ስንል ዝሙት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ስካር፣ ፍቅረ ንዋይ (ገንዘብ መውደድ) የመሸም ጉጉት...ናቸው። ገላ.፭፣፲፱–፳፩። ስለዚህ እነዚህን ከማድረግ መቆጠብ ከክርስቲያኖች ይጠበቃል። በዓለም ስንኖር በዓለም የኑሮ ጣዕም ተጠምደን ከእውነተኛ አምላካችን እንዳንወጣ መለየት አለብን። ዮሐ.፲፭፣፲፰ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጐና ደስ የሚያሰኝ ምን እንደሆነ ለይተን እናውቅ ዘንድ በልባችን መታደስ ተለውጠን መኖር እንጂ ይህን ዓለም መምሰል የለብንም። ሮሜ.፲፪፣፪፣ ቆላ.፫፣፳–፳፭።

ስለዚህ ወጣቶች ምንም እንኳን የችኩልነትና የስሜታዊነት ዕድሜ ላይ ያለን ቢሆንም ክርስቲያን ወጣቶች ግን በዚህ በዓለማዊነት መንፈስ ሳይሆን ማስተዋልና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለበትን መንፈስ ይዘን ገሪ ቶችን ፊት ለዓለሙን ተመልክተን ጥቅምና ጉዳቱን እንገነዘብ በትክክል መጓዝ ይገባናል። ካለበለዚያ ግን ለኀጢአትና ለዲያብሎስ ተገዢ ሆነን ከሚፈረድባቸው ወገኖች እንመደባለን።

## ፫. ዘመናዊነትን መሻት

ዘመናዊነት ስንል ዘመኑ የወለደው አዲስ ነገር ማለታችን ነው። በእርግጥ ዘመናችን ከጊዜ ወደ ጊዜ አዳዲስ ግኝቶችን እያስተናገደ ነው። ብዙ ግኝቶች በየጊዜው ይፈጠራሉ። በተለይ አሁን ያለንበት ክፍለ ዘመን የቴክኖሎጂ እድገት ጉልቶ የሚታይበት ብዙ አዳዲስ ነገሮች የሚታዩበት ክፍለ ዘመን ነው።

በመሠረቱ የዘመኑ ጠቀሜታ ሥልጣኔ ከእምነት ውጪ ነው የሚል አስተሳሰብ ባይኖረንም የሚታዩት ሁሉ የሚሰሙት ሁሉ ጠቃሚ ናቸው ግን አንልም። በተለይ ደግሞ በኢኮኖሚና በቴክኖሎጂ ባደጉ ዓለማት እየተደረገ ያለው ነው። እንደ መመሪያ አሜን ብለን የምንቀበለው የጽድቅ ሥራ አይደለም እርቃንን ወጥቶ በየአደባባዩ መታየት ዝሙትን በይፋ በአደባባይ መፈጸም፣ ተፈጥሮአዊ እነሱን በልዩ ልዩ ቀለማት ማዥጐርጐር እንዲሁም ቅጥ ያጣ አለባበስን ማዘውተርና ሌሎችም ሁሉ ወጣቱ ትውልድ ዘመናዊነትን የተቀናጀ እየመሰለው የሚከተላቸው ነገሮች ናቸው። በተጨማሪም የአነጋገር ቋንጠኝነትና የውጪ ጥራዝ ነጠቅ ቃላትን እየጠግመሩ



መምህር ተከስተ ቀለመወርቅ

መናገር የሰላምታ ልውውጥ፣ የአካሄድ ቁንጠኛነት ለልዩ ሱሶች ስጫት ለአሽሽ፣ ለሲጋራ ለዝሙት፣ መጋለጥ እነዚህ ሁሉ ዘመኑ የተከተላቸው የሥነ ምግባር ብልሹነት ድርጊቶች በሀገራችን ወጣቶች ዘንድ እየተለመዱ ከጊዜ ወደ ጊዜም እያደጉ በመምጣት ላይ ይገኛሉ። ወጣቱ እነዚህን ሁሉ ድክመቶች ቆም ብሎ እንዳይመለከታቸው በዘመናዊነት ፈረስ እየጋለበ ስለሆነ ጊዜ የለውም።

ክርስቲያን ወጣቶች ግን ዘመን የወለደውን ሁሉ ተከትለው መሄድ የለባቸውም (መዝ.፩፻፲፰፣፱፣ ፩፻፲፰፣ ፩፻፭) በመሆኑም የእግዚአብሔር ቃል የሚመክረው ዘመኑን እንድንዋጀው እና በጥበብ እንድንመላለስ ነው። ምክንያቱም ቀናቱ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ። ኤፌ.፭፣፲፭–፲፮፣ ቈላ.፬፣፭። ተብሎዋልና።

ክርስቲያን ወጣቶች ንጽሕት ሃይማኖታችንን ብርቅዬ ባህላችንን ሥርዓታችንን፣ ትውፊታችንን ኢትዮጵያዊነታችንን የሚቀይር ዘመናዊነት አያስፈልገንም። የራስን እየጣሉ የሌላውን መቀበል ስንፍና ነው። ያልሆኑትን ለመሆን መሞከርም እብደት ነው። ስለዚህ ከውጪ ለሚመጡብን የቅልውጥ ሃይማኖቶችና ሥርዓቶች ማራገፊያ ከመሆን የራስን አጽንቶ ይዞ በማንነት መኩራትና መሳሌ ሆኖ መገኘት ይበጃል።

## ፬. ለውጥ ፈላጊነት

ወጣቱ ትውልድ ከሚያንፀባርቃቸው ባህርያቶቹ መካከል ለውጥ ፈላጊነት አንዱ ነው። በአንድ ነገር ላይ አለመወሰን ያንንም ይህንንም መከጀል ያዝ ለቀቅ የማድረግ ሁኔታ። ይህ ዓይነቱ ባህርይ ግን የሚመጣው ብዙውን ጊዜ ከዓላማ ቢስነት ነው። የወደፊቱንም ሕይወት ባስተውሉ ካለማየት ነው ዓላማ ወደምንፈልገው የድል አድራጊነት መድረክ የሚያደርሰን መስመር ነው።

እግዚአብሔር ሁሉን በዓላማ ላይ ተመስርቶ ነው ሥራውን የሚሠራው። አዳምንና ልጆቹን ከባርነት ነፃ ያወጣቸው ወደ ቀደመ ክብራቸው የመለሳቸው አስቀድሞ በያዘው ዓላማ ነው። የሐዋ.፪፣፳፫፣ ኤፌ.፩፣፱–፲፩፣ ዓለምን ካለመኖር ወደ መኖር የሚያሳልፈው በያዘው እቅድና ዓላማ መሠረት ነው። ማቴ.፳፭፣፴፩።

፪ኛጢሞ.፫፣፲–፲፫ ስለዚህ በእግዚአብሔር አርአያነት የተፈጠረ የሰው ልጅ አኗኗሩ ሁሉ በዓላማ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። ዓላማውም በየጊዜው የሚለዋወጥ ከሆነ ከአንዱ ሳይሆን ይቀራል። በመሆኑም በተለይ በወጣትነት ሕይወት ዓላማ የሌሽ ጉዞ መንገዝ ነፋስ እንደሚገፋው የባህር ላይ መርከብ መሆን ነው። በተለይም በሃይማኖት ጉዳይ እንደ ብረት የጠነከረ ዓላማ ከሌለን ነፋስ እንደሚያወዛውዘው ዛፍ ወዲያ ወዲህ መፍገምገም ይመጣል። ኤፌ.፬፣፲፬።

በእርግጥ ለውጥ የሕይወት ቅመም ናት ብለው የሚያምኑ ሰዎች የኖራሉ። አዲስ ነገርን መመኘትም የሕልውና ምልክት ነው። ግን የያዘውን ወድዶ ባለበት የሚኮራና የሚመካ ሰው ማን ይሆን? ብርቱ ሰው ማለት እሱ ነው። በተለይ በክርስቲያናዊ ሕይወት በጽኑ ዓለት በክርስቶስ ላይ ተመስርቶ በሃይማኖት ተደላድሉ ሳይናወጥ የቆመ ሰው እሱ ብፁዕ ነው። ✚


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃና
ማስተባበሪያ መምሪያ በየ፫ወሩ የሚዘጋጅ
ትምህርታዊ መጽሔት

# ፈለገ ጥበብ

፫ኛ ዓመት ቁጥር ፮

መስከረም – ኅዳር ፲፱፻፺፫ ዓ.ም


## ማውጫ


ዘመንና የሰው ልጅ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፪

ቃለበረከት

ዘመን የማይቈጠርለት የዘለዓለም አምላክ . . . . . . . . . . . . ፫

ሐዋርያነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፭

ሥርዓተ ቤተክርስቲያን

ምሕረት በንስሐ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፰

ትምህርተ ሃይማኖት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲

መስቀልን የምናከብረው ስለአከበረን ነው . . . . . . . . . . . . . ፲፫

እኔም ወጣት ነበርኩ

የ፺፩ ዓመት የዕድሜ ባለጸጋ . . . . . . . . . . . . . . ፲፯

ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

ሰው የሚኖረው በእምነት ነው . . . . . . . . . . . . . . ፲፱

መግሬረ ፀር

ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም . . . . . . . . ፳፪

ከወጣቱ ለወጣቱ

በሕይወቴ ዘመን የሚያስደስተኝና የማልረሳው ትዝታዬ . . . . . . . . ፳፬

ምሕዋረ ፀሐይ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፳፯

የኢትዮጵያ ንግሥት የሕንደኬ ጃንደረባ

ክርስትናን የተቀበለበት ቦታ በቅድስት ሀገር . . . . . . . . . . ፳፱

ዘመነ ጽጌ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፴፩

እስት ጉቡእ

አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ኮከበ ኢትዮጵያ ወአርማንያ . . . . . . . . . . ፴፫

በዘመናዊነት ፈረስ እየጋለበ ስለሆነ ጊዜ የለውም . . . . . . . . . ፴፬



ኤዲተሮች

ሊቀ ካህናት ኃይለሥላሴ ዓለማየሁ

መጋቢ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

ቀሲስ በላይ ተገኝ

አዘጋጆች

ዋና አዘጋጅ

ም/ዋና አዘጋጅ መልአከ ሰላም ኃይለ ኢየሱስ ከበደ

ስልክ 56-26-521 55-00-981 55-00-99 46

ፖ.ሣ.ቁ 81288


www.ethiopianorthodox.org

# ርእሰ አንቀጽ

# ዘመንና የሰው ልጅ

በእግዚአብሔር ጥበቃና ቸርነት ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረትን ጨርሰን ወደ ፲፱፻፺፲ ዓ.ም ተሸጋግረናል። እንኳን ከዘመነ ዮሐንስ ወደ ዘመነ ማቴዎስ በሠላም፣ በፍቅር አደረሰን፣ አደረሳችሁ። ለዚህም ያበቃን አምላካችን ክብርና ምስጋና ይድረሰው። በእርሱ እንደተገለጸው ዘመን ለሰው ልጅ የሕይወት መለኪያ ነው። አንድን ትውልድ አሳልፎ ሌላውን ትውልድ ሲተካ የሚኖር መታደስና ግርጀት የሌለበት ሁል ጊዜ ለውጥና መታደስ በሚሻ በሰው ልጅ ሕይወት እየተወከለ አሮጌ ዓመት፣ አዲስ ዓመት ሲባል መኖሩ የተለመደ ቢሆንም ዘመን ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ የመመለስ ባሕርይ ስለሌለው ዘመን አልፎ ሌላ ዘመን ሲተካ ሁል ጊዜ እንደተናፈቀ ይኖራል። የዘመናት ባለቤት ልዑል እግዚአብሔርም በዘመናት መካከል የቸርነቱ ሥራ ስለሚፈጽም ለዘመንም እንደ ሰው ልጅ ጠባይ የተለያየ ስያሜ ተሰጥቶታል።

ይኸውም:-

፩ኛ. ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረው ዘመን፣ ዓመተ ፍዳ፣ ዓመተ ኵነኔ በመባል ይታወቃል። ይህም በአዳም ውድቀት ምክንያት ሰው በሠራው በደል ለ፭ ሺህ ፭ መቶ ዘመን ሙሉ በሙሉ ተጠያቂ ሁኖ በመገኘቱ፣

፪ኛ. ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ያለው ዘመን ዓመተ ሥጋዌ፣ ዓመተ ምሕረት ተብሎ ይታወቃል። ለዚህም ልዑል እግዚአብሔር የባሕርይ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ልኮ ዓለምን በልጁ ደም ስለዋጀ በዚህ ምክንያት በምሕረትና በአምላካዊ ቸርነት የሚኖርበት የይቅርታ ዘመን በመሆኑ ዓመተ ምሕረት ተብሏል።

ሊቃውንትም የዘመን ታሪክና የሰው ልጅ ሕይወታዊ ጉዞ በመከተል ዘመናትን በመከፋፈል ዓመተ ፍዳ፣ ዓመተ ኵነኔ፣ ዓመተ ሥጋዌ፣ ዓመተ ምሕረት በማለት ሰይመውታል።

ዘመን የተፈጠረው ለሰው፣ ሰውም የሚመላለሰው በዘመን ዑደት ላይ ነው። በዚህ ሂደት ሰው ተወልዶ እስኪያረጅና እስኪሞት ድረስ ላይ ነው። በዚህ ሂደት ሰው ተወልዶ እስኪያረጅና እስኪሞት ድረስ እንግዳ ሆኖ በሚኖርበት ዓለም ቀንና ሌሊት፣ ብርድና ትኩሳት፣ በጋና ክረምት፣ መፀውና ጸደይ፣ የጨረቃ ሙላትና ጉድለት፣ የከዋክብት ምግብና ሁሉ እየተፈራረቀበትና እየተለዋወጠበት የሚኖር ፍጡር ነው። እንደዚህም ሆኖ ሰው በተሰጠው አእምሮ እስበ በዘመኑ ሁሉ ትውክልቱን በእግዚአብሔር አድርጎ ዓለምን እንዲያስተዳድር ሥልጣን ተሰጥቶታል። (ዘፍ.፩፥፳፰)

ይሁን እንጂ የተሰጠውን ኃላፊነት ገሸሽ በማድረግ በሕይወቱ ላይ ብዙ የተለዋወጠ ነገር ይታይበታል። በዚህ መልኩ ደግሞ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ቸርነትና ፍቅር ርቆ የሚያገኘው ሕይወት አይኖርም። እግዚአብሔር ግን ያው እግዚአብሔር ነው። አልተለወጠም።

ነቢዩ ዳዊት:- ዓመቶችህ ለልጅ ልጅ ናቸው፤ አቤቱ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትክ፤ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው፤ እነርሱ ይጠፋሉ አንተ ግን ትኖራለህ፤ ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ፤ እንደ መጎናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፤ ይለወጡማል፤ አንተ ግን ያው አንተ ነህ፤ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም። (መዝ.፻፩፥፳፭–፳፯)።

ብሎ እንደገለጸው እግዚአብሔር ለሁሉም እንደሚያስፈልገው አድርጎ አዘጋጅቶታል። ሁሉም ለፍጥረቱ እንደሚስማማው አድርጎ አከናውኖታል፣ ሁሉንም ይመግባል፣ ሁሉንም ይመራል፣ ሁሉንም ያስተዳድራል፤ ሁሉም በጊዜው ያሳልፋል እሱ ግን ያው እሱ ነው ዘለዓለም ሕያው ነው። ግዛቱም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ነው። ስለዚህም ነው ነቢዩ ዳዊት «ዓመቶችህ ለልጅ ልጅ ናቸው» ያለው።

ዘመን ሁል ጊዜ በእግዚአብሔር ጸጋ ይባረካል። ምድርም በረከቷን ትሰጣለች። ተራሮችም፣ ኮረብቶችም፣ ዕፀዋትም፣ ወንዞችም፣ አብሕርትም፣ አዝርዕትም፣ እንስሳትም፣ አራዊትም፣ ሁሉም በእግዚአብሔር ደስ ይላቸዋል።

አሁንም ነቢዩ ዳዊት:- «የዓመተ ምሕረትህን ዘር ትባርካለህ ምድረ በዳዎችም ልምላሜን ይጠግባሉ፣ የምድረ በዳ ተራሮችም ይረካሉ፣ ኮረብታዎችም ልምላሜን እንደ ዝናር ታጥቀው ደስ ይሰኛሉ።» ብሎ እንደገለጸው (መዝ.፷፬፥፲፩–፲፪)።

ዘመን ካለተጠቀሙበት አዲስ ዘመን ወይም ዓመተ ምሕረት በመባሉ ብቻው በሰው ሕይወት ላይ የሚያመጣው ትርጉም የለውም። ትርጉም የሚኖረው ሰው በዘመኑ ለራሱ እና ለወገኑ የሚጠቅም ሥራ ሲሰራበት ብቻ ነው።

ዛሬ በሰው ሕይወት ብዙ ውጣ ውረድ ይታያል። ይህ ሁሉ የሚከሰተው የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር በመራቁና ለእግዚአብሔር ትእዛዝ ባለመገዛቱ እንጂ የሰው ልጅ በመከራና ስቃይ በችግርና በማጣት ውስጥ እንዲኖር ተፈርዶበት አይደለም። «እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ፣ የምድርን በረከት ትበላላችሁ፤ እምቢ ብትሉ ግን ብታምፁም፣ ሠይፍ ይበላችኋል፤ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና።» (ኢሳ.፩፥፲፱–፳)

በሰው ልጅ የዘወትር እንቅስቃሴ፣ በቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የሰው ጠላት የሆኑ ድኅነትና ድንቍርና፣ ዘረኝነት፣ የፍትሕ መጓደል፣ አድልዎ፣ ሚካኝነት፣ ጦርነትና ጉስቁልና፣ ረሃብና በሽታ፣ ስደትና መታረዝ ሁሉ የሰው ልጅ ለመከራና ለበሽታ የተፈጠረ አስመስለውታል።

እነዚህ ሁሉ ከሰው ስንፍና ጋር ተደማምረው በሰው ልጅ ሕይወት ላይ በነፍሱም በሥጋውም ከፍተኛ ጉዳት አስከትለውበታል፣ እያስከተሉበትም ይገኛል።

እነዚህን ማስወገድ የሚቻለው ግን በእግዚአብሔር ኃይል ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ፣ ሳይሰለቹ በቅንነት በመሥራት እንጂ በመመኘት ብቻ ከቶ ሊሆን አይችልም።

ሰው ራሱ ሕሊናው ለእግዚአብሔር ተገዢ በማድረግ፣ መጥፎ ተግባራትን ትቶ በአዲሱ ዘመን በአዲሱ መንፈስ አዲስ ሰው ሆኖ ሲገኝ ነው እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት የሚቻለው።

ስለዚህ መጻሕፍት ደግመው ደጋግመው እንደገለጹልን አዲስ ዘመን በመጣ ቁጥር መንፈሳችን ከማስጨነቅ ይልቅ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ሠርተን ማለፍ ይገባናል። ፍቅርና አንድነት የሚሰፍንበት፣ ሰላምና ጤና የሞላበት የሰው ልጅም ለንስሐ የሚበቃበት የቤተ ክርስቲያናችን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ የሚስፋፋበት እንዲሆንልን የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሆንልን ዘንድ የሁላችንም ምኞትና ጸሎት ሊሆን ይገባል። ✤

# ዘመን የማይቈጠርለት የዘለዓለም አምላክ

**ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ**

**ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት**

**መስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፺፲ ዓ.ም አዲሱ ዓመትን ምክንያት በማድረግ ለመላ ኢትዮጵያውያን ያስተላለፉት ቃለ በረከት**



በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

በሀገራችን ኢትዮጵያ በገጠርና በከተማ፣ ከሀገር ውጭም በተለያዩ አህጉር የምትኖሩ፣

የሀገራችንን ዳር ድንበር ለመጠበቅና ለማስከበር በየጠረፉ ያላችሁ፣

በተለያየ ሕመም ምክንያት በየሆስፒታሉ፤ እንዲሁም የሕግ ታራሚ ሆናችሁ በየእስር ቤቱ የምትገኙ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት የመንፈስ ቅዱስ ልጆቼ በሙሉ:-

ዘመን የማይቆጠርለት የዘለዓለም አምላክ እግዚአብሔር እንኳን ከዘመነ ዮሐንስ ወደ ዘመነ ማቴዎስ በሰላም አሸጋገራችሁ።

«ንስእለከ እግዚኦ ከመ ትባርክ ዐውደ ዓመት ዘእምኀበ ኂሩትከ ...አቤቱ አምላካችን ሆይ! ከቸርነትህ የሚገኘውን ዐውደ ዓመት ትባርክ ዘንድ እንለምንሃለን...» (ቅዱስ ያሬድ)

ልዑል እግዚአብሔር የጊዜያትን መጀመሪያ፣ መካከልና መጨረሻ፣ የዕለታትን መመላለስ፣ የዘመናትን መፈራረቅና የዓመታትን ዑደት እንዲያስተውል ለሰው ልጅ ጥበብንና ዕውቀትን በቸርነቱ ሰጥቷል። (መጽሐፈ ጥበብ ፯፥፲፰) የሰው ልጅ በዚህ በተሰጠው ጥበብ የቀንና የሌሊትን፣ የበጋና የክረምትን፣ እንደዚሁም የመፀውንና የፀደይን መፈራረቅ በመመልከት የጊዜ መለኪያን አበጅቷል፤ ዕለቱን በሰዓት፣ ሳምንቱን በወራት፣ ወራቱንም በዓመታት እየቀመረ ዘመናትን ለመቁጠር ችሏል። ዘመን አለፈ፣ ዘመን ተተካ የሚለውም በዚሁ ከልዑል አምላክ በተቸረው ጥበብ ነው።

ስለዚህ ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የእግዚአብሔርን ፍጹም ቸርነት በማስታወስ ስላለፈው ዓመት ምስጋና ማቅረብ ተገቢ ነው። ከዚህ ዕለትና ከዚህ ዓመት መድረሳችን በራሳችን ጽድቅ፣ ጥበብና ማስተዋል አይደለም፣ በእግዚአብሔር ቸርነት ከዚህ ዕለትና ዓመት ደርሰናል። ዛሬ በምንሸጋገርበት በአዲሱ ዓመትም እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ለሀገርና ለወገን የሚጠቅም ሥራ እንድንሠራበት፣ ሁላችንም የተጣለብንን ኀላፊነት ለመወጣት እንድንችል የእግዚአብሔርን ቅዱስ ፈቃድ በጸሎት መጠየቅ አስፈላጊ ነው።

ከዓመት ወደ ዓመት ስንሸጋገር ባለፈው ዓመት ያላሟላነውን ሥራ መፈጸም አለብን። ባለፈው ዓመት ብዙ ሠርተን ከሆነ በአዲሱ ዓመት ደግሞ የተሻለና የበለጠ ሥራ ለመሥራት ጥረት ማድረግ ይኖርብናል።



www.ethiopianorthodox.org

ካልሠራን ደግሞ ለመሥራት መትጋት ተገቢ ነው። እግዚአብሔር ለእኛ ዕድሜ መስጠቱ ለሌሎች አስተማሪዎችና ማስተማሪያዎች እንድንሆን ነው። ስለዚህ፣ ጊዜም ሕይወትም በከንቱ እንዳያልፍ ልንጠነቀቅ ይገባል።

በመሠረቱ ጊዜን መቁጠር የተጀመረው በሥራ ነው። ለሰውም ጊዜ መሰጠቱ ሰው በጊዜ እንዲሠራበት ነው። የጊዜን ወርቃማነትና ክቡርነት ያስተዋሉ ሰዎች ለሥራ የተመደበው የቀኑ ሰዓት ስለማይበቃቸው ለዕረፍት በተፈቀደው ጊዜ በትጋት ሲሠሩ ይታያሉ። በዚህም ትጋታቸው ሌላው ተረድቶ ማድነቅ ወደማይችለው የዕድገት ደረጃ ደርሰዋል። እንግዲህ «ፈረሰኛ ሲሮጥ እግረኛን ምን አቆመው?» እንደሚባለው ያደጉና የበለጸጉ ማኅበረ ሰቦች ከእድገት ወደበለጠ ዕድገት ለመድረስ በሥራ በሚፋጠኑበት በአሁኑ ወቅት በማደግ ላይ ያለ ኅብረተሰብእ ጊዜውን ያለ ሥራ ሊያሳልፍ አይገባውም።

ማንም ሰው ሥራ መሥራት የማይችልበት ጊዜ እንዳለ የታወቀ ነው። ስለዚህ ሥራ መሥራት የሚቻልበትን ጊዜ ያለ ምንም የሥራ እንቅስቃሴ እንዲባክን ማድረጉ ጊዜን ለሥራ የፈጠረውን የአምላክን ትእዛዝ እንደ መቃወም ይሆናል።

በመሆኑም ኅብረተሰብአችን ረኃብንና በሽታን፣ ኋላቀርነትንና ድንቁርናን ለመቋቋም በአዲሱ ዓመት ለበለጠ ሥራ በአዲስ መንፈስና በአዲስ ሕይወት ለአዲስ ሥራ መትጋት ይኖርበታል።

የተወደዳችሁ ወገኖቼና የመንፈስ ቅዱስ ልጆቼ!

በአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ዕለት ለሥነ ምግባርም ሆነ ለአእምሮ ምቹ ባልሆነ ቦታ ተገኝቶ ከልክ ያለፈ ዓለማዊ ደስታ ከማድረግ ይልቅ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመኼድ ለአዲሱ ዓመት ሁሉንም ላደረሰ አምላክ ምስጋና ማቅረብ ተገቢ መሆኑን ልታስተውሉ ይገባል። እንደዚሁም በአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ዕለት ከቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሥርዓት ውጭ የሆነ ከባዕድ አምልኮ ጋር ግንኙነት ያለውን ተግባር መፈጸም ተገቢ እንዳልሆነ ቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር ትመክራለች፤ ታስተምራለች።

አዲሱን የዘመን መለወጫ በዓል በምናከብርበት ጊዜ ደስታችን ፍጹም እንዲሆን የተቸገሩ ወገኖችን ሁሉ ማሰብ ክርስቲያናዊ ተግባራችን መሆኑን አንርሳ።

በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ውስጥ በድርቅ በረኀብና በዕርዛት የሚሠቃዩ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖች መኖራቸው በግልጥ ተነግሮአል። እንደዚሁም ጦርነቱ ባስከተለው ችግር ቤትና ንብረታቸውን አጥተው ያለመጠለያ በቍርና በሐሩር የሚጨነቁ ወገኖች ብዙዎች ናቸው። ለእነዚህ ሁሉ ጊዜያዊ ርዳታ ለማድረግና ዘላቂ መፍትሔ ለመፈለግ በሚደረገው ጥረት ሁሉ ተሳታፊ መሆን ከሁሉም ወገን ይጠበቃል።

ወገንን መርዳት፣ ለወገን የትሩፋት ሥራ መሥራት ከጥንት ጀምሮ የነበረ ነው። ትናንት ስትፈጽሙት የነበረና የተለመደ የዘወትር ተግባራችሁ ስለሆነ ዛሬም ችግሩ እስከሚቃለል ድረስ ቸል እንዳትሉ ያስፈልጋል።

ችግር በዓለም ላይ በተለያየ መንገድ ይመጣል፣ በተለይ ከሰው ኃይል ቁጥጥር በላይ የሚሆን አባር ቸነፈር ልዩ ልዩ ደዌና በሽታ ከጦርነት ጋር በሀገር ላይ ሲከሠት ታላቅ መቅሠፍት ነው። ስለሆነም ሁል ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ከሚደረገው ጸሎትና ምህላ ጋር ኅብረተሰብኡ የጠባይ ለውጥ እንዲያደርግ የምክርና የትምህርት ልግሥና ሊታከልበት የሚገባ መሆኑን ሁሉም ሊገነዘበው ይገባል።

እግዚአብሔር አምላካችን በዓሉን የደስታና የጤና፣
ዘመኑን የምሕረትና የሰላም ያድርግልን፤
ለሀገራችንና ለመላው ዓለም ፍጹም ሰላምን ይስጥልን፤
ሕዝባችንን በፍቅርና በአንድነት ያጽናልን፤
የተዘራውን ዘርዕ፣ የተተከለውን ተክል ይባርክልን፤
የተወለዱትን ሕፃናት ያሳድግልን።
አሜን።

አባ ጳውሎስ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም
ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

✢ ✢ ✢

# ሐዋርያነት

በአባ ገሪማ

የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽሕፈት ቤት፣ የውጭ ግንኙነት የበላይ ኃላፊና የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ሊቀ ጳጳስ



የሐዋርያነት ተግባር ጥሪው የደረሰው ማንኛውም ሰው ሒዶና ተጉዞ በሚያደርገው፣ በሚናገረው፣ በሚጽፈውና በሚያደርሰው መልእክት የሚሠራውንና የሚንቀሳቀሰውን የሚያመለክት ነው።

የዚህም እንቅስቃሴ ሂደትና ውጤት የተንቀሳቃሹን ብቃትና ንቃት እንዲሁም ፍጹምነት ይጠይቃል።

የሐዋርያነት ሥራን ከሃይማኖታዊ አሠራር ውጭ አጥብቦ ማየት የሚችል ሰው ቢኖርም አሠራሩ ከሃይማኖት አንፃር ሰፋ ባለ መልኩ መታየት ያለበት ነው።

በየጊዜው የነበሩና የሚኖሩ የሃይማኖት ሰዎች የእምነታቸው የሕግ አቋምና ሥነ ሥርዓት በሚፈቅደው መሠረት እንደ የእምነታቸው የሐዋርያነት አሠራር ነበራቸው፣ አላቸው፣ ይኖራቸውማል።

የሐዋርያነት ሥራ የፈቃደ እግዚአብሔርና የትእዛዘ እግዚአብሔር አዋጅ መንገሪያና መናገሪያ መድረክና ራስን በመካድ የሚደረግ ሐዋርያዊ ጉዞ ስለሆነ አላማው ታውቆ በፈቃደ እግዚአብሔር በብቃትና በንቃት የሚሠራበት አቅጣጫ ነው።

የሐዋርያነትን እንቅስቃሴ ከሰው ሕይወት ጋር አገናዝቦና አያይዞ ለመሥራትም ቀላል የሆነ የሐዋርያነት አሠራር ዘዴ መከተሉ ይጠቅማል።

እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረ ጀምሮ የራቁትን ለማቅረብ፣ የቀረቡትንም ለመመገብ የሚጠቀምበት መግሪያ ትምህርት ነው።

ከዘመነ አበው ተያይዞ የመጣውን ትውፊት መሠረት በማድረግ የእግዚአብሔር ወዳጆች የሆኑት እስራኤላውያን በዘመነ አበው በቤተ ሰብእ ላይ ያተኑር የነበረው አስተዳደር ወደ ማኅበራዊ ሕይወት ማሸጋገሩ አስፈላጊ ሁኖ በመገኘቱ እግዚአብሔር ለቤተ እስራኤል መሪና አስተዳዳሪ እንዲሆናቸው ሙሴን አስነሥቶ በፈርዖን አገዛዝ ሥር ተጥሎ ይማቅቅ ወደነበረው ቤተ እስራኤል ላከው። (ኦሪት ዘፀአ.፫ እና ፬)

ነቢያተ እግዚአብሔር ሕዝበ እግዚአብሔርን እንዲያስተምሩና በባርነት የሚኖሩትን ነፃ እንዲያወጡ ከእግዚአብሔር ሲላኩ ጉዟቸውንና ሥራቸውን በፈቃደ እግዚአብሔር ይጀምሩ እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።

ለምሳሌ እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ግብፁ ፈርዖን በላከው ጊዜ ነቢዩ ሙሴ ለዚህ አሠራር የተባ አንደበት የሌለው መሆኑን በማስረዳቱ ይህን በግልጥ የሚታይ ችግር ለማስወገድ ወንድሙ አሮን አፍ እንዲሆነው መታዘዙ፣ ሙሴም በወንድሙ በአሮን ረዳትነት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለማስተላለፍ ችሎ ውኃውን ወደ ደምነት መለወጡ አንድ ተብሎ ተቆጥሮ አሥረኛው ሞተ በኩር፣ አሥራ አንደኛው ስጥመት በምድረ ግብፅና ባሕረ ኤርትራ በግብፃውያን ላይ ተፈጽሞ፣ በእግዚአብሔር ቸርነት በመልአኩ ተራዳኢነት በታላቁ ሙሴ መሪነት ቤተ እስራኤል ከአራት መቶ ሠላሳ ዘመን የባርነት ኑሮ ነፃ ወጣ።

በዚያን ጊዜም ሙሴና ቤተ እስራኤል «ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ፣ ፈረሰ ወመስተፅዕነ ወረወ ውስተ ባሕር» «ፈረሰኛውን ከነፈረሱ ወደ ባሕር አሽቀንጥሮ የጣለ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን» በማለት ዘምረዋል። (ኦሪት ዘፀአት ፲፭፥፲፮)

ከዚህም ጋር ይኸው ታላቁ የቤተ እስራኤል መሪ የነበረው ሙሴ እንደ እግዚአብሔር ቸርነት ሕዝበ እግዚአብሔርን በምድረ በዳ ዓርባ ዘመን ከመራና ካስተዳደረ በኋላ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይዞ ወደ ተስፋይቱ ሀገር እንዲገባ የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ አለመሆኑን አውቆና የሚሞትበት ዕለትም መድረሱን ተረድቶ የርሱን ኃላፊነት ተረክቦ የሚሠራ የቤተ እስራኤል መሪ የሚሆን ሰው እንዲሰጥ እግዚአብሔርን ይጠይቃል። እግዚአብሔርም የሙሴን ጥያቄ ተቀብሎ የሙሴ የቅርብ ረዳት የነበረውን የነዌን ልጅ ኢያሱን የቤተ እስራኤል መሪ አድርጎ በእስራኤላውያን ፊት እንዲሾመው እግዚአብሔር ሙሴን አዘዘውና ሙሴም ከእግዚአብሔር የታዘዘውን ፈጸመ።

በይቀጥላልም የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ ሕዝቡን ሰብስቦ ከመነሻው ጀምሮ እግዚአብሔር ለቤተ እስራኤል ያደረገውን በመዘርዘር አስረድቶ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሕግ አጥብቀው እንዲይዙ አሳሰባቸው። ቸርነቱ እንዲበዛላቸውም ለእግዚአብሔር መታዘዝና እርሱንም ብቻ ማመን አስፈላጊ መሆኑን የመሰነባበቻ ጊዜ ነበርና ደኅና አድርጎ አስተማራቸው።

በይቀጥላልም ሙሴ ከሞአብ ሜዳ ተነሥቶ በኢያሪኮ ፊት ለፊት ወዳለው ወደ ናባው ተራራ ወደ ፍስጋ እናት ወጥቶ ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ድረስ ያለውን ምዕራቡንም ደቡቡንም ካየና ከተመለከተ በኋላ እንደ እግዚአብሔር ቃል በአንድ መቶ ሃያ ዓመቱ ሞተ፤ ተቀበረ። ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። (ዘዳግ.፴፬)

ከሙሴ ሞት በኋላ በኢያሱ መሪነት እስራኤላውያን ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ ርስት መግባታቸውን፤ በኃይለ እግዚአብሔር የኢያሪኮን ግምብ ማፍረሳቸውንና ከመነሻ እስከ መድረሻ በተደረገውም ጦርነት ሁሉ ድልን መቀዳጀታቸውን፤ በመጨረሻም



www.ethiopianorthodox.org

ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን እንደ ገና ማደሳቸውን አሁንም መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። (ኢያሱ ፳፬፥፳፬)

ከጊዜ በኋላም በዘመነ ነገሥት ከልደተ ክርስቶስ በፊት በስምተኛው መቶ ዓመት መጨረሻ አካባቢ የነበረው ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስ ከዕለታት በአንደኛው ቀን ሕያው አምላክ ለነቢይነት ሥራ ወደ ሕዝቡ የሚልከው ነቢይ ማጣቱን ሰምቶ ለዚህ ጥሪ ፈቃደኛነቱን ቢገልጥም ከፈቃደኛነቱ ጋር የነበረበትን ድክመት (ጉድለት) አልደበቀም ነበር። (ኢሳይያስ ፮፥፰)

ከእግዚአብሔር የሚሰወር ምንም ነገር የለምና ነቢዩ ኢሳይያስ ከንፈሩ ለምፅ ያለበት በመሆኑ የእግዚአብሔርን ቅዱስ ስሙን ለመጥራት አለመቻሉ ነበር።

በዚያን ጊዜ ሕያው አምላክ በእሳት ማኀየዊ ለምፁን ተኩሶና ቀድሶ በላከው ጊዜ ነቢዩ ኢሳይያስ ወደፊት በመሄድ የተላከበትን ከግቡ አድርሷል።

ከሙሴና ከአሮን ጀምሮ በብሉይ ኪዳን የተሾሙ የእስራኤል መሳፍንት፣ ነቢያትና ካህናት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለቤተ እስራኤል ያስተላልፉ የነበረውና የእስራ ኤላውያንም ሕልውና የሚረጋገጠው ለእግዚ አብሔር ባላቸው ታማኝነት ሲሆን ለእግዚ አብሔር ታማኞች ሳይሆኑ ሲቀሩም ጥፋት የሚደርስባቸው መሆኑ ግልጥ ነበር። ምንም እንኳ እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ያላቸውን ታማኝነት በማጉደላቸው ምክንያት ጥፋት ቢደርስባቸውም ንስሐ ገብተው ወደ እግዚአብሔር በተመለሱ ቁጥር እግዚአብሔር ሊያድናቸው ዝግጁ መሆኑን የሚያመለክት ትምህርት ነበር።

ከላይ ተያይዞ ሲነገር የመጣው እንደ ሚያስረዳው ሰው በበደልና በኃጢአት እንደተዋጠ ሊተወው የማይፈቅድ እግዚአ ብሔር የእስራኤላውያን ክፉ ጠላትና የታላቁ የአሦር ንጉሥ ነገሥት መንግሥት ዋና ከተማ ወደነበረችው ወደነነዌ ሄዶ ታላቋን የነነዌን ከተማ ወደ ንስሐ ይጠራ ዘንድ ወይንም ታላቋን የነነዌን ከተማ ይሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ነቢዩ ዮናስን ቢያዘው ባለመ ታዘዝ በመርከብ ሁኖ ከእግዚአብሔር ፊት ለማምለጥ በመሞከሩ፣ በዚያን ጊዜ እግዚአ ብሔር ታላቅ ነፋስና ማዕበል ማስነሣቱ፣ ዮናስም ዕጣ ወጥቶበት ወደ ጥልቅ ባሕር መጣሉ፣ ነቢዩ ዮናስን የሚውጠውንም ታላቅ ዓሣ አንባሪ ማዘጋጀቱ በከርሠ ዓሣ አንበሪ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት ውሎና አድሮ በባሕር ዳር ወደሚገኝ የብስ መጣሉ እንደገናም ወደነነዌ ከተማ ሄዶ እንዲያ ስትምር በታዘዘ ጊዜ ወደነነዌ ከተማ ሄዶ ማስተማሩና ታላቋ የነነዌ ከተማም ከጥፋት መዳኗ በትንቢተ ዮናስ ከምዕራፍ አንድ እስከ አራት ባለው መረዳት እንችላለን።

ነቢዩ ዮናስ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ሁኖ የእግዚአብሔርን ቃል በመያዝ ወደነነዌ ከተማ መሄድ አለመፈለጉን፣ ነቢዩ ዮናስ ውሎና አድሮ እንደገና ጥሪው ሲደርሰው ካለፈው ተአምር ትምህርትን አግኝቷልና ደስ ሳይለው ታዛዥ ሁኖ (መስሎ) ወደ ነነዌ መሄዱ፣ የነነዌ ከተማ የጥፋት ትንቢቱም ተፈጻሚነት ሳያገኝ በመቅረቱ ነቢዩ ዮናስ በእግዚአብሔር ማኩረፉን አሁንም ከትንቢተ ዮናስ መረዳት እንችላለን።

ከጊዜ በኋላም እስራኤላውያን የነቢዩ የሚልክያስን ድምፅ ከሰሙ አምስት መቶ ዘመን በመሆኑ የእግዚአብሔርን ቃል ከነቢይ አንደበት ለመስማት ይጓጉ ነበር። በዚህ ረጅም ነቢይ አልባ ጊዜ እስራኤላውያን ትንቢትን የሚናገርላቸው ተአምራትን የሚያሳያቸው ነቢይ ማግኘት ይሹ ነበር።

በዚያን ጊዜ ነው ልብሱ የግመል ጠጉር፣ ኑሮው እንደባሕታዊ የሆነ በዮርዳኖስ በረሀ አካባቢ እየተዘዋወረ «እነሆ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» በማለት የንስሐ ጥሪውን በማሰማትና ኃጢአታቸውን በማናዘዝ ብዙዎችን በዮርዳኖስ የንስሐ ጥምቀትን በማጥመቅ ነበር በዮርዳኖስ በረሀ ሲዘዋወር የታየው። ይህም ሰው «ከሴቶች ልጆች የሚበልጠው የለም» ተብሎ በጌታ ቃል የተነገረለት ዮሐንስ መጥምቅ ነው። (ማቴ.፲፩፥፲፩)

ሕያው አምላክ እንዲያስተምሩ የብሉይ ኪዳን ነቢያትን ሲልካቸው በሥራ አፈጻጸም ለሚያጋጥማቸው ችግር ሳነሡት ጥያቄም ተገቢውን መልስ በማግኘት የማስተማር ሥራቸውን በመቀጠል ለሕዝቡ በቂ አገልግሎትን በመስጠት መልካም የሥራ ውጤትን አስመዝግበው አልፈዋል።

ብሉይ ኪዳኑ መነሻ፣ አዲስ ኪዳኑ መድረሻ ሁኖ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ጊዜው ሲደርስ በጊዜው ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ» (ገላትያ ፬፥፬) እንዳለው ሙሴ በኦሪት የጻፈለት፣ ነቢያት ትንቢት የተናገሩለት፣ ሱባኤ የተቆጠረለት፣ ጊዜው ደርሶ በጊዜው ጊዜ ሰውን ለማዳን በግብረ መንፈስ ቅዱስ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሁኖ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በዳዊት ከተማ ቤተልሔም ምድረ ኤፍራታ የተወለደው ዓለምን የማዳን ሥራውን ለመፈጸም የሆነ ነው። ይህም ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቈጠረ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም የሆነ ነው። (ሉቃስ ፪፥፯)

## የክርስትናው ታሪክ አመጣጥ

### ስለክርስትናው ታሪክ አመጣጥ፤

- ከናዝሬት እስከ ቤተልሔም፣
- ከቤተልሔም እስከ ዮርዳኖስ፣
- ከዮርዳኖስ እስከ ቀራንዮ ጎልጎታ፣
- ከቀራንዮ ጎልጎታ እስከ ደብረ ዘይት

በሌላ ዘይቤ

- ከጽንሰት እስከ ልደት፣
- ከልደት እስከ ጥምቀት፣
- ከጥምቀት እስከ ስቅለት፣
- ከስቅለት እስከ ዕርገት የሆነውን የሐዋ ርያነት ሥራ መመልከት ነው።

ይህ ሁሉ የሆነው በተነገረው ትንቢት በተቆጠረው ሱባኤ መነሻነት መሆኑ ግልፅ ነው።

ለዚህ ሁሉ ታሪክ መነሻ የሆነው አዳምና ሔዋን በጠላት ቅስቀሳ እንደ እግዚአብሔር ለመሆን በችኮላ ትእዛዘ እግዚአብሔርን መጣሳቸው ነበር። (ኦሪ.ዘፍጥረት ፫) አዳምና ሔዋን ትእዛዝ ፈጻሚዎች ባለመሆናቸው ከፉውንና ደጉን የማወቁ ጥበብ በጊዜው ሲፈጸም እንደ እግዚአብሔር መሆኑ ግን አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመንን አስቈጥሯል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራውን ፈጽሞ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር ውሎና አድሮ እንደተነሣ «ሑሩ ወመሐሩ...» «ሂዱና አስተምሩ» (ማቴ.፳፰፥፲፱) የሚል ትእዛዝ ለሐዋርያቱ ሰጥቷል።

ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ በመጀመሪያ የነገራቸው የደስታ መግለጫ «ሰላም ለኵልክሙ» «ሰላም ለሁላችሁ ይሁን» የሚል ነው። (ዮሐ.፳፥፲፱)

ይህ ደስታና ሰላምም ፍጹም እንዲሆን ለሁሉም እንዲዳረስ «ሂዱና አስተምሩ» ብሎ ማዘዙና ሁሉም እንዲሰማ ጥብቅ መመሪያ መስጠቱ ዓለሙን ማስተካከል የሚቻለው በሐዋርያነት ሥራ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

ከዚህም ጋር ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ «አንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስከ ትለብሱ ኃይለ እምአርያም» «ከላይ ከአርያም ኃይልን እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ኑሩ» የሚል ነው። (ሉቃስ ፳፬፥፵፱)

ሐዋርያት በበዓለ ጰራቅሊጦስ ዕለት ያን ሰማያዊ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከለበሱ በኋላ አጕልተው፣ አስፍተውና አመስጥረው በማስተማራቸው ጨለማውን አስወገዱ፣ ሀሰትን አሸነፉ፣ ዕርቅንና ሰላምን መሠረቱ፣ በኃጢአት የባርነት ቀንበር ሥር ሁነው ለሚማቅቁት ነፃነትን፣ እኩልነትን አስገኙ።

ሐዋርያት ይህን ትእዛዝ ለመፈጸም ባደረጉት ሐዋርያዊ ጉዞ የትንሣኤን ደስታና የትንሣኤን ሰላማዊ መልእክት በትንሣኤም የተገኘውን ነፃነትና እኩልነት ለመስበክ ባደረጉት ሐዋርያዊ ጉዞ ብዙ መከራንና ስቃይን ተቀብለዋል።

ይሁንና ሐዋርያት በሐዋርያነት ተጋድ ሏቸው እውነተኛውን የሰው ሕይወት መሥርተዋል። በሰው ልጅ እኩልነት የማያምን የነበረውን የሮሚ መንግሥት እንኳ ሳይቀር የክርስትናው ሕይወት ተገዥ እንዲሆን አድርገውታል።

በመሠረቱ የሐዋርያነት ሥራ እንደማ ንኛውም ተግባር ሁሉ ዕለቱን ተጠንቶ ዕለቱን በሥራ ላይ የሚውል አሠራር አይደለም። ከበቂ ትምህርት ጋር የረጅም ጊዜ ልምድና እግዚአብሔርን ለማመስገን ሰውንም ለማገል ገል ራስን አሳልፎ የመስጠት ፍጹም ፈቃደ ኛነትንም ይጠይቃል።

ለምሳሌ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያትና ሰብአ ሁለቱን አርድዕት በሐዋርያነት ሥራ ያሠማ ራቸው ለሐዋርያነት ሥራ ይበቃሉ ያላቸውን መርጦ በመጥራት ሦስት ዓመታት ከሦስት ወራት ካስተማረ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሐዋርያነት ሥራቸውን ጀመሩ። የሥራ ውጤታቸውም ያማረ የሰመረ ሆነ።

በአሁኑ በስምንተኛው ሺህ የሐዋርያነት አሠራር ብርቱ ጥንቃቄን፣ ፈሊጥንና የረቀቀ መንፈሳዊ ጥበብን የሚጠይቅና ዝግጅት የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው። ስለዚህም ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ኩኑ የዋሀነ ከመ ርግብ ወጠቢባነ ከመ አርዌ ምድር» ያለው። (ማቴ.፲፥፲፮)

ለዚህም ወሳኙና ቁም ነገሩ ቅዱሳት መጻሕፍትን አዘውትሮ መመልከትና ደኅና አድርጎ ማጥናቱ ነው። ከዚህም ጋር ጥልቀት፣ ርቀትና ምጥቀት ያለው ዕውቀት ለማፍለቅ የሚቻለው በጥንታውያንና ዘመናውያን የጥበብ ቋንቋዎች የተጻፉትን መጻሕፍት ደኅና አድርጎ በማንበብና በመተርጎም አገናዝቦና አሳክቶ የሐዋርያነት ሥራን መፈጸም ሲቻል ነው።

ከሁሉም በላይ ለሐዋርያነቱ ሥራ ከንውን አስፈላጊው ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ነው።

እግዚአብሔር አምላክ የፈጣሪነቱንና የሐዋርያነቱን ኃይል ከገለጠባቸው ፍጥረታት ሁሉ ተመሳሳይና ተወዳዳሪ የሌለው ታላቅ ፍጡር ሰው ስለሆነ የሰው ሕይወት ከማንኛ ውም ፍጥረት ሁሉ የሚበልጥ የከበረ ነው።

እግዚአብሔር አምላክ እስከሞት ድረስ የወደደውን ዓለም እስከ መጨረሻ በመውደድ የእርሱን አርአያ በመከተል የዓለም ብርሃንና የምድር ጨው ሁነው የሚያገለግሉ ሐዋርያ ትን አስቀምጧል።

የሐዋርያነት ሥራ አመሠራረትና አመጣ ጥም ከዓለም ታሪክ መነሻ እንሥቶ ከዕለት፣ ከሳምንት፣ ከወርና ከዓመት የሰው ሕይወት ጋር ተያይዞ የመጣ መሆኑን ቀደም ሲል ለመናገር ሞክረናል።

የሐዋርያነት ሥራ ብዙ ጊዜ ከፖለቲ ከኞች ሥልጣንና ኃይል ጋር ተቈራኝቶ ስለሚመጣ (ስለሚጓዝ) እንዳይጋጭ በሂደቱ ብርቱ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል።

ለሐዋርያነት ሥራ ትእዛዝ ሰጭው እግዚ አብሔር አምላክ ነው። ትእዛዙን ተቀብለው የሐዋርያነት ሥራቸውን በቅደም ተከተል የተያያዙትም፦

- የዘመነ አበው፣
- የዘመነ መሳፍንት፣
- የዘመነ ነገሥት፣
- የዘመነ ሥጋዌ

ነቢያትና ሐዋርያት እንዲሁም ሊቃ ውንተ ቤተ ክርስቲያን ናቸው።

ይህም የሐዋርያነት ሥራ የነበረ፣ ያለና የሚኖር እስከ ዓለም ፍጻሜ ከሰው ሕይወት ጋር አብሮ የሚጓዝ ነው።

እግዚአብሔር አምላክ በብሉይ ኪዳን አስተማሪዎችን ፈልጎ ነበር። በሐዲስ ኪዳንም ራሱ በሐዋርያነት ተገልጦ ሦስት ዓመታት ከሦስት ወራት አስተማረ። በይቀጥላል የሚያስትምሩ ሐዋርያትንም ሾመ።

ይህን መልእክት የተቀበሉ ሐዋርያትም በመጀመሪያ ሁሉንም አገልግሎት ይፈጽሙ ነበር። ደቀ መዛሙርት እየበዙ ሲሄዱ ግን ሌላውን ዓይነት አገልግሎት በሕዝቡ ለተመረጡት ሰጥተው እነሱ የእግዚአብሔርን ቃል በመስበክ እንደተወሰኑ የሚከተለው ጥቅስ ያስረዳናል።

«የእግዚአብሔርን ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም። ወንድሞች ሆይ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስ የመላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፤ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን። እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን። (የሐዋ.፮፥፪–፬) የሚል ነው።

ከዚህም ጋር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሐዋርያነት የተላከበት ዋና ዓላማ ወንጌልን ለመስበክ እንደሆነ በግልፅ ተናግሯል። (፩ኛቆሮ.፩፥፲፯)

ዛሬም እንደ መጀመሪያው አብዛኛው ሕዝብ አውቃለሁ በማለት የሚኖር ስለሆነ ለሐዋርያነት አሠራር አመች ጊዜ አልሆነም።

ከቅዱሳት መጻሕፍት አንዱ የሆነው የሐዋርያት ሥራ በመባል የታወቀው የመጀመሪያዎቹ የክርስቶስ ተከታዮች (ቤተሰቦች) በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው ስለ እርሱ የሚናገረውን የምስራች ቃል በይሁዳ ሀገር ሁሉ፣ በሰማርያ፣ በገሊላ ከዚያም እስከ ምድር ዳርቻ እንዴት እንዳዳረሱት የሚተርክ (የሚያስረዳ) ነው። መጽሐፉ የክርስትናው እምነት በቤተ እስራኤል መካከል በማዕከለ ምድር ኢየሩሳሌም ተጀምሮ እስከ ዓለም ዳርቻ ደርሶ የመላው ዓለም ሕዝበ ክርስቲያን ሃየማኖት እስከ መሆን ድረስ እየሰፋ መምጣቱንም የሚናገር ነው።

መጽሐፉ የክርስትናው እምነት የቤተ እስራኤልን ሃይማኖት በተሟላ መልኩ ፍጹም ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት መደረጉንም ያስረዳል።

የሐዋርያት ሥራ በመባል የታወቀው ቅዱስ መጽሐፍ የሐዋርያነት ሥራ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ላይ ያደረገውን ኃይል አጕልቶ የሚያሳይ ነው። (የሐዋ.፩፥፰፰)

ይኸው ከላይ ስሙ የተጠቀሰው ቅዱስ መጽሐፍ ሐዋርያት ወንጌለ መንግሥተ ሰማያትን እስከ ዓለም ዳርቻ የማዳረሳቸው ታሪክ ገና ያላለቀ በይቀጥላል እስከ ዓለም ፍጻሜ የሚሄድ መሆኑን የሚያመለክተን ነው።

አሁንም ቤተ ክርስቲያን ይዛ የምትገኘው የሐዋርያነትን ሥራ ነው።

ይህም የሐዋርያነት የአሠራር ዘይቤ ቤተ ክርስቲያንን ከካህናት፣ ካህናትን ከምእመናን፣ ሥራን ከሠራተኛ ለማገናኘት ታላቅ አርአያነትና ምሳሌነት ያለው በመሆኑ ሁሉም አርአያነቱን ለመከተል ጥረት ማድረግ ይገባዋል።

ምንም እንኳ በዓለም በየጊዜው የሚለዋወጥ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የነበረ፣ ያለና እስከ ዓለም ፍጻሜ የሚኖር መሆኑን ብናውቅም ስለሐዋርያነት አሠራር የምንጽፍና የምንናገር ሁሉ የበለጠ ጥንቃቄ በማድረግ አሻሚ ሁኔታዎችን በማስወገድ እውነቱን ለእውነት ፈላጊዎች በማቅረብ ትክክለኛውን የዓለም ሕይወት ገጽታ ለተመልካቹ ለማቅረብ ከፍተኛ ጥረት መደረግ ይኖርበታል።

እንደነ ሙሴና ኢሳይያስ ድክመቱን አውቆ ለእግዚአብሔር ነገሮ በረከትን ተቀብሎ ትእዛዙን የሚፈጽም፤ እንደ ኢያሱ «እኔና ቤቴ እግዚአብሔርን እናመልካለን፤ እናንተም የምታመልኩትን ዛሬውን ምረጡ» በማለት ስፋትና ጥልቀት ወሳኝነትም ያለው ትምህርት የሚሰጥ፤ እንደ ሐዋርያት ጠሪውን ተቀብሎ ሦስት ዓመታት ከሦስት ወራት ሠልጥኖ ሰማያዊ ኃይልን ተጎናጽፎ ሐዋርያዊ ጉዞውን የሚቀጥል ዛሬም ይህ የስምንተኛው ሺህ ዓለም በበለጠ ያስፈልገዋል።

አሁን እኛ የምንኖረው በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት የተነገረበት ብዙ ንቅናቄ በሚታይበት በስምንተኛው ሺህ ዓለም ነው።

ያለንበት ጊዜና ዓለም የሕይወታችንን አቋምና ቅርፅ በብዙ መልኩ ለዋውጦት ይታያል። አዲስ የኑሮ ዘዴም ስለተያዘ የሐዋርያነት ሥራ የሰውን መንፈስ ካለመግዛት ደረጃ መድረሱን እንመለከታለን።

የዛሬዎቹ ነዋሪዎች ዛሬ የሚሠሩትን በሚቀጥለው ታሪክ ያስመዘግባሉ እንጂ የነበረውን ታሪክ መሰረዝ ስለማይችሉ የሐዋርያት ሥራ በነበረው ትውፊት መሠረት በስፋትና በጥልቀት መቀጠል ይኖርበታል።

ከእግዚአብሔር ጋር ያልሆነ ሁሉ ሕይ ወቱ የጨለመ ይሆናልና ነው። ✤

www.ethiopianorthodox.org

# ሥርዓተ ቤተክርስቲያን

## ዘመን ማቴዎስ

አዲሱ ዘመን አስተምሮ የማሳመን፣ ሠርቶ የማሠራት፣ የሰላም፣ የፍቅርና የበረከት ዘመን እንዲሆንልን አበክረን መጸለይ ይገባል፤ ጸሎት ከድንገተኛ ሞት ይሰውራል፤ በዕድሜ ላይ ዕድሜ ይጨምራልና። «በዚያ ወራት ሕዝቅያስ ለሞት እስኪደርስ ታመመ፤ ነቢዩም የአሞጽ ልጅ ኢሳያስ ወደ እርሱ መጥቶ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ትሞታለህ እንጅ በሕይወት አትኖርምና ቤትህን አስተካክል» አለው። ሕዝቅያስም ፊቱን ወደ ግርግዳው መልሶ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ «አቤቱ በፊትህ በእውነትና በፍጹም ልብ ሄድሁ ደስ የሚያሰኝህንም አደረግሁ ታስብ ዘንድ እለምንሃለሁ፤ እጅግ አድርጎ አለቀሰ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኢሳይያስ መጣ፤ ሂድ ሕዝቅያስን እንዲህ በለው የአባትህ የዳዊት አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ጸሎትህን ሰምቻለሁ፤ እንባህንም አይቻለሁ፤ እነሆ በዕድሜህ ላይ አሥራ አምስት ዓመት እጨምራለሁ፤ ኢሳይያስ ምዕራፍ ፴፰፥፪–፮ «እርበላችሁ ኃጢአታችሁን ተናዘዙ ትፈውሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለሌላው ይጸልይ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለችና» (ያዕቆብ ምዕ.፭፥፮) «እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መስዋዕት ሊሰሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮቻችን ፍሬ ለእርሱ እናቀርብለት ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎች ማካፈልን አትርሱ እንዲህ ያለው መስዋዕት እግዚአብሔር ደስ ያሰኛዋልና። (ዕብራውያን ምዕ.፲፫፥፲፭) እያንዳንዱ በክርስትና እምነት ያለ ሰው ሁሉ ጥላቻን በፍቅር፤ ንቀትን በለጋስነት፤ ቁጥዓን በትዕግስት፤ ድልነሥቶ በንስሐ መታደስ አለበት። እንዲህ ከሆነ ከአዲስ ዘመን ጋር አብሮ መጓዝ ይቻላል እንግዲህ ወንድሞቼ ሆይ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስ መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ። እርሱም በጐና ደስ የሚያሰኝ ፍጹም የሆነ ነገር ምን እንደሆነ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ። (ሮሜ. ምዕ.፲፪፥፩–፫)።

## ጸሎት፤

ጸሎት መንፈሳዊ አገልግሎት እንደመሆኑ መጠን ለሥጋና ለነፍስ ጠቃሚ መሆኑ ለማንም አይሰወርም፤ ከብዙ ዘመንም አስቀድሞ የታሪክ ምንጭ ሆኖ እንደቆየ የተረጋገጠ ነው። ጸሎትን ትምህርታዊ መሣሪያ በማድረግ የረቂቃን ጠላቶችን ምሽግ ያፈራረሱ አባቶቻችን ብዙዎቹ ናቸው ስለዚህ ለክርስቲያን ሁሉ ጸሎት መላልሶ መጸለይ እንዲገባ ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል።

ጸሎት ምንድነው? የሚል ሰው ቢኖርም የሰው ልጅ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብበት እግዚአብሔርን የሚያመሰግንበት የላይና የታች ከንፍር ደግሞ የሚያቀርበው መስዋዕት መሆኑን ሊረዳ ይችላል።

በውኑ እንግዲህ የከንፈራችን ፍሬ የሚሆን የምስጋና መስዋዕት ሁል ጊዜ ለእግዚአብሔር ማቅረብ አይገባንም? በስሙ እናምን ዘንድ። (ዕብራውያን ምዕራፍ ፲፫ ቁ.፲፭)

«እስራኤል ሆይ በኃጢአት ወድቀሃልና ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ተመለስ ከእናንተ ጋር ቃልን ውሰዱ ወደ እግዚአብሔር ተመልሳችሁ ኃጢአታችሁን አስወግዱ፤ ተመለሱ በቸርነትም ተቀበሉ፤ እና በወይፈንም ፈንታ የከንፈራችንን ፍሬ እንሰጣለን» (ሆሴ.ም.፲፬ ቁ.፩) እንመልከት እያንዳንዱ ምዕመን እግዚአብሔርን በነፍስ በሥጋ ያገለግለው ዘንድ በእንስሳዊ ባሕርዩ

> **ምሕረት በንስሓ**
>
> ከብፁዕ አቡነ ሳሙኤል
>
> የጅማ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

መጾም በመልአካዊ ባሕርዩ መጸለይ የሚገባ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። እየጾመ ባይጸልይ በሥጋ ብቻ መገልገል እየጸለየ ባይጾምም በነፍስ ብቻ ማገልገል ነውና። በጸሎታቸው ሀገር ይጠብቃሉ በትሩፋታቸውም ያጸድቃሉ ተብለው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተሾሙ አባቶች ቁጥራቸው በርከት ያለ ነው። ጸሎትም በ፯፥ በ፲፪፥ በ፳፬ቱ ጊዜያት መጸለይ እንዲገባ ዳዊት «ስለጽድቅህ ፍርድ ሰባት ጊዜ በቀን አመሰግንሃለሁ ሕግህን ለሚወዱ ብዙ ሰላም ነው ዕንቅፋትም የለባቸውም» (መዝሙር ፩፻፲፰ ቁ.፩፻፷፬ ዘወትርም መጸለይ ተፈላጊ መሆኑን ሲያስረዳ ነቢይ እንዲህ ይላል እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ እባርከዋለሁ ምስጋናውም ዘወትር በአፌ ነው ነፍሲም በእግዚአብሔር ትከበራለች (መዝሙር ፴፫፥፪) ተግቶ ነቅቶ መጸለይ መገባቱን ሲያስጠይቅ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማይታበል አምላካዊ ቃል ይመክረናል። «ስለዚህም ከሚመጣው ነገር ሁሉ እንድታመልጡና በሰው ልጅም ፊት ለመቆም ኃይል እንድታገኙ ሁል ጊዜ ተግታችሁ ጸልዩ» (ሉቃስ ም.፳፩ ቁ.፴፮) ሌላም ይህን የመሰለ እውነተኛ ምስክር አለ «ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጣ ተኝተውም አገኛቸው ጴጥሮስን ከኔ ጋር አንዲት ሰዓት ልትተጉ እንዴት አልቻላችሁም? አለው ወደ ፈተናውም እንዳትገቡ ትጉ ጸልዩም መንፈስ ይወዳልና ሥጋ ግን ደካማ ነው» (ማቴዎስ ም.፳፮ ቁ.፵) በምንጸልይበትም ጊዜ ከቂም ከበቀል ርቀን ከወንድሞቻችን ተስማምተን ቢሆን ነው እንጂ እንዲህ ካልሆነ እግዚአብሔር የምናቀርበውን ምስጋና አይቀበለውም። እምናችሁ «የምትለምኑትንና የምትለምኑትን ሁሉ እንድታገኙ ይሆንላችኋል። ለጸሎትም በተነሣችሁ ጊዜ በወንድሞቻችሁ ላይ ያለውን በደል ይቅር በሉ የሰማይ አባታችሁ ደግሞ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲላችሁ እናንተ ግን ይቅር ባትሉ በሰማይ ያለው አባታችሁ ኃጢ አታችሁን ይቅር አይላችሁም» (ማር.ም.፲፩ ቁ.፳፬) ጸሎትም ከሁሉ አስቀድሞ ተፈላጊ መሆኑን ሲያገናዝብ ሐዋር ያው እንዲህ ብሎ ጽፏል «ከሁሉም አስቀድሞ ጸሎትንና ልመናን ምስጋናን ታደርግ ዘንድ እማልዳለሁ ይህም ይህ ነው ከዚህ ጋራ ለሰው ሁሉ ጸልዩ ኑሮአችን በጸጥታና በሰላም ይሆን ዘንድ በጽድቅና በንጽሕና እንዲሆን በመድኃኒታችን በእግዚአብሔር ፊት የተወደደ የተመረጠ ምስጋና ይህ ነው»። (ጢሞቴዎስ ምዕራፍ ፪ ቁጥር ፩)

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሥርዓተ ጸሎት አፈጻጸም በፍትሐ ነገሥት በፍትሕ መንፈሳዊ እንደታዘዘው ነው። «ጸሎት ብሂል» ጸሎት ማለት ሰው ከልዑል እግዚአብሔር ጋር የሚነጋገርበት እያመሰገነ ጌትነቱን አምና በደሉን አውቆ አምላኩን ደስ ለማሰኘት ለሚጸልይ ሰው የተሠሩ ሥራዓቶች አሉ። እነዚህም በዝርዝር ሲገለጹ፤

፩ኛ. በጸሎት ጊዜ ቀጥ ብሎ በእግር መቆም እንደሚገባ ሥርዓት ተሠርቷል። ይህም «በፅባሕ እቅውም ቅድሜከ ወእስ ተርኢ ለከ» ብሎ ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ እንደገለፀው ነው። (መዝ.፭ ቁ.፫፥)

፪ኛ. ወገብን በዝናር መታጠቅ ሲሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ወገባችሁ የታጠቀ ይሁን ባለው መሠረት ነው» (ሉቃስ ም.፲፪ ቁ.፴፭፥)

፫ኛ. ክርስቶስ በዳግም ምጽአቱ ጊዜ በእርሱ ይገለፁ ዘንድ የተነገረለት ነውና ፊትን ወደ ምስራቅ መልሦ መጸለይ ነው፤

፬ኛ. በመስቀል አምሳል ከላይ ወደታች ከግራ ወደቀኝ በጣት ማማተብ ነው ጌታችን እኔ በእግዚአብሔር ጣት አጋንንትን የማወጣ ከሆነ ብሎ እንደተናገረ በጣት የማማተብ ሁኔታም አጋንንትን ለማራቅ ነው ሉቃስ ም.፲፩ ቁ.፳ ከላይ እስከ ታች፤ ከግራ እስከ ቀኝ ማማተብም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ መውረዱና እኛን ከግራ ወደቀኝ የመመለሱ ነው ተብሎ ይገለፃል። አውራጣትን በሚከተል ጣት በመስቀል አምሳል ማማተብም አምላክ በመስቀሉ ደህንነትን ፈጽሟል። የዚህም ምሳሌ ነው በመስቀል አምሳል የምናማትብባቸው ጊዜአቶችም ጸሎት ሲጀመርና መስቀሉን ከሚያነሳ አንቀጽ ሲደርሱ ነው።

፭ኛ. የሚጸልየው ሰው በመፍራት፤ በመንቀጥቀጥ ሆኖ መጸለይ ይገባዋል። ይህውም የሚጸለየው ጸሎት ልብ ወደ ፈጣሪ የሚስብበት በሐሳብም ሆነ በአንደበት የሚጸልየው ሰው ለኅሊናው መተርጐምም ስለአለበት ነው።



፯ኛ. አስተብርኮና ስጊድ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተያዘበት ሌሊት እንደጸለየና በግንባሩ እንደ ሰገደ በጉልበቱ እንደ ተንበረከከ ቅዱስ ወንጌል ይመሰክራል። የሚሰገዱባቸው ጊዜያቶች በቤተ ክርስቲያናችን ተጽፈዋል የሚጸልይ ሰው በጸሎት ጊዜ ስግደቱን ከሚያነሳ አንቀጽ ሲደርስ ለልዑል እግዚአብሔር ይሰግዳል። ጸሎቱን ሲጀምር አንድ ጊዜ ወይም ሦስት ጊዜያት ይሰግዳል በጸሎት መጨረሻ ስግደት ታዟል። ይህም ሲጀምር ፫ ጊዜ ሰግዶ እንደሆን ሲጨርስ ፩ ጊዜ ይሰግዳል ማለት ነው። ሆኖም ምዕመናን ከስግደትና ከአስተብርኮ የሚከለከሉባቸው ጊዜያት አሉ እነዚህም:-

ሀ. ዕለተ እሁድ

ለ. በዓለ ሃምሳ

ሐ. በጌታችን በእመቤታችን በአላት

መ. ሥጋውን ደሙን ከተቀበሉ በኋላ መስገድ እንዳይገባ ተከልክሏል።

፯ኛ. ነቢዩ ዳዊት «በሌሊት እጃችሁን አንስታችሁ በቤተ መቅደስ እግዚአብሔርን አመስግኑ ብሎ እንደ ተናገረ እጃችንን ዘርግተን መጸለይ እንዲገባ ሥርዓት ተሠርቷል» (መዝሙር ፩፻፴፫)።

፰ኛ. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አልአዛርን ባስነሣው ጊዜ ዓይኖቹን ወደ ላይ አቅንቶ እንደጸለየ የሚጸልይ ሰው ዓይኖቹን ወደ ላይ ማንሳት እንደሚገባው ነው።

ከዚያውም ዘንድ የጸሎት ጊዜያት ተለይተዋል ከ፳፬ቱ ሰዓተ መአልትና ሰዓተ ሌሊት መካከል ለይቶ ፯ ጊዜ መጸለይ ይገባል በማለት ሥርዓት ተሠርቷል። (መዝ.፩፻፲፰ ቁ.፩፻፷፬)

እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

፩ኛ. የሚጸልየው ሰው ከእንቅልፍ ነቅቶ ከመኝታው ተነስቶ ገና ሥራ ሳይጀምር የሚጸልየው ጸሎት ነው።

፪ኛ. በ፫ ሰዓት የሚጸለይ ጸሎት አለ፤

፫ኛ. በስድስት ሰዓት የሚጸለይ ጸሎት ነው።

፬ኛ. በዘጠኝ ሰአት የሚጸለይ ጸሎት ነው።

፭ኛ. በሠርክ የሚጸለይ ጸሎት ነው።

፮ኛ. በመኝታ ጊዜ የሚጸለይ ጸሎት ነው።

፯ኛ. በመንፈቀ ሌሊት የሚጸለይ ጸሎት ነው።

በተለይ የጧትና የሠርክ ጸሎት በቤተ ክርስቲያን መሆን እንዲገባ ሲታዘዝ ይልቁን በቅዳሜና በእሁድ ቀን ሳይታመም ከጸሎት የተለዩ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ይመከራል። የ፫ ሰዓትና የሌሎች ጊዜያት ጸሎት ግን በቤትም ቢሆን በሌላ ቦታ መጸለይ አይከለከልም። በእነዚህ ጊዜያቶች በአንዷቱ የመጸለያው ጊዜ በደረሰና የሚጸልየው ሰው ለመጸለይ ከማይች ልበት ቦታ ቢሆን በልቡ የኅሊና ጸሎት ማድረስ እንዲገባው ታዟል።

ካህናት ሊጸልዩት የሚገባ ጸሎት ግን በቤተ ክርስቲያን መሆን አለበት ይህም

፩ኛ. ጸሎተ ጥምቀት

፪ኛ. የቅዳሴ ጸሎት

፫ኛ. የካህናት ሹመት ጸሎት

፬ኛ. ታቦተ ሕግና ቤተ ክርስቲያን ሲባረክ የሚጸለይ ጸሎት

፭ኛ. የሥርዓተ ተክሊል ጸሎት

፮ኛ. የሕሙምተኞች ጸሎት (ጸሎተ ቀንዲል)

፯ኛ. ጸሎተ ፍትሐት እነዚህ ሁሉ በቤተ ክርስቲያን መፈጸም እንዳለባቸው ተሠርቷል።

ጸሎተ ማዕድ ከምግብ በፊት ሆነ ከምግብ በኋላ መጸለይ ይገባል ከምግብ በፊት የሚጸለየው ጸሎት እግዚአብሔር የሚበሉትን ይባርክና በረከት ያሳድርባቸው ዘንድ ሲሆን በመጨረሻም ምግቡ ሰውነትን የሚጠብቅ ለደህንነት ያደርገው ዘንድ ነው የሚጸለይ። ሰው የተለያዩ የጸሎት መጻሕፍት እንደ መዝሙረ ዳዊት እንደ ስብሐተ ሙሴና መሐልየ ነቢያት እንደ መሐልዩ ሰለሞን እንደ ውዳሴ አምላክ እንደ ውዳሴ ማርያምና የመሳሰሉትን ሁሉ ከደረሰ በኋላ ጸሎቱን የሚያሳርገው በአቡነ ዘበሰማያትና በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አልአዛርን ባስነሳው ጊዜ ዓይኖቹን ወደ ላይ አቅንቶ እንደ ጸለየ ሁሉ የሚጸልይ ሰው ሁሉ ዓይኖቹ ወደ ላይ ማንሳት እንደሚገባ ነው (ዮሐ. ም.፲፩፥፵፩)።

## ምሕረት በንስሓ

ኃጢአት ሲሰሩ አይቶ ረዘም ያለ የዕድሜ ቀጠሮ ሰጥቶ ሲወጣ በንስሐ ለመጥራት የሚያደርገው ቸርነት ነው እግዚአብሔር ሰው በኃጢአት ሳለ በንስሐ ሳይመለስ በሞት ገመድ ተጠልፎ ከዚህ ዓለም እንዲለይ ፍጹም ፈቃዱ አይደለም።

ስለዚህ ቀድሞ በነቢያት አድሮ እግዚአብሔር እንዲህ ይል ነበር «እኔ ሕያው ነኝና ኃጢአተኛው ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ይኖር ዘንድ እንጂ ኃጢአተኛው ይሞት ዘንድ አልፈ...ም» (ሕዝ.ም.፴፫፥፲፩) ደግሞ በዘመነ ሐዋርያት ስለ እግዚአብሔር ቸርነትና ትዕግሥት እንዲህ ይላል ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው እግዚአብሔር ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሳል» (፪ጴጥ.ም.፫፥፱) እግዚአብሔር ለዚህ በጎ ይደረግለት ለዚያ ክፉ ይደረግበት የማይል እውነተኛ ዳኛ ነው። የማያዳላ ሚዛንም ነው እግዚአብሔር ሰው በኃጢአት እየወደቀ ከክብር ተለይቶ እንዳይቀር ትልቅ፤ ትንሽ፤ ድሃ፤ ባለጸጋ፤ ወንድ፤ ሴት ልጅ፤ ሽማግሌ ሳይል ለሁሉ የንስሐ ዓለም አዘጋጅቶ ይጠብቀዋል ሰው ኃጢአት ሠርቶ የንስሐ ትዝታ ካልኖረው ልመናው በእግዚአብሔር ዘንድ አይሰማም፤ ፈቃዱም አይፈጸምለትም፤ እግዚአብሔርም ምሕረቱን ረድኤቱን ያርቅበታል፤ የቸርነት ዓይኑን ይዘጋበታል፤ «እጆቻችሁን ወደ እኔ ብትዘረጉ ዓይኔን ከእናንተ እሳውራለሁ ልመናንም ብታበዙ አልሰማችሁም እጆቻችሁም ደም ተሞልተዋልና ታጠቡ ሰውነታችሁንም አንጹ» (ኢሳ.ም.፩፥፲፭–፲፮)።

## ስለዚህ ማርያም እንተ ዕፍረት

ስለ ኃጢአት ሰውነትዋ ያፈሰሰችውን ዕንባዋን የሰጠችውን ገንዘብዋን በልቡና ጽላት ጽፎ ማስታወስ ይጠቅማል፤ የማርያም እንተ እፍረትም ታሪክ መምሕራን እንደሚከተለው ይተርኩታል ከዕለታት አንድ ቀን ትልቅ መስታዋት ፊት ለፊት ዘርግታ የመልከዋን ውበት የገላዋን ጽርየት ስትመለከት፤ መልክ ቢያምር ውበት ቢያሸበርቅ ሞት ምንም የማይቀር የሰው እዳ መሆኑን ተገነዘበች፤ ወዲያው (ኢመጻእኩ እደውእ ጻድቃነ አላ ኃጥአነ ለንስሐ ማቴ.፱፥፲፫) ኃጥአንን ለንስሐ ልጠራ መጣሁ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም እያለ ሥርየተ ኃጢአትን የሚያስተምር ኢየሱስ ክርስቶስ ትዝ አላትና ምን እበላለሁ ምን እጠጣለሁ ሳትል በሦስት መቶ ወቄት ወርቅ ሽቶ ገዝታ ወደ ዓለሙ መምህር ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሄደች በዚህ ጊዜ ሽቶውን ምንም ሳታስቀር በክርስቶስ ራስ ላይ አፈሰሰችው እርሷም ስለኃጢአቷ ሥርየት እየለመነች ከልቅሶዋ ብዛት የተነሳ እግሩን በዕንባ አጠበችው በራሷ ጠጉሯም ወለወለች ጌታም ኃጢአት ተሰረየልሽ ሃይማኖትሽ አዳነሽ ብሎ ከኃጢአት ንጽሕት አደረጋት፤ (ሉቃ.ም.፯፥፵፮–፶)።

ስለዚህ ፈረስኛ ሲሮጥ እግረኛ ምን አቶመው እንደሚባለው እያንዳንዱ አማኝ ክርስቲያን ሁሉ የመጻሕፍትን ስልታቸውን ማወቅ ምክራቸውን መቀበል ይኖርበታል። ✝



www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ሃይማኖት

ትምህርት የሚያቀርቡልን ታላቁ ሊቅ መልአከ ገነት ገ/ሥላሴ አወቀ ናቸው።

በዛሬው እትም በነገረ መለኮት ሐተታ ሰፊ ትምህርት የሚያቀርቡልን ታላቁ ሊቅ መልአከ ገነት ገ/ሥላሴ አወቀ ናቸው። መልአከ ገነት ገ/ሥላሴ አወቀ ከዚህ ቀደምም ጥልቅ በሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች እና ለመናፍቃን መልስ የሚሆን ጠቃሚ ቁም ነገሮችን አቅርበውልናል። አሁንም ጥልቀትና ምጥቀት ያለው ትምህርታቸውን እነሆ ፈለገ ጥበብ መጽሔታችን ይዛላችሁ ቀርባለች።

ከመልአከ ገነት ገ/ሥላሴ አወቀ የምናገኘው ትምህርት እጅግ ሰፊና የረቀቀ ትምህርት በመሆኑ ዛሬም አንባቢ በቀላሉ በሚረዳበት መልኩ የእግዚአብሔር ህላዌ፣ የመለኮት ትርጉም፣ የእግዚአብሔር ምሉዕነት፣ የእግዚአብሔር አንድነት፣ ተዋሕዶተ ሕሉና የመሢሕ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ትርጉምና እና በሌሎችም ንዑሳን ርእሶች ብዙ የሚሉን አሉና እንከታተላቸው።

አዘጋጅ ዕንቁባሕርይ ተከሥተ

## የእግዚአብሔር ህላዌ

ህላዌ ባሕርይ፣ ህላዌ አካል፣ ህላዌ ሥልጣን፣ ህላዌ ጥበቃ ይሆናል።

ባሕርይ በሚሆንበት ጊዜ አለመ መርመር፣ ኢኗኗር (አንዋር) በዚህ ጊዜ ነበረ፣ በዚህ ጊዜ ያልፋል አይባልም።

ህላዌ አካል ሲሆን ለአብ ሙሉ አካል፣ ለወልድ ሙሉ አካል፣ ለመንፈስ ቅዱስ ሙሉ አካል አለው ማለት ነው።

ህላዌ ባሕርይ ሲሆን ሕላዌ ዘአብ፣ ህላዌ ዘወልድ፣ ህላዌ ዘመንፈስ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ ኀቡረ ህላዌ። የአብ ህላዌ፣ የወልድ ህላዌ፣ የመንፈስ ቅዱስ ህላዌ አንድ ህላዌ ነው። (ቅዱስ ያሬድ)

ህላዌ ኢኗኗር ሲሆን «ዘሃሎ ወይሄሉ» ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር አስገኝ የሌለው ማለትን ያሳያል።

ህላዌ ጥበቃ ሲሆን እሱ ወዳጆቹን ከአጋንንት ይጠብቃቸዋል፣ ከመቅሰፍት፣ ከመከራ ያድናቸዋል። ፍጥረቱን ሁሉ ጠብቆ ያኖራል ማለት ነው።

«እመ እግዚአብሔር ኢአቀበ ሀገረ ከንቶ ይትጌሑ እለይሄልው (መዝ.፻፳፮፥፪) እግዚአብሔር ሀገርን ካልጠበቀ ጠባቂዎች በከንቱ ይተጋሉ»

## መለኮት

መለኮት፣ መለከ ገዛ ካለው የወጣ፣ መለኮት፣ ግዛት፣ መለኮት ሥልጣን፣ መለኮት ስም፣ መለኮት አካል፣ መለኮት ባሕርይ ነው።

ስም ሲሆን «መለኮትሰ ስም ዘአልቦ ብዕድና» መለኮት መለያየት የሌለበት ስም ነው፤ ይላል (ቅዱስ ቄርሎስ) የሦስቱ መጠሪያ ነው። «አብ መለኮት፣ ወልድ መለኮት፣ መንፈስ ቅዱስ መለኮት፣ አሐዱ አምላክ» እስመ ሰለስቱ ጉልቄ መለኮቱ» ሲል የአካሉ ቁጥር ሦስት ነው ማለት ነው። (ተረፈ. ቄርሎስ)።

መለኮት ሥልጣን ግዛት ሲሆን «ውስተ ኵሉ በሐውርት መለኮቱ» ፍጥተቶቹ ሁሉ በግዛቱ ሥፍራ ሁሉ መዝ.፻፪

መለኮት ባሕርይ ሲሆን «ይሴለሱ በአካላት ወይትወሐዱ በመለኮት «በአካለ ሦስት ሲሆን በመለኮት (በባሕርይ) አንድ ይሆናሉ ባሕርይ ሲሆን የአንድነት መጠሪያ ነው። ወላዲ መለኮት፣ ተወላዲ መለኮት፣ ሠራጺ መለኮት አይባልም አብ መለኮት ወልድ መለኮት መንፈስ ቅዱስ መለኮት ይባላል እያሉ ሰውን ወደ ክደት የሚወስዱ አሉና ከእነዚህ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ወላዲ የተባለ አብ ነው፣ ተወላዲ የተባለው ወልድ ነው፣ ሠራጺ የተባለው መንፈስ ቅዱስ ነው። ወላዲ መለኮት፣ ተወላዲ መለኮት፣ ሠራጺ መለኮት አይባልም? አብ መላኮት፣ ወልድ መለኮት፣ መንፈስ ቅዱስ መለኮት ይባላል የግብር ስም ነው ይላሉ። ይሄ ሰውን ግራ ለማጋባት ነው እንጂ ግብር የሌለው የአካል ስም የለም። ወላዲ የተባለ አብ ነው። ተወላዲ የተባለ ወልድ ነው፣ ሠራጺ የተባለ መንፈስ ቅዱስ ነው። ይህ ማለት ግን ሦስት አማልክትን የሚያስተረጉም እንዳልሆነ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ሕሉና መለኮት ማለትም የባሕርይ አንድነት የባሕርይ እኗኗር ማለት ነው «ማኅደረ መለኮት» ሲል እመቤታችንን ማኅደረ አምላክ የአምላክ ማደሪያ (ወላዲተ አምላክ) ማለት ነው። ቅዱስ ያሬድ እመቤታችንን ማኅደረ መለኮት የመለኮት ማደሪያ» ሲል ገልጿል።

## እግዚአብሔር ረቂቅ ነው አይዳሰስም (አይገሠሥም)

እግዚአብሔር ረቂቅ ነው አይዳሰስም ረቂቅ ነው አካል አለው፣ አካል አለው ረቂቅ ነው። እንዲህ ነው፣ እዚህ አለ፤ እዚያ የለም፤ አይባልም። ሰማይና ምድርን በእጁ ይዟል። አንድ ጣቱ በዓለም ውሉ ነው የቀረውሳ? ቢሉ አይታወቅም ነው መልሱ። ግራ ቀኝ የለውም፤ «ወልድ ነበረ በየማነ አብ» ሲል በአብ ቀኝ ተቀመጠ ማለት አይደለም። በክብር ተስተካከለ ማለት ነው። ክብር ዕሪናውን ሲያመለክት ነው። «እስመ ብሂለ የማንስ ያኤምር ኀበ ተዋሕዶቶሙ በክብር» «ቀኝ ማለትስ የአንድነት ክብራቸውን ያመለክታል። አካሉ እዚህ ላይ ነው፤ እዚህ ላይ ይቀመጣል አይባልም።



## እግዚአብሔር መንፈስ ነው።

እግዚአብሔር መንፈስ ነው መንፈስ ማለትም አይያዝ፣ አይዳሰስም ማለት ነው። እንኳን እግዚአብሔር እሱ የፈጠራቸው መላእክትም ረቂቃን ናቸው። ከፍጥረታት ሁሉ በዚሁ ዓለም ነፋሳት ይረቃሉ፤ ከነፋሳት መላእክት፣ ከመላእክት ነፍሳት፣ የነፍሳት ርቀት ደግሞ በሥላሴ ዘንድ እንደ ተራራ ግዙፍ ነው። ከሁሉም ደግሞ የእግዚአብሔር ርቀት ይበልጣል። ከነፋሳት መላእክት፣ ከመላእክት ኀሊናቸው፣ ከኀሊናቸው የእኛ ነፍስ አይመረምርም።

## እግዚአብሔር ሙሉ ነው አይወሰንም።

«አነ እመልእ ሰማየ ወምድረ እኀዝ ዓለም በእራሁ ኵሉ እጉዝ ውስተ እደሁ»

«እኔ ሰማይና ምድርን የመላሁ ነኝ። ሁሉ በእጁ የተያያዘ በእጁ ዓለምን የያዘ ነው። «አማንኑ ይነብር እግዚአብሔር ምስለ ዕጓለ መሕያው ውስተ ምድር ዘሰማይ ወሰማየ ሰማያት ኢየአክሉ ወባሕቱ ዝንቱኒ ቤት ዘሐነፅኩ ለስምከ» ጠፈር፣ ከሰማዮች በላይ ያለ ሰማይም የማይወስነው እግዚአብሔር እውነት ከሰው ጋር በምድር ይኖራል ብዬ ነውን? ነገር ግን ይህ የሠራሁት ቤት መቅደስ ስምህ ሊመሰገንበት ነው። (፩ኛነገ. ቁ.፳፯)

«ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ሰማይኒ መንበርየ ወምድርኒ መከየደ እገር የአየኑ ቤተ ተሐንፁ ሊተወእየኑ ማኅደረ ለምዕራፍየ»

«እግዚአብሔር እንዲህ አለ ሰማይ ዙፋኔ ነው። ምድርም የእግሬ መርገጫ ናት። ቤትን ወዴት ትሠሩልኛላችሁ? የማድር በትስ ቤት ወዴት ነው። (ኢሳ. ፷፮፥፩)። ለስሙ መጠሪያ ቤተ እግዚ አብሔር ተሠራ ተባለ እንጂ እግዚአብሔር ሰው በሠራው ጐጆ ተወስኖ የሚቀመጥ አይ ደለም።

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር መሉዕ ሰማያተ ወምድረ»

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚ አብሔር በሰማያትና በምድር ምሉዕ ነው።

እግዚአብሔር በሕልም፣ በራእይ፣ በአካልም የሚታያቸው አለ፤ ይህም በፈቀደው ባሕርይ ይባላል። ለምሳሌ ለሙሴ «በአምሳለ ሐመልማል ወነበልባል» በሐመልማልና በነበልባል አምሳል ታይቶ ታል።

ለጌዴዎን በአምሳለ ፀምር ወጠል።

ለእዝራ በአምሳለ ነፋስ ወአንበሳ በነፋስ አምሳልና በአንበሳ ተመስሎ ታይቶታል።

«እስመ በእንጽሖ መንፈስ ርዕይዎ ነቢያት ለእግዚአብሔር»

ልብን ንፁህ በማድረግ ነቢያት እግዚአብሔርን አይተውታል። በቀረው በአካልነቱ (በባሕርዩ) ማንም ሊያየው አይችልም። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ

«ለእግዚአብሔር አልቦ ዘርእዮ ግሙራ»

ብሉ እንደገለጸው እግዚአብሔርን በሙሉዕነት ፈጽሞ ያየው የለም። በፈቀደው ይታያል ማለትም፣ ለስብእ ስገል ወርቅ ላመጣው ሕፃን፣ ዕጣን ላመጣው ጐበዝ፣ ከርቤ ላመጣው አረጋዊ መስሎ ታያቸው። ኋላ እርስ በርሳቸው እንዴት ያለ መልካም ሕፃን ነው? መልካም ጐበዝ እንጂ፣ መልካም አረጋዊ እንጂ ተባባሉ ተመልሰው ቢገቡ በአምሳለ ሕፃን ለታየው በአምሳለ ወሬዛ፣ በአምሳለ ወሬዛ ለታየው በአምሳለ አረጋዊ፣ በአምሳለ አረጋዊ ለታየው በአምሳለ ሕፃን ታያቸውና አንዱ ነገር እንደ አንተ ነው አለ፣ ሁለተኛውም እንደ አንተ ነው እንጂ፣ ጐበዝ የለም ሽማግሌ ነው ሲባባሉ መልአኩ እንደ ሁላችሁ ነው ሲላቸው ተመልሰው ቢገቡ በአምሳለ አረጋዊ ለታየው በአምሳለ ሕፃን፣ በአምሳለ ሕፃን ለታየው በአምሳለ ወሬዛ፣ በአምሳለ ወሬዛ ለታየው በአምሳለ አረጋዊ ታያቸው። ስለዚህ ፍጹም አምላክነቱን ተረድተው ተመልሰው ሄዱ።

## የእግዚአብሔር አንድነት

የእግዚአብሔር አንድነቱ በባሕርይ፣ በሥልጣን፣ በጌትነት፣ ባለመርመር፣ ባለመታመም፣ ባለመሞት በሕያውነት በመኖር፣ አምላክ፣ ፈጣሪ፣ እግዚአብሔር በመባል ነው። ይህ ሁሉ የአንድነት ነው።

ሦስትነት ሲሆን አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ፣ ይባላል። የሦስትነት ስሙ ነው።

ይኸውም የአንድ ስም ወደ ሌላ ስም አይፈልስም፤

«ኢይፈልስ ስመ አብ ለከዊነ ስመ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወኢይፈልስ ስመ ወልድ፣ ለከዊነ ስመ አብ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወኢይፈልስ ስመ መንፈስ ቅዱስ ለከዊነ ስመ አብ ወወልድ»።

ማለት የአብ ስም የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ስም ወደ መሆን አይፈልስም፣ (አይለወጥም)። የወል ድም ስም የአብና የመንፈስ ቅዱስ ስም ወደ መሆን አይፈልስም ወይም አይለወጥም። የመንፈስ ቅዱስ ስምም የአብና የወልድ ስም ወደ መሆን አይፈልስም (አይለወጥም) እንዲል፣ ሃይማኖተ አበው ዘእግናጢዮስ ፲፩ ቁጥር ፳።

«ወለለ አሐዱ አሐዱ እምነ አካላት ፍጹም በገጹ ወበመልክዑ፣ አብኒ አብ ውእቱ፣ ወወልድኒ ወልድ ውእቱ፣ ወመንፈስ ቅዱስኒ መንፈስ ቅዱስ ውእቱ። ወለለ አሐዱ አሐዱ እምአካላት ኢይትዌለጡ እምህላዌሆሙ፣ አብሂ ለከዊነ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወወልድሂ ለከዊነ አብ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወመንፈስ ቅዱስሂ ለከዊነ አብ ወወልድ»

ማለት ከአካላት አንዱም አንዱ ከባሕርያቸው አይለወጡም፣ አብ ወልድን መንፈስ ቅዱስንም ለመሆን አይለወጥም፣ ወልድም አብን መንፈስ ቅዱስን ለመሆን አይለወ ጥም፣ መንፈስ ቅዱስም አብን ወል ድን ለመ ሆን አይለወጥም።» እንዳለ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ሃይማኖተ አበው ዘጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ፳፥፩፣ ፳–፴።

«አብ አሐዱ ፍጹም በአካሉ ወወልድ አሐዱ ፍጹም በአካሉ፣ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ ፍጹም በአካሉ፣ ወእኮ እሉ ከመ መዓርገ መንግሥት አላ አሐዱ መለኮቶሙ ወአሐደ ምኵናኖሙ ወአሐዱ ሥምረቶሙ ወአሐዱ ፈቃዶሙ፣ ወአሐዱ ምልክናሆሙ፣ ወአሐዱ እግዚአብሔር ፈጣሬ ሰማያት ወምድር ወባሕር ወኵሉ ዘውስቴቶሙ»።

ማለት አብ በአካሉ ፍጹም አንድ ነው፣ ወልድም በአካሉ ፍጹም አንድ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም በካሉ ፍጹም አንድ ነው፤ እነዚህ ሦስቱ እንደ መንግሥት መዐረግ አይደሉም፣ ባሕርያቸው አንድ፣ አገዛዛቸው



www.ethiopianorthodox.org

አንድ፣ አሳባቸው አንድ፣ ፈቃዳቸው አንድ፣ አምላክነታቸው አንድ ነው እንጂ። ሰማይን፣ ምድርን፣ ባሕርን፣ በውስጣቸው ያለውን ሁሉ የፈጠረ እግዚአብሔር አንድ ነው» እንዳለ ቅዱስ ቄርሎስ። ሃይማኖተ አበው ዘቄርሎስ ፸፩፥፫ ቁ.፪።

እንደዚህም ደግሞ የአንድነቱ ስም አምላክ፣ ፈጣሪ፣ እግዚአብሔር፣ ንጉሥ፣ ጌታ ይባላል።

ስለዚህ አንድ የሚሆኑበት ስም አለ። የሚለያዩበት ስም አለ ማለት ነው። በምሥጢረ ሥጋዌም፣ አማኑኤል፣ ኢየሱስ፣ ክርስቶስ፣ መድኃኔ ዓለም ይባላል። ይህ ሁሉ ስመ ሥጋዌው ነው። ማለት እግዚአብሔር ወልድ ብቻ የሚጠራበት ነው። አብ፣ መንፈስ ቅዱስ አይጠሩበትም። ሰው ልጅነት የሚቀበለው ከእግዚአብሔር በመሆኑ፣ «አጠምቀከ በአብ፣ አጠምቀከ በወልድ፣ አጠምቀከ በመንፈስ ቅዱስ» በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቃሃለሁ። ይባላል (ማቴ.፳፰፥፲፱) እንጂ በፍጡር ስም አጠምቅሃለሁ አይባልም።

«ዘኢተወልደ እማይ ወእመንፈስ ቅዱስ ኢይሬእያ ለመንግሥተ እግዚአብሔር «ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ መንግሥተ እግዚአብሔርን አያያትም፣ ተብሎ በወንጌል ተጽፎአል። እማይ ወልድ፣ እመንፈስ ፡ መንፈስ ቅዱስ፣ መንግሥተ እግዚአብሔር አብ ነው። ከሦስቱ ያልተወለደ መንግሥተ ሰማይን አይወርስም ተብሏል። ዮሐ.፫፥፭።

አዳምና ሕያዋንን ልጅነት ያገኙ ከአብ፣ ከወልድ፣ ከመንፈስ ቅዱስ፣ እንጂ ከሌላ አይደለም። በፍጡራን ስም ሊጠራ የሚገባው አለማዊው ስም ነው።

## ተዋሕዶተ ሕሉና

ተዋሕዶተ ሕሉና ማለት የባሕርይ አንድነት ማለት ነው «ኮነ» (ኾነ) ሲል ተለወጠ ማለት አይደለም፣ ሳይለወጥ ሰው ኾነ ማለት ነው። በኮነ የተነሱ መናፍቃን በኃደረ፣ በኃደረ የተነሡ መናፍቃን በኮነ ይረታሉ። ኀደረ ያለው ይዘው ኀድረት ነው፣ በጻድቃን እንድያድር አደረበት እንዳይሉ «ኮነ» ሰው ሆነ አለባቸው። ኮነ ያለው ይዘው እንደማየ ቃና እንደብእሲተ ሎጥ ተለወጠ እንዳይሉም ኀደረ አለባቸው። ስለዚህ «ኮነ እና ኀደረ» የተዋሕዶን ምሥጢር ያስረዳሉ።

በእነዚህ ሐሳቦች እነንስጥሮስ እነ ሳምሳጢ ጳውሎስ የመሰሉ መናፍቃን ተነስተው ነበር። ንስጥሮስ «ማርያም ሰው ወለደች በዚያ ወልደ እግዚአብሔር አደረበት» ብሎ ተነሳ ፪ መቶ ሊቃውንት አውግዘው ለዩት።

ብዙዎች መናፍቃን መሲሕ በሚል ቃል ይሳሳታሉ፣ በመሠረቱ መሢሕ ማለት የከበረ አራት ሽቱ አምስተኛ ዘይት የሚቀባ ከነገደ ሌዊ የተወለደ ሊቀ ካህናት ከነገደ ይሁዳ የተወለደ ንጉሠ ነገሥት ማለት ይሆናል።

ጌታ ግን እንደ አራቱ ሽቱ አራቱ ባሕርያተ ሥጋ፣ እንደ አምስተኛ ዘይት አምስተኛ ባሕርየ ነፍስን ነስቶ ሰው ሆኖአል።

እንደ ቅባቱ የባሕርይ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ፣ በሥጋ ደግሞ የባሕርይ ሕይወት ሆነው። ክርስቶስ ማለት የከበረ ንጉሥ ማለት ነው «ክርስቶስ ንጉሥነ እንዲል» ኢየሱስ ማለት አዳኝ (መድኃኒት) ማለት ነው። «ኢየሱስ መድኃኒነ እንዲል» ኢየሱስ ሲተረጎም «ወኢየሱስ ይተረጐም መድኃኒተ እስመ ተወልደ እምብእሲት ወአድኃነ ሕዝቦ» ኢየሱስ ከሴት ተወልዶ ሕዝቡን አድንዋልና መድኃኒት ይባላል።

«ቀብዐ» ብሎ አከበረ ማለት እንጂ አዋሐደ የሚል ትርጉም አይሰጥም ። «ቀብዐን» አዋሐደ ብሎ መተርጐም ስሕተት ነው።

«ኢትግሥሡ መሢሐንየ» ሲል እነዚህ ተቀብተው የተሾሙት ነቢያቶቼን አትዳስሷቸው ማለት አትጣልዋቸው መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው የከበሩ ናቸውና ማለት ነው።

ክርስቶስ የሚለው መሢህ ከሚለው ጋር አንድ ነውይ? ተብሎ ቢጠይቅ በያዕቆባውያን ዘንድ ለየት ያለ ሐሳብ አለ፣ ይኸውም «ወሰመ ክርስቶስ በኅበ ያዕቆባውያን አሐዱ አካል ወአሐዱ ህላዌ» በእስክንድርያ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ተብሎ ሲተረጐም በእስራኤላውያንና በቅባቶች ግን መሢሕ ማለት ክቡር በመንፈስ ቅዱስ የከበረ ማለት ነው ይላሉ። አያስኝም፣ ስሕተት ነው።

«ቀብዐ» አከበረ እንጂ፣ አዋሕደ የሚል ትርጉም አይሰጥም።

«ቅብዕ» ብሂል ክብር ብሂል «ቅብዕ ማለት ክብር ማለት ነው እንዳለ (ቅዱስ ቄርሎስ)

«ወብእንተዝ ቀብዓከ እግዚአብሔር አምላክከ» ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ አከበረህ» ሲል፣ ፍጡር ሥጋን ስለተዋሐደ ፈጣሪ፣ አከበረህ አለ። መዝ.፵፬፥፫። ክርስቶስ ብሎ ትንቢት የተናገረ ነቢዩ ኤርምያስ ነው (ተረፈ ኤር.፯ ቁ.፫) መሢሕ ብሎ የተነበየ ነቢዩ ዳንኤል ነው። (ዳን.፱ ቁ.፳፭–፳፯)።

ኢየሱስ ተብሎ ይጠራል ያለ መላእክ እግዚአብሔር ነው። (ማቴ.፩ ቁ.፳፩)። ኢየሱስ ማለት መድኃኒት፣ ክርስቶስ ማለት የከበረ ንጉሥ ማለት ነው። «ኢያእመሩ ስሞ ለክርስቶስ» ክርስቲያን ሲባሉ የክርስቶስን ስም አላወቁም ሲል ቅዱስ ቄርሎስ ይነቅፉቸዋል።

ክርስቶስን የጸጋ ልጅ የሚሉ መናፍቃን አሉ፣ የእነዚህ መናፍቃን አባባል መሠረታዊ ስሕተት እንዴት ይታያል? ቢባል ደግሞ፣ እንደዚህ ዓይነቱ ስሕተት እንደ ንስጥሮስ ከህደት (ኀድረት) ይባላል። የጸጋ ክብር የሚሰጠው ለፍጡር ነው፤ ማለት እንደ አዳምና ሕያዋን፤ እንደ ነቢያት፤ እንደ ዳዊት፣ እንደ ሰሎሞን፣ ማለት ነው። ጸጋ ማለት ሰው ወደ እግዚአብሔር ሲቀርብ የሚሰጥ ሲሆን ኃጢአት ሲፈጽም ይነሣዋል ማለት ነው።

የክርስቶስ ክብሩ የባሕርዩ ነው እንጂ የጸጋ አይደለም። የጸጋ ክብር የሚነሳ ነውና። የጸጋ ክብር ከበረ ካሉት ክርስቶስን ፍጡር አደረጉት፣ እንደዚሁ እንደፍጡራት እንደ አዳም እንደ ነቢያት፤ ሲሞት ተኰነነ፤ ሞቶ በስብሶ ቀረ ማለታቸው ነው።

እንዲህ ማለት ደግሞ ፍጹም ክሕደት ነው። ሰው ዛሬ በጥምቀት የሥላሴ ልጅ ሆነ፤ ነገ ኃጢአት ሲሠራ ጸጋው ተለይቶት ይሄዳል። እሱ ግን፤ የባሕርይ አምላክ ነውና ኃጢአት አልሠራም [illegible]

ስለዚህ በሰውነቱም በአምላክነቱም የባሕርይ ክብር ነው የከበረ እንጂ የጸጋ ክብር አይደለም።

ጸጋ ማለት የሚነሳ ክብር ማለት ነው፤ የሚሰጠውም ለፍጡር እንጂ ለፈጣሪ አይደለም። ይህን የኑፋቄ ትምህርት ወደ አገራችን የመጣው (የገባው) ፩ኛ. አፄ ሱስንዮስ ደ ንቀዝ ላይ ነግሦ ሳለ ፪ኛ. በርጉም ተክለ ሃይማኖት ዘመነ ንግሥና ነው።

ቆሪጥ ተክለ ሃይማኖት የጸጋ እምነትን፣ መናፍቅ ኤዎስጣቴዎስ የቅብዓት እምነትን አስተማሩ ይላል።

በደጉ ኤዎስጣቴዎስ አስጠግቶ፣ ይኼ የኤዎስጣቴዎስ ሃይማኖት ነው ብሎ፣ የቅብዓት እምነትን፣ (በቀብዓተ መንፈስ ቅዱስ ከበረ)

ቆሪጥ ተክለ ሃይማኖት ደግሞ ደብረ ሊባኖስን መካነ ኢየሱስን፣ በዓታ ጉንደርን፣ የጸጋ ትምህርትን አስተምረዋል።

ክርስቶስን የጸጋ ልጅ ከሚሉ፣ ብዙ የሚለዩ የማይመስሉ የቅብዓት ሃይማኖትን የሚከተሉ መናፍቃን እንዳሉ ይነገራል። የእነዚህስ መሠረታዊ ስሕተት ምንድነው ቢባል መነሻ ሐሳቡ የንስጥሮስ ክህደት ነው። ይኸውም ቅብዓት ማለት ኀድረት ማለት ነው። ቅብዓቶች ሥጋ ማርያምን በቅብዓተ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ሆነ ይላሉ፣ የሥጋ ንዴት እንዳይተላለፍበት ቅብዓተ መንፈስ ቅዱስ ንዴትን አጠፋለት ይላሉ።

እኛ አርቶዶክሳዊያን ደግሞ የለበሰው ሥጋ ራሱ አከበረው እንጂ በኀደረተ መንፈስ ቅዱስ የከበረ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ አነጻ፣ ከፈለ፣ አዋሐደ እንላለን። መጽሐፍ ለሦስቱ ይሰጣል አብ አከበረ፣ ወልድ አከበረ፣ መንፈስ ቅዱስ አከበረ፣ ይላል። አብ አስነሣው፣ ወልድ አስነሣው፣ መንፈስ ቅዱስ አስነሣው ይላል። ሥልጣናቸው አንድ ለመሆኑ ለማጠየቅ ነው።

እኛ «ወሶበ ተዋሐደ ኀጺን ምስለ እሳት ያመውቆ ለቈሪር ፍጥረቱ በእፎ እንከ ኢያብዕል ቃል ሥጋ ዚአሁ» ኀጺን ከእሳት ጋር በተዋሐደ ጊዜ ቈርር ፍጥረቱን የሚያሞቀው ከሆነ ቃል የራሱን ሥጋ እንዴት ገንዘብ አያደርገውም? ይህ ለወልድ ሲሰጥ ነው።

ለመንፈስ ቅዱስ ሲሰጥ «ወገባሪሁ ለውእቱ ሥጋ መንፈስ ቅዱስ እስመ ውእቱ ቀብዖ ወተዋሐደ ቦቱ» ያንን ሥጋ የሠራው (የፈጠረው) መንፈስ ቅዱስ ነው ይላል። ለአብ ሲሰጥ «በእንተዝ ቀብዓከ እግዚአብሔር አምላክከ» ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ አከበረህ» (መዝ.፵፬ ቁ.፯) ስለዚህ ፈጣሪህ ፍጡር ነፍስን ፍጡር ሥጋን ስለተዋሐድከ አከበረህ ማለት ነው። ይኸ ሁሉ የሚነገረው ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጡር ሥጋን ስለተዋሐደ ነው።

በአጠቃላይ በቅብዐተ መንፈስ ቅዱስ ከበረ ማለት ስሕተት ነው። ቀብዐ ብሎ ተዋሐደ አያሰኝም «ቅብዕ ብሂል ክብር ብሂል» ቅብዓት ማለት ክብር ማለት ነው።

«ለሊሁ ቀባዒ ወለሊሁ ተቀባዒ» እንደ አምላክነቱ ሥጋን ከአብ ጋር ያከብራል፤ እንደ ሰውነቱ ደግሞ ከበረ ይባላል። ✦




«ወአንሰ ሐሰ ሊተ ኢይዜኃር ዘእንበለ በመስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእነ።»

# መስቀልን የምናከብረው ስላከበረን ነው


ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ
የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምርያ ዋና ኃላፊ


እኔስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል እንጂ በሌላ አልመካም። (በሌላ የምመካ ከሆንስ ሐሰት ነው። (ገላ.፮፥፲፬)

መስከረም በጠባ ጊዜ የመስቀልን ነገር ስናወሳ፣ መስከረም ፲፯ እና ፲፰ ቀን የምናከብረው በዓለ መስቀል አስቀድሞ ይታወሰናል። ይሁን እንጂ አበው ነገር ከሥሩ ውኃ ከጥሩ እን ዲሉ፣ ነገረ መስቀልን ከሥር ከመሠረቱ ማየቱ የበለጠ ጠቃሚ ይሆናልና ነገረ መስቀልን ከሥሩ ለመቃኘት፣ በተለይም ወጣቱ ትውልድ ስለ መስ ቀል መጠነኛ ግንዛቤ መጨበጥ ይችል ዘንድ፣

፩ኛ. መስቀል በሥርዓተ ኦሪት፣

፪ኛ. መስቀል ከቀራንዮ በኋላ

፫ኛ. ቅድስት እሌኒና መስቀለ ክርስቶስ የሚሉ ርዕሶችን ባጭር ባጭሩ እንመለከታለን።

## ፩ኛ. መስቀል በሥርዓተ ኦሪት

መስቀልን በኦሪት መነፅር ስንመለ ከተው፣ አበሳ፣ ጌጋይ፣ ኵነኔ መር ገም፣ ስቅላትና ሞት በሚሉ አስፈሪና አስደንጋጭ የአደጋ ምልክቶች ተከቦ እናየዋለን።

ኦሪት «እስመ ርጉም ውእቱ በኃበ እግዚአብሔር ዘስቁል ዲበ ዕፀ፤»

በዕንጨት የተሰቀለ ሰው በእግዚ አብሔር ዘንድ የተረገመ ነው ማለ ትዋ፣ የመስቀልን አስፈሪነት ለማስገ ንዘብ በመሆኑ፣ ኦሪት በመስቀል ላይ፣ ለምሕረትና ለይቅርታ የሚያበቃ አመለካከት ፈጽሞ እንዳልነበራት ያመለክታል። ኦሪት «ርጉም» ያለች ውን ለማየት ስንሞክርም፣ ሞት የተገባው በደለኛ፣ ዓመፀኛ፣ ወንጀ ለኛ፣ ጥፋተኛ፣ ነውረኛ በሚሉና በተመሳሳይ አሳፋሪ ቃላት የሚገለጽ ሆኖ እናገኘዋለን። በዚህ ሚዛን ላይ የተገኘ በደለኛ ሰው ዕድል ፈንታው ሞት ብቻ ሳይሆን የሞት ሞት ነበር። ያውም መስቀል።

ኦሪት ርጉም ያለችውን የሚቀጣ ባቸው የመስቀል ዓይነቶች ልዩ ልዩ ቅርፅ ያላቸው ብዙ እንደሆኑ የሚገ መት ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ የሚታወቁት ግን ሦስት ናቸው አራተ ኛው ደግሞ ዛፍ ነው። እነዚህ ሦስት

የመስቀል ዓይነቶችም ፩ኛ.✞ ፪ኛ.T ፫ኛ.X የመሰለ ቅርፅ እንደ ነበራቸው ተጽፎአል።

በሦስተኛው ተራ ቁጥር የተገለ ፀው የመስቀል ቅርፅ፣ መስቀል ቅዱስ እንድርያስ በመባል የሚታወቅ ሆኖ በ፪ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰው የመስ ቀል ቅርፅ ደግሞ የላቲን መስቀል በመባል ይታወቃል። በዚህ መሠረት መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል የላቲኑ መስቀል መሆኑን በብዙ አርቲስቶች የተደገፈ ጥናታዊ አባባል ነው። ፬ኛው የመስቀል ዓይነት ግን ማንኛውም ለአፈፃፀም ምቹ የሆነ ዛፍ እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፏል። (አስ.፪፥፳፩–፳፫)።

በመስቀል እንዲሞት የተፈረ ደበት ሰው፣ እጅ እግሩን በማሰር ወይም አሰቃቂና አስፈሪ በሆነ ችንካር በመቸንከር፣ እኔን ያየህ ተቀጣ ለማሰኘት በሚፈጸም አስፈሪ የቅጣት ዓይነት ይቀጣ ነበር። በዚህ መሠረት ታላቁ እስክንድር ከአንድ ሺሕ በላይ ብዛት ያላቸው ሰዎችን በስቅላት እንዲቀጣና አይሁድ በባቢሎን በባርነት በነበሩበት ዘመንም በስቅላት ይቀጡ እንደ ነበር ዮሲፎስ የተባለ ዕውቅ የታሪክ ጸሐፊ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮ ጽፏል።

የፋርስ ንጉሥ ዳርዮስም፣ ትእዛ ዙን የሚተላለፍን ሰው በስቅላት ሲቀጣ መኖሩን ለማስገንዘብ፣... «ይህንም ትእዛዝ የሚለውጥ ሁሉ ምሰሶው ከቤቱ ተነቅሎ እርሱ ይሰቀ ልበታል። ቤቱም የጉድፍ መጣያ ይደረግ፣ ብዬ አዝዣለሁ።» በማለት ያስተላለፈው አዋጅ በመጽሐፈ ዕዝራ ተጽፎ እናገኛለን። ዕዝ.፮፥፲፩።

መስቀል፣ ወዲያውኑ እየተሠራ በደለኛው እንዲሰቀልበት ከማድረግ ይልቅ፣ በአብዛኛው ጊዜ ተዘጋጅቶ ይቀመጥ እንደ ነበር መገመት የሚያስችል ጽሑፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎአል፤ ለምሳሌ ጨካኙና ተንኮ ለኛው ሐማ የተሰቀለበት መስቀል፣ ራሱ ለመርዶክዮስ መሰቀያ ይሆናል ብሎ አዘጋጅቶ ባስቀመጠው ግንድ እንደ ነበር እንገነዘባለንና ነው። አስ.፯፥፩–፲።

እዚህ ላይ ግን ባለ ኦሪቱ ዕብራዊና ባለ ጣዖቱ አረማዊ መስቀልን ሕግ እኩል ተግባራዊ ሲያደርጉ ስንመ ለከት፣ የመስቀልን ታሪካዊ መነሻና ምንጭ ኦሪት ነበረች ከማለት ይልቅ፣ በአሕዛብ ዘንድም ቀደም ብሎ የተለመደ ማኅበራዊ ሥርዓት ወይም ፖለቲካዊ ሕግ ሆኖ ሲሠራበት የኖረ ነበር፤ ማለቱ የቀለለ ሆኖ እናየዋለን።

www.ethiopianorthodox.org


በሌላ በኩል ደግሞ፡ አይሁዳዊም ሆነ አረማዊ ለሞት የሚያበቃውን በደል ፈጽሞ ሲገኝ በመስቀል የመቀጣቱ ነገር አግራሞ ያልነበረው ጉዳይ ሆኖ እያለ፡ ሮማዊው ዜጋ ግን ምንም ዓይነት ወንጀል ቢፈጽም ስንኳ፡ በመስቀል እንዳይቀጣ ሮማዊቷ ሕግ ነፃ አውጥታዋለችና በመስቀል አይቀጣም። በሮማ ግዛት፡ በስቅላት እንዲቀጣ የሚፈረድበት ሰው፡ ሮማዊ ዜግነት የሌለው በሮማ የግዛት ክልል ሮማዊውን ክበርቴ እያገለገለ በባርነት የሚኖር ኢሮማዊ ዜጋ ብቻ ነበር።

እንግዲህ ኦሪት «በዕንጨት የተሰቀለ ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነው» ብላ ነበርና መስቀል፡ እስከ ሞተ ክርስቶስ ድረስ የመርገም፡ የበደል፡ የኑውርና የርኩሰት ምልክት፡ ሟቹ የሚረከስበት፡ የሟቹ ወገንም የሚያፍርበት ነበር ማለት ነው።

## ፪ኛ. መስቀል ከቀራንዮ በኋላ

ብዙ ሰዎች መስቀልን የማክበራችን ምሥጢር ማወቁ ይሳናቸዋል፡ ይከብዳቸዋል፡ ይጸንባቸዋል። እኛ ግን መስቀልን የምናከብረው ስላከበረን ነው። ክብር ምስጋና ይግባውና አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ መስቀልን ታግሶ፡ በደሙ ክሶ፡ በቀራንዮ ጭሎ፡ ዓለምን ከቀደሰልን በኋላ፡ መስቀል የርግማን፡ የኃፍረትና የኃጢአት ምልክት መሆኑ ቀርቶ መስቀል መርገመ ኦሪት የተሻረበት፡ ሰላምና ኍፃነት የታወጀበት፡ የኛ የድኅነት፡ የበረከትና የነፃነት አርማ፡ የወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ የሰላም ዙፋን ሆኖ ዓመተ ፍዳና ዓመተ ኩነኔን ተሽሮ ዓመተ ምሕረት የታወጀበት የነፃነት ዋስትናችን ነው። ለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ

«ወለነሰ ተሣየጠነ ክርስቶስ እመርገማ ለኦሪት በዘመድአ በእንቲአነ ወፆረ መርገማ፡ እኛንስ ክርስቶስ ከኦሪት መርገም ዋጅቶናል። ስለኛ ሕግን በመፈጸሙና የኦሪትን መርገም በመሸከሙ።» ብሏል ገላ.፫፥፲፫።



በነቢዩ፡

«ውእቱ ነስአ ደዌነ ወፆረ ሕማመነ፤ በእንቲአነ ሓመ፤ ወንሕነሂ ርኢናሁ ሕሙመ ወቅሡፈ በሕማም። ወውእቱሰ ቈስለ በእንተ ኃጢአትነ ወሐመ በእንተ ጌጋይነ፤ ትእምርተ ሰላምነ፤ ወበቍስለ ዚአሁ ሐየውነ ቍኢስለነ።»

እሱ ደዌያችንን ገንዘብ አደረገ፡ ሕማማችንም ተሸከመ፡ ስለ እኛም ታመመ፤ እኛም ታሞ በመከራም ተጨንቆ አየነው። እሱ ግን ስለ ኃጢአታችን ቈሰለ፤ ስለ በደላችንም ታመመ፤ የፍቅር፡ የአንድነታችንም (የሰላማችንም) ምልክት እሱ ነው። በእሱ ቍስልም ከቁስላችን ዳንን...። ተብሎ ተጽፎ ነበርና ትንቢት እንዲፈዙም፡ ኦሪታዊ መርገመ መስቀል እንዲያከትም፡ አምላክ ወልደ አም ላክ ደዌያችንን ተሸክሞ በቀራንዮ ዋለልን። ኢሳ.፶፫፥፬–፭፤ ዮሐ.፲፱፥፩–፴፪። ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ም.፰፥፫ ላይ፡

«ወኰነና ለይእቲ ኃጢአት በነፍስቱ፡ ኃጢአትን በሰውነቱ ቀጣት።»

ያለውን እንደነ ቅዱስ አትናቴዎስ የመሰሉ አበው ሊቃውንት ደግሞ፡

«ወአስተሐፈረ ኃጢአተ በዲበ ምድር፤ ወአብጠለ ሞተ በውስተ ሲኦል ወሰዐረ መርገመ በዲበ ዕፀ መስቀል፤ ወነሰተ ሙስና በውስተ መቃብር። ወዘኢየሐምም ሐመ በሥጋ ሐማሚ ተዋሒዶ ቃል ምስለ ሥጋ ወገብረ ዘንተ ከመይፁር ሕማመ ዚአነ ወያእትቶ እምኔነ ወየሀበነ ዘዚአሁ ሕይወተ፤ ወአዕረገ ርእሶ መሥዋዕተ በእንቲአነ»።

በምድር ላይ ኃጢአትን አሳፈረ፤ በሲኦልም ሞትን አጠፋ፤ በመስቀል ላይ መርገምን ሻረ፤ በመቃብር ውስጥም ሙስና መቃብርን አጠፋ። የማይታመመው በሚታመመው ሥጋ ታመመ፤ ቃል ከሐማሚ ሥጋ ጋር ተዋሕዶ ሕማምን ከሥጋ ያርቅ ዘንድ፡ ከእኛም ያርቀው ዘንድ፡ የርሱንም ሕይወት ይሰጠን ዘንድ ይህን አደረገ። ስለኛም ራሱን መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ። በማለት ይገልጹታል። ሃይ አበ ዘቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርየዊ ፴፥፵።

ንጹሐ ባሕርይ ክርስቶስ፡ ከሥራው ስሕተት ከአንደበቱ ሐሰት ሳይገኝበት፡ በኃጢአተኞች ዘንድ፡ ኃጥእ፡ በደለኛ ተብሎ መስቀል ላይ ዋለ መባሉ እውነት ነው። ሆኖም ክርስቶስ መስቀል ላይ የዋለበት አንድ ዐቢይ ምክንያት እንዳለ ግን መዘንጋት የለበትም። ይኸውም ዕዳ በደላችንን ደዌ ኃጢአታችንን ተሸክሞ በደሙ ካሣ መርገማችንን ሽሮ ከኃጢአት ባርነት ነፃ ያወጣን ዘንድ መሆኑን ነው። ስለዚህም፤



«እስመ ዘኢየአምር ኃጢአተ ረሰየ ርእሶ ኀጥአ ከመ ኪያነ ያጽድቀነ»

ለእግዚአብሔር። ኃጢአት የሌለበት ንጹሐ ባሕርይ ክርስቶስ እሱ እኛን የእግዚአብሔር ማደሪያ ለመኾን ያበቃንና ያከብረን ዘንድ፣ ራሱን እንደ በደለኛ አድርጎ በመስቀል ላይ ዋለ።» ተብሎ ተጽፎአል (፪ኛቆሮ. ፭፥፳፩)።

መስቀል ብርሃናችንና የቤተ ክርስቲያናችን መሠረት ነው። ለዚሁም ታላቁ አባት ቅዱስ ያሬድ፡ «መስቀል ብርሃን ለኵሉ ዓለም መሠረተ ቤተ ክርስቲያን።» በማለት፣ መስቀል በጨለማ ግርዶሽ ይኖር ለነበረ ዓለም ሁሉ ብርሃን፡ ለቤተክርስቲያንም መሠረት መሆኑን አስትምሮናል።

የሰው ልጅ በ፭ ሺህ ፭ መቶ የታሪክ ዘመኑ፡ ሞት በላዩ ላይ ሰልጥኖበት፡ የዲያብሎስ የባርነት ቀንበር ተጭኖት፡ ለችግሩ መፍትሔ፣ ለሕመሙ መድኃኒት አጥቶ ዘመነ ፍዳውን በመቍጠር ሲባዝን ከኖረ በኋላ የእግዚአብሔር የይቅርታና የምሕረት ቀን (ዕለተ አድኅኖ) በደረሰ ጊዜ ግን ሰላሙንና ነፃነቱን ያገኘው በመስቀል ነው።

በዚህ መሠረት መስቀል ነፃነታችን ነውና እናከብረዋለን። «እስመ ክርስቶስኒ ምዕረ ሞተ በእንተ ኃጣውአ ሰብእ። ክርስቶስኮ ስለሰው ኀጢአት አንድ ጊዜ ሞቶአል፤ ኃጢአት የሌለበት ክርስቶስ ስለኛ ሞተ፤ ...ነፍሳቸው ታስራ ወደ ነበረችበት ኼዶ ነፃነትን ሰበከላቸው።» እንዳለ መጽሐፍ (፩ኛጴጥ. ፫፥፲፰–፲፱፤ ም.፪፥፳፬)። አዎ! እኛ መክፈል የማንችለው ካሣ ተከፍሎልን ዕርቅ ያገኘነው በመስቀል ነው። «ወገብረ ሰላመ በደመ መስቀሉ ለዘበሰማይ ወለዘ በምድር፤» ተሰቅሎ ባፈሰሰው ደሙ በሰማይ ያሉ መላእክትንና በምድር ያለን እኛን አስታርቆ ሰላሙን ሰጠን እንዲል። (ቈላ.፪፥፳)።

መስቀል ሰላማችንና ነፃነታችን ብቻ ሳይሆን ክብራችንና ቅድስናችንም ነው፤ በመስቀሉ ተቀድሰናል፤ በመስቀሉ ከብረናል።

«ወበእንተዝ ኢየሱስኒ ከመ ይቀድሶሙ ለሕዝብ በደመ መስቀሉ በአፍአ እምትዕይንት ተቀትለ።»

ሕዝቡን በደመ መስቀሉ ያከብራቸው፡ ይቀድሳቸው ዘንድ ከከተማ በአፍአ (በውጭ) ተሰቀለ። እንዲሁም ከሆነ እሱ የተቀበለውን መከራ መስቀል እየተቀበልን ከዚህ ዓለም ልዩ ሆነን፤ እሱ ወዳለበት እንገሥግሥ።» ዕብ.፲፫፥፲፪–፲፫። ካለ መስቀሉ ሰላም፡ ካለ መስቀሉ እርቅና አንድነት፣ ካለ መስቀል ፍቅርና ሰላም አልተገኘምና፡ መስቀል ክብራችን ነው የምንለው ለዚህ ነው። አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ በሥጋው ክሶ ኃጢአትን ደምስሶ ዲያብሎስን ድል ነስቶ የቸርነት ሥራውን በመሥራት የሰውን በደል ይቅር ብሎ ሰውን ከአምላክነቱ ያስታረቀ፣ ሰማያውያንና ምድራውያንን አንድ ያደረገ አስታራቂያችን እሱ ነው።

«እስመ ውእቱ ሰላምነ ዘረሰዮሙ እሐደ ለክልኤሆሙ።» (ኤፌ.፪፥፲፫–፲፯፤ ቈላ.፩፥፳)።

መስቀል ተስፋችንና ምርኩዛችን መሆኑንም ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ እንዲህ በማለት ይገልፃል።

«ተስፋየ እምንእስየ ምርጉዝ ለርስዐንየ ዝንቱ ውእቱ መስቀል።»

ከሕፃንነቴ (ከታናሽነቴ) ጀምሮ ተስፋዩና አለኝታዩ፣ በሽምግልናዩ ወይም በድካሜ ጊዜም ምርኩዜ ይኸው መስቀል ነው። ዋዜማ ዘመጋቢት መስቀል።

ለሰው ልጅ ክብርና መመኪያ ከመስቀል የበለጠ ሌላ ነገር አለመገኘቱን በግልጽ የተረዳ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም

«ወአንሰ ሐሰ ሊተ ይዜኃር ዘእንበለ በመስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእነ።»

እኔስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል እንጂ በሌላ አልመካም፤ ሌላ መመኪያ አለኝ ብል ሐሰት ነው። በማለት ክብረ መስቀልን በሚገባ ያስገነዝባል። (ገላ.፮፥፲፬)።

የመስቀሉ ነገር ሰላም፡ ነፃነት፡ ዕርቅና ድሕነት ሆኖ እያለ ግን አንዳንድ ሰዎች የመስቀሉ ጠላቶች ሆነው መታየታቸው አስገራሚ ነገር ነው። በእርግጥ የመስቀሉ ምሥጢር አይታያቸውምና ስንፍና ይመስላቸው ይሆናል፤ ያላዋቂ ትችትም ለመሰንዘር ይሞክራሉ፤ እኛ ትርጉሙን ሳናውቅ መስቀልን እንደምናከብረው መስሎ ይታያቸዋል፤ ይህ የተሳሳተ ግምታቸውና አመለካከታቸውም መስቀሉን እንዲጠሉ ያደርጋቸዋል።

ለዚሁም የመስቀሉ መሠረታዊ ጠላት የሆነ ዲያብሎስ መስቀሉን እንዲጠሉ ያደርጋቸው ዘንድ ግዴታ ስለሆነ ነው። ዳሩ ግን በፊልጵስዩስ ም.፫፥፲፰–፲፱፤ «ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶቹ ሆነው ይመላለሳሉና፤ ብዙ ጊዜ ስለ እነርሱ እላችኋለሁ፤ አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላለሁ። መጨረሻቸው ጥፋት ነው። ሆዳቸው አምላካቸው ነው፤ ክብራቸው በነውራቸው ነው፤ አሳባቸው ምድራዊ ነው።» ተብሎ ተጽፎአልና ጥላቻው የማይቀር ቢሆንም መስቀሉን መግፋት ግን ውጤቱ ምን እንደሚሆን ማስተዋሉ ጠቃሚ ይሆናል።

መስቀሉ ኃይላችን፡ መድኃኒታችን፤ ክብራችን፤ ጸጋችንና በረከታችን ነውና መስቀሉን እናከብረዋለን፤ በመስቀሉ ኃይለ አጋንንትን፡ ፀብአ አጋንንትን ድል እንነሣበታለን፡ መስቀሉን ስንሰብክ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ መስቀሉን ስናከብር የተሰቀለውን ክርስቶስ እናከብራለን።

«እስመ ነገረ መስቀሉሰ ዕበድ ውእቱ በኀበ ሕጉላን፤ ወበኀቤነሰ ለእለ ድኅነ ኃይለ እግዚአብሔር ውእቱ»።

የመስቀሉ ነገርስ በጥፋተኞች ዘንድ ስንፍና ነው፤ ለኛ ለዳንነው ግን፡ የእግዚአብሔር ኃይል ነው።... መቼም አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ፥ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ፤ «ወንሕነሰ ንሰብክ ክርስቶስሃ ዘተሰቀለ» እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን።» (፩ኛቆሮ.፩፥፲፰–፳፬)።

## ፫ኛ. ቅድስት እሌኒና መስቀለ ክርስቶስ

መስከረም ፲፯ ቀን ወይም በዋዜማው፤ በዓለ መስቀልን ስናከብር ከመስቀሉ ቀጥለን የምናስባት ቅድስት እሌኒ ናት። ቅድስት እሌኒ የመስቀሉ ጥበብ ተገልጾላት ክብሩና ሞገሱ በግልጽ ታይቶአት፣ መድኃኒቱ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን ቅዱስ መስቀል የት ባገኘሁት እያለች ለብዙ ጊዜ ታስብና ትመኝ ነበር። በተለይም ልጇ መምለኬ እግዚአብሔር ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ፡ መክስምያኖስ ከሚባል ጠላቱ ጋር ሲዋጋ፤

«በዝንቱ ትእምርተ መስቀል ትመውእ ፀረከ።»



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ የመስቀል ምልክት ጠላት ህን ድል ትነሳለህ» በሚል ራእይ የእግዚ አብሔር መልአክ የመስቀሉን ቅርፅ በብርሃን ሰሌዳ ስላሳየው፤ ራእዩ የእግዚአብሔር ኃይል መሆኑን በመገ ንዘብ፣ በሰንደቅ ዓላማው፣ በጋሻው፣ በጦሩ፣ በፈረሶቹ ሽልማትና በሠራ ዊቱ ትጥቅ ሁሉ መስቀልን አርማው በማድረግ በጠላቱ ላይ በዘመተ ጊዜ፣ ቃሉን የማያጥፍ እግዚአብሔርም ኃይለ መዊዕ ስለሰጠው ጠላቱን ድል ነሥቶ መንግሥቱን አደላድሎ ለክር ስቲያኖችም የነፃነት አዋጅ አውጆ በሰላም እንዲኖሩ ማድረጉን ካየች በኋላ፣ ለመስቀለ ክርስቶስ የነበራት ክብርና ፍቅር በእጅጉ እየመጠቀ ሊኼድ ችሏል።

መስቀለ ክርስቶስ፣ በአይሁድ ክፋትና ምቀኝነት ምክንያት መቃብር ተፈርዶበት ማንም አይሁዳዊ የቤቱን ጥራጊ መስቀሉ በተቀበረበት እንዲ ደፋ ሕግ ሆኖ ከሁለት መቶ ዓመታት በላይ ሲሠራበት የኖረ በመሆኑ፣ ቅዱስ መስቀሉ በተቀበረበት ቦታ ላይ የተሰበሰበው የቤት ጥራጊ ተራራ አክሎ የተፈጥሮ ጋራ እንጂ የመስቀል መቃብር ይሆናል ብሎ መገመት እስከ ማይቻል ድረስ ደርሶ ነበር። ቅድስት እሌኒ ግን መስቀሉን ከአይ ሁድ በቀር ሌላ ሊያጠፋው የሚያስብ እንደ ማይኖር ተረድታለችና አረጋ ውያን አይሁድን አጥብቃ መመር መርን መረጠች። በዚህ መሠረት ከተጠየቁ አረጋውያን አይሁድ መካከል አንድ አረጋዊ፣ ስሙ ኪራኮስ የሚባል አረጋዊ፣ ከአያት ቅድመ አያቱ የሰማ ውን ምሥጢር ነገራት፤ የመስቀሉ መቃ ብር ከተራሮቹ አንዱ መሆኑን አሳወቃት።

«አረጋዊ አንግሐ ገይሥ ብእሲ ዘስሙ ኪራኮስ ዘዕጣን አንፀረ ሰገደ ጢስ በኅልኅታ ዘደፈኑ አይሁድ ዮም ተረከበ ዕፀ መስቀል»።

ስሙ ኪራኮስ የሚባል ሽማግሌ ሰው መስቀሉ የሚገኝበትን ምሥጢር ለንግሥት እሌኒ ይነግራት ዘንድ ማልዶ ገሠገሠ፤ ዕጣንም፣ መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ በማመልከት ጢሱ ሰገደ። አይሁድ በኅልኅታ የቀበሩት ዕፀ መስቀልም ዛሬ ተገኘ። (እንዳለ ቅዱስ ያሬድ)

ቅድስት እሌኒ ዕጣን አጢሳ ፈጣሪዋን በጸሎት ብትለምን ምልክት እንደምታገኝ ተገልጾላታልና አበውን ሰብስባ ዕጣኑ ጢስ ጸሎቱ ተጀመረ፤ በዚህ ጊዜ የዕጣኑ ጢስ ሰማይ ደርሶ ለመስቀሉ በመስገድ መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ በትክክል አመለከተ።

ከዚህ በኋላ ቅድስት እሌኒ ፈቃደ እግዚአብሔር መሆኑን በመገንዘብ ተራራውን የማስቆፈር ሥራዋን ቀጠ ለችበት። ነገር ግን ተራራው ሲቆ ፈር፣ ከፊሉ ሥራውን የምኝነት ሥራ ሲለው፣ ሌላው ደግሞ ተስፋ በማስ ቆረጥ ሥራውን ለማሰናከል በሥራው ላይም ዕንቅፋት መፍጠሩን ተያያዘው። ቅድስት እሌኒ ግን ከእግዚአብሔር የማረጋገጫ ምልክት አግኝታለችና ጥረቷን በእምነት ቀጠለች። መስከረም ፲፯ ቀን ፫፻፳፯ ዓ.ም የተጀ መረው ቁፋሮ ከ፯ወር ብርቱ ጥረት በኋላ መጋቢት ፲ ቀን ፫፻፳፯ ዓ.ም መስቀሉ በእግዚ አብሔር ፈቃድ ተገኘ።

በቁፋሮ የተገኙ መስቀሎችም ሦስት ነበሩ፤ እነዚህም አንዱ የጌታ መስቀል ሲሆን ሁለቱም የሁለቱ ሽፍቶች መስቀሎች ናቸው። በዚህ ጊዜ የጌታችንን መስቀል ለይቶ ለማወቅ ችግር ሆኖ ነበር፤ ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር የታመነ ልብ፣ ምንም ቢቸገር የችግሩ መፍትሔ ከእግዚአብሔር መሆኑን ያውቃልና በቅድስት እሌኒ አእምሮ አንድ ሐሳብ ተቀረፀ። ይኸውም መስቀለ ክርስቶስ ኃይሉን የሚያሳይበትና ራሱን የሚገ ልጽበት ሁኔታ እንዳለ የሚያስገነዝብ ሐሳብ ነበር። በዚህ ሐሳብ መሠረት መስቀሎቹ ምልክት እንዲያሳዩ ሙከራ በሚደረግበት ጊዜ የሁለቱም ሽፍቶች መስቀሎች ምንም ዓይነት ምልክት ያላሳዩ ሲሆን በጌታችን በኢ የሱስ ክርስቶስ መስቀል ግን ምውታን ተነስተዋል፤ ዕውራን አይተዋል፣ ሽባ ዎች ተነስተው ሮጠዋል፣ በአጠቃላይ በመስቀለ ክርስቶስ ልዩ ልዩ ተአም ራት ታይቷል። ብዙ በረከትም ተገኝቷል።

ቅድስት እሌኒም ይህን ክብር ያደ ላትን ፈጣሪዋን በማመስገን፣ መስቀለ ክርስቶስን በወርቅና በዕንቊ አስጊጣ በኢየሩሳሌም በክብር እንዲቀመጥ አደረገች። መስቀሉ ተቀብሮበት በነበረ ቦታ ላይም «ትንሣኤ ክርስ ቶስ» ተብሎ የተሠየመ ትልቅ ቤተክ ርስቲያን አሠራች።

ከጊዜ በኋላ ግን መስቀሉ ወደ ፋርስ በምርኮ ተወስዶ ከቆየ በኋላ፣ እንደገና ወደ ኢየሩሳሌም ተመል ሷል። አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ የተባሉ አባት መጽሔተ አሚን በሚል ጽሑፋቸው እንዲህ ይላሉ «እሌኒ ንግሥት ከመቃብር ያወጣችው መስቀለ ክርስቶስ በወርቅና ዕንቊ ሽልማና አጊጣ በኢየሩሳሌም አስቀ ምጣው ሲኖር፣ ኮስሮኤል የሚባል የፋርስ ንጉሥ ፳፪ ሺህ ክርስቲያኖችን አስገድሎ ከ፫ ሺህ በላይ የሆኑትን ማርኮ ኢየሩሳሌምን በማቃጠል መስ ቀለ ክርስቶስን ከብዙ ንዋየ ቅድሳት ጋር ዘርፎ ወስዶት ነበር። ነገር ግን ክርስቲያኖች በዚህ እያዘኑ ሳለ ፈቃደ እግዚአብሔር ያነሣሣው ሕርቃል የሚባል ንጉሥ በ፮፻፳፰ ዓ.ም ወደ ፋርስ ዘምቶ ኮስሮኤልን ድል አድርጎ የጌታችንን መስቀል አግኝቶ ሲመለስ መስቀሉን ራሱ ተሸክሞ ከፋርስ እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ አለሜማ በእግሩ በመጓዝ መስቀሉን አምጥቶ ለኢየሩ ሳሌም ምእመናን በክብር አስረከበ። ሕርቃል መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ በደረሰ ጊዜም የከተማው ሕዝብ ሁሉ ከደስታው ብዛት የተነሳ መብራት፣ ችቦና ጡዋፍ እያበራ ንጉሡንና መስቀሉን በዕል ልታ ተቀበለ ይባላል። በኢየሩሳሌም ያሉ ምእመናን ክርስቲያን ሁሉ መስቀሉ ከምርኮ ሲመለስ በዕልልታና በደስታ፣ አበባ እየያዙ በመብራት እንደተቀበሉት ሁሉ በሀገራችን በኢትዮጵያም መስከረም ፲፮ ቀንና ፲፯ ቀን መብራት እያበራን አበባ ይዘን በዕልልታና በሆታ በየዓመቱ በዓሉን እናከብራለን። ይህም በ፮፻፳፱ ዓ.ም ምሕረት የተዠመረው በዓል፣ በኢትዮጵያ እስከ ዛሬ ድረስ ጸንቶ ይኖራል።» በማለት ጽፏል። መጽሔተ አሚን ገጽ ፵፭ እና ፵፮

በእርግጥም እኛ ኢትዮጵያውያን ዓለምን በሚያስደንቅ ሥነ ሥርዓት፣ ደመራ ደምረን ችቦ አብርተን ካህናት በዝማሬ (በጸሎት) ምእመናን በሆታና በዕልልታ፣ በዓለ መስቀልን በየዓመቱ እናከብራለን። በተለይም ወጣት የሰንበት ት/ቤቶች ልጆቻችን ለበዓሉ አከባበር ድምቀት፣ ልዩ ፈርጥና ጌጥ በመሆን ከፍተኛ ድምቀትን ይሰጡታል።

ከዚህም ሌላ አስደናቂው ነገር በዓሉን ማክበራችን ብቻ ሳይሆን መስቀል የክብርና የነፃነት አርማችን መሆኑን አምነን፣ የክብር ጌጣችን በማድረግ በንቅሳት ወይም በመበ ጣት፣ በግንባራችን እናሳየዋለን፤ በተለይ በአንገታችን እንሸከመዋለን፤ በተለይ ሴቶች በልብሳቸው ያስጠልፉታል፣ በየቁሳቁሱ ላይ ይስሉታል። ከእነዚህ ምልክቶች ሁሉ ቢያንስ አንዱ ስንኳ የሌለው ክርስቲያን በማንነቱ ያፍራል እንጂ ክርስቲያን የሆነ መስሎ አይታ የውም፣ ለክርስቲያን ሁሉ ከመስቀል የተለየ ሕይወት የለውምና መስቀልን ይመካበታል።

ስለዚህ መስቀል ዓለም የተቀደ ሰበት፣ ሰይጣን ያፈረበት ኃይላችን ክብራችንና ሕይወታችን ስለሆነ እንከ ራበታለን። በአጠቃላይ መስቀልን የምናከብረው ስላከበረን ነው። ✣



# እኔም ወጣት ነበርኩ

## የ፺፩ ዓመት የእድሜ ባለጸጋ

የብዕር ቅኝት በመምህር ዕንቁባሕርይ ተከሥተ

ዛሬ ብፁዕ አቡነ አብርሃም የ፺፩ ዓመት የእድሜ ባለጸጋ ናቸው። አቡነ አብርሃም ቤተክርስቲያንን ለ፹፬ ዓመታት ያገለገሉ ናቸው። በተለይ ብዙዎች ብፁዕ አቡነ አብርሃምን የሚያውቋቸው ድምፀ እንዚራ በሆነ እጅግ ማራኪና ተደናቂ በማይለወጥ ድምፀ ላኅያቸው ነው።

በቃ የድምፃቸው ላኅይ አቡነ አብርሃም ለአቋቋም፣ አቋቋም ለአቡነ አብርሃም እንደተፈጠረ ያስመስላቸዋል።

በዛሬ የወጣቱ አምድ ላይ ያቀረብንላችሁ እኚሁ ስመ ጥር የሆኑት ሊቅ ናቸው። በእርግጥ ብፁዕ አቡነ አብርሃም በአሁኑ ጊዜ እርጅና ይዟቸዋል። ድሮ እንደ ልብ ይንቀሳቀስ የነበረ እጅና እግር ዛሬ እጁን ለእርጅና ሰጥተዋል።

እነዚያ መጻሕፍትን ድጓን ከእነ ምልክቱ ያነቡ የነበሩ ዓይኖች ዛሬ ፈዘዋል። በሩቅ እንደ ልብ ማየት አልቻሉም። እንደዚህም ሆኖ ለማነጋገር በሄድኩበት ጊዜ በላያቸው ላይ ግርማ ሞገስ ያለው ካባ ደረብ አድርገው አባታዊ አቀባበል በማድረግ የሕይወት ተሞክሯቸውን በአንደበታቸው በሰፊው አካፍለውናል። ለወጣቱም የሚሉት አለ፣ ለሁሉም ነገር መልካም ንባብ ለአንባቢዎች።



ፈለገ ጥበብ – ብፁዕ አባታችን እንደ ሚታወቀው በቤተ ክርስቲያናችን ለብዙ ዓመታት ከተራ አገልጋይነት እስከ ሊቀ ጳጳስነት ደርሰዋል። በሊ ቅነት በኵልም በቤተ ክርስቲያናችን በሰፊው ይታወቃሉ ለዚህ መነሻ የሚ ሆነው ከሕፃንነትዎ እስከ ቤተ ጉባኤ ያለው ታሪክ ቢገልጹልን?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም – የተወለድኩት እንድማጣ ኢየሱስ ይባላል አባቴ ብላታ ምሕረቱ ትርፌ እናቴም ወ/ሮ በለጡ ፀዳል ይባላሉ። በደብረ ማርቆስ ከተማ ክልል ውስጥ ነው ከፊደል ጀምሮ እስከ ድጓ ድረስ የተማርኩት ከትውልድ መንደሬ ሳልወጣ ነው።

ፈለገ ጥበብ – ወደ ኋላ ልመልስዎትና በስንት ዓመተ ምህረት ነው የተማሩት?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም – ወላጆቼ ገበሬዎች ስለነበሩ ዓመተ ምሕረቱን አያውቁትም ይሁንና በ፲፱፻፲፪ ዓ.ም እንደሆነ ይገመታል።

ፈለገ ጥበብ – ማን ከተባሉ መምህር ነው የተማሩት?

ብፁዕ አቡነ አብርሃመ መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ከተባሉት ነው የተማርኩት ድንግል ናቸው። ኋላም ደብረ ፀሐይ ማርቆስ ገብቼ ርዕሰ ደብር ጸጋ ከሚባሉ መምህር ድጓን ሦስት ጊዜ ዘልቄዋለሁ። እሳቸውም ድንግል ናቸው።

ፈለገ ጥበብ – ድጓን ሲማሩ በአጫብር፣ በቆሜ፣ በቤተ ልሔም ዜማ በየትኛው ነበር የተማሩት?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም በአጫብር ነው የተማርኩት

ፈለገ ጠበብ – አቋቋምስ ከማን ነው የተማሩት?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም አቋቋም የተማርኩት ጎንደር ሄጄ ከየኔታ አካሉ መዘምር አርባዕት፣ አርያም ክብረ በዓል ተምሬአለሁ።

ፈለገ ጥበብ – አቋቋም ሲማሩ በተለይ በላይ ቤት ተጠያቂ እንደነበሩ ይነገራል። ስለዚህ የላይ ቤት አቋቋም ከየት ነው የተማሩት?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም – ላይ ቤት የተማር ኩት ከየኔታ መንገሻ ነው በደብረ ታቦር አካባቢ ማለት ነው። ኋላ ጐንደር ገብቼ የየኔታ መንገሻ ልጅ ከየኔታ አካሉ ተምሬአለሁ።

ፈለገ ጥበብ – በስንት ዓመት ነው አቋቋም የተመረቁት?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም – በሰባት ዓመት ነው የተመረቅሁት።

ፈለገ ጥበብ – ድጓ፣ ቅኔ አቋቋም ወስነው ማስተማር የጀመሩ በሰባት ዓመት ነው?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም – በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም ነው።

ፈለገ ጥበብ – ከዚህ እያይገፍ የምጠይቅዎት በመጻሕፍት ትምህርት ብዙ ጊዜ እንደ አገለገሉ ነው የሚነገረው ስለመጻሕፍት ትምህርት ቤት ሂደት ትንሽ የላይ ቤትና የታች ቤቱን ለይተው ቢገልጹልኝ?

ብፁዕ አቡነ አብርሃመ – እኚ ላይ ቤቱ በድምጫ እንጂ አልተማርኩትም





www.ethiopianorthodox.org



የተማርኩት ታቹ ቤት ነው ከየኔታ እንደ ሻው ደቀ መዝሙር ከነበሩት ከመምህር እካሉ ነው መጻሕፍቱን ያጠናቀቅኩት።

ፈለገ ጥበብ – መጽሐፍ የተማሩት ማን ከሚባለው መምህር ነው?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም – መጻሕፍት የተማ ርኩት ከመምህር ክፍለ ማርያም የዳዊት ትርጓሜ ለብቻው! ሌላው ዓቢየ እግ ዚእ ከነበሩ የኔታ ወልደ ሰንበት ነው።

ፈለገ ጥበብ – ቅኔ የተማሩት የት ነው?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም – ቅኔ የተማርኩት መሪጌታ ልሳነወርቅ ከሚባሉ ሞጣ አጠ ገብ ከሪዞ ሚካኤል ይባላል ለሁለት ዓመታት ለራሴ የሚበቃኝን ተምሬአለሁ።

ፈለገ ጥበብ – እስከ አሁን ድረስ የቆየነው ከሕፃንነት እስከ ቤተ ጉባኤ ነበር። ስለ ዚህ ይህን ከዚህ እናብቃና ብፁዕነትዎ መቼ ነው ለጵጵስና የተመረጡት?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም – በ፲፱፻፹፮ ዓ.ም ነው።

ፈለገ ጥበብ – የጵጵስና መመዘኛ የዚያን ጊዜ ምን ነበር?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም – መጻሕፍተ ትርጓሜን ያወቁ ነበር።

ፈለገ ጥበብ – የተሾሙት ወድያው ነው ወይስ ቆየተው?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም በብፁዕ አቡነ ባስልዮስ በዚሁ በአዲስ አበባ ሐምሌ ፲፯ ቀን ነው የተሾምኩት! ሐገረ ስብከቱም ሐረር ነበር። በዚያም ለ፴፪ ዓመታት አገልግ የአለሁ ከ፲ በላይ አብያተ ክርስቲያናት አሠርቼአለሁ። ከ፰ ሺህ በላይ እሕዛብ ወደ እምነት ክርስትና አስተምሬ መልሻለሁ። በአጠቃላይ በቤተ ጉባኤ ያስተማርኩት ፰ ዓመታት ነው።

ፈለገ ጥበብ – ከጵጵስና እስከ ሽምግልና ባሉት ዘመናት ከሠሯቸው ሥራዎች ደስ ይሉኛል ብለው የሚያስታውሱት ካለ?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም – ዘወትር በማኅሌት አምላኬን በማገ ልገሌ በጣም ደስ ይለኛል።

ፈለገ ጥበብ – በገጠመኝ የሚያሳዝን ነገር የገጠመዎት ምን ነበር?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም – ድሮ ነው በጎንደር ቤት የመ ጽሐፍ ተማሪ ሳለሁ አን ዲት እናት ሃይማኖተ አበው አጽፈው ለጎንደር ቤት ማርያም ይሰጣሉ። ከዚያም እኔ በእለተ እሑድ መጽሐፉን አነብ ነበር። ከዚያም በተጨማሪ ዮሐ ንስ ወልደ ነጐድጓድ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ እስከ ምስካየ ኅዙናን ገዳም ይር ቃል። ታዲያ በዚያን ጊዜ መንገድ ጣልያን እስከ ሚገባ ድረስ በተለይ በክረምት በጣም ጭቃ ነው። መጽሐፉን በልብሴ እየሸ ፈንኩ በሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት አነብ ነበር በዚያን ጊዜ ይደበድበኝ የነበረው ዝናብ እንዲሁም ጭቃው አይረሳኝም።

ፈለገ ጥበብ – ሌላ የገጠመዎት ካለ በትም ህርት ቤት ከጓደኛ ጋር ተጣልተው ከሆነ? ወይም በቀለም ተከራክረው ከሆነ? አለዝያም በትምህርት ቤት ሲኖሩ «በእንተ ስማለማርያም» ሲሉ ውሻ እንኳን አልጮኸበትም?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም – ይህን ካነሣህ ዘንድስ አንድ ውሻ ነበረች ተማሪ ሲለምን ድምፅ አታሰማም ዝም ትላለች፤ ቁራሽ ተቀብየ ዘወር ስል ባቴን ነከሰችኝ። ይኸንን አስታውሳለሁ። የውሻ ቁስል ያድርግልህ እንደሚባለው ወዲያውኑ ዳንልኝ።

ፈለገ ጥበብ – የድሮ የነበሩ የመምህራን አያያዝና የአሁን መምህራን አያያዝ አንድ ይመስላል? በአሁን ጊዜ የአብነት ትምህርት ቤቶች በመዳከም ላይ ናቸው ስለዚህ እንዴት ሆነው ቢጠናከሩ ነው የሚሻለው ብለው ያምናሉ?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም – የድሮ የጐንደር መጻሕፍት ቤት ይንከባከቡት የነበሩት እጨ ኃይለ ሥላሴ ናቸው። ይኸውም ለ፵ የመጻሕፍት ቤት ተማሪዎች በወር ለየአንዳንዱ ፲ ብር እየሰጡ ለመምህሩ አንድ መቶ ብር፣ ለምክትሉ ሃምሳ ብር እየሰጡ ደህና ይዘውት ነበር። ጣልያ ንም ቢሆን እ[illegible] በጀቱ አላቆመውም በዚሁ ዓይነት የድሮ ትም/ቤት እንክብካቤ ይደረግለት ነበር። እጨጌ ራሴ አንዲት እማሆይ ታከለች የሚባሉ በገዛ ገንዘባቸው ያጻፉት መጽሐፍ ነበር። ያ መጽሐፍ የማነበው እኔ ነበርኩኝ በማነብበት ጊዜ ስማቸው እጠራ ስለ ነበር በዚህም ምክንያት ጐንደር ከገባሁት አንድ ቀን ብቻ ነው የለመንኩት።

ፈለገ ጥበብ – በአሁን ደረጃ የአብነት ትምህርት ቤቶች ማለትም የመጻ ሕፍት፣ የድጓ፣ የአቋቋም የቅኔ እየተ ዳከሙ ናቸው ስለዚህ እነዚህን ትምህ ርት ቤቶች ለማጠናከር ቤተ ክርስቲያን ምን ርምጃ ብትወስድ ነው ብለው ያምናሉ?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም – የአብነት ትምህርት ቤት እንዳይጠፉ በየአለበት ማጠናከር ያስፈልጋል። አብነት ነውና ሁሉ የሀገር ቅርስ ነው እጫብር፣ ቆሜ፣ ቤተ ልሔም ሆነ፣ እንዳይጠፉ ቤተ ክርስ ቲያን በጣም መጣር ያስፈልጋታል። ጐንደር ድሮ የሠርክ ጎብስት ነበር። አሁን ጠፍቷል። አሁንም የመምህራን ፍልሰት ከገጠር ወደ ከተማ በጣም ተስፋፍቷል። ድሮ ጎጃም የቅኔ፣ ጎንደር የመጻሕፍትና የአቋቋም መፍለቂያ ነበር። በአሁን ጊ.ኔ በጣም ቀንሷል ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ችግሩ በጊዜው ማቆም አለባት።

ፈለገ ጥበብ – የአርባ አራቱ ጐንደር ቀለም ስለሚባለው ቢገልጹልኝ?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም – አሁን [illegible] ያለው የታች ቤት ቀለም ነው። የላይ ቤት ቀለምም ጥሩ ነው። ለቀታ አለው ያሳመረዋል። የታች ቤት ቀለምም ጥሩ ነው ቁሙን አይለቅምና።

ፈለገ ጥበብ – ከእን የኔታ [illegible]ረገ ወይን ገብረ ማርያም በፊት የላይ ቤት ተጠያቂ ማን ነበር?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም – ዓቢየ እግዚእ የነበሩ የኔታ ወልደ ሰንበት ናቸው የላይ ቤት አቋቋም መጀመሪያ መፈጠርያው እዚ ያው ዓብየ እግዚእ ነው ከዚያ በኋላ ነው ወደ ሌላው የተስፋፋው።

ፈለገ ጥበብ – ያለንበት ዘመን የፈተና ዘመን ነው ይልቁንም ወጣቱ ትውልድ በኤድስ በሽታ እየተቀሰፈ ነው። ስለዚህ ለአንባብያን የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም – አንድ ለአንድ በሚለው ጋብቻ ራስን መጠበቅ ነው ወጣቱ ዛሬ በራሱ ፈቃድ የሚመራ እንጂ በአባት እናት ፈቃድ አይ መራም፤ እናም የአባቶችን ፈለግ እየተ ከተለ አንድ ለአንድ ጋብቻ እያጸና ቢኖር ይሻላል እላለሁ። በዘፈቀደ መኖር ብዙ ጉዳት ያመጣልና። ✣



# ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር



ከሁሉም መጀመሪያ ያለ እምነት አንድ ስንዝር መንገድ የማንራ መድበት ዓለም ሃይማኖት ነው። በሃይማኖት ውስጥ የሚነገረንን ሐሳብ ሂደን በዓይናችን የምናየው ወይም በጆሮአችን የምንሰማው ነገር አይደለም ምክንያቱም ሃይማኖት የሚታይና የሚዳሰስ ዓለም አይደለምና ነው። ሃይማኖት የሚታየውና የሚዳሰሰው በእምነት ዓይን ነው። ይሁንና ብዙዎች ሰዎች ሃይማኖትን አስመልክቶ የሚነገራቸውን ነገር ሊቀበሉት ያመነታሉ። የሚያዩትና የሚዳስሱት አይደለምና። ነገር ግን እንደዚህ ያሉ ሰዎች ያላስተዋሉት አንድ ቁም ነገር አለ እነርሱም እንደሚፈልጉት ሃይማኖት በዓይን ሊያዩት በእጅ ሊዳስሱት ከተቻለ ሃይማኖት መሆኑ ቀርቶ ዕውቀት፣ ሳይንስ እንደሚሆን አላስተዋሉም። በሃይማኖት ውስጥ ያለውን ቁም ነገር ማስተዋል የሚቻለው እምነት ሲኖር ብቻ ነው። እምነት ካለን በሃይማኖት ውስጥ ያለውን ቁም ነገር ቁልጭ ባለ ሁኔታ እናየዋለን፤ እውነተኞች ክርስቲያኖች ከሆንን፤ እውነተኞች አማኞች ከሆንን፤ ክርስቶስን ቀን በቀን ልናየው እንችላለን ቀን በቀንም ልንነካው እንችላለን፤ ሲያንጋግረንም እንሰማዋለን በእርግጥ እጃችንን ጠቁመን እግዚአብሔር (ክርስቶስ) ያው እዚያ ቁሟል ወይም ተቀምጧል ብለን ማሳየት አንችልም ምክንያቱም እግዚአብሔር (ክርስቶስ) እንደዚህ እንደለንበት ግዙፍ ዓለም ሁሉ ጠቁመን የምናሳየው አይደለምና ነው። እንኳን አምላክ የሆነው ክርስቶስን ጠቁሞ ማሳየት ቀርቶ የአንድ የሆነ የሒሳብ ፕሮብሌም መልስ እንኳ ለሐሳባችን ሲታየን፣ መልሱን በሐሳባችን ስናገኘው መልሱን እንዳገኘነው እርግጠኞች እንሁን እንጂ ሰው በዓይኑ እንዲያየው በእጁም እንዲነካው ማድረግ አንችልም። እንዲያስተውለው ልናደርገው ከቻልን ግን በዓይን የማየት ያህል፤ በእጅ የመንካት ያህል እንዲሰማው ልናደርገው እንችላለን።

እምነት ያለው ሰው ዓይን ካለው ሰው በማይተናነስ ሁኔታ ብዙ ነገር ሊያይ ይችላል። ክርስቶስን በዓይን እይተው ሊቀበሉት ቢቻል ኑሮ ምንም አያስደንቅም! ምንም አያስመሰግንም!

## ሰው የሚኖር በእምነት ነው

ዶ/ር የማነ ገብረ ማርያም

ነበር። በዓይን ሊያዩት ስለማይቻል በእምነት የሚቀበሉት ክርስቲያኖች ግን የሚመሰገኑ ናቸው። ብፁአን ናቸው። ወደ ሐዋርያው ወደ ቶማስ ታሪክ ፊታችንን መለስ ብናደርግ ክርስቶስን ሙቶ፣ ተቀብሮ ስላየው ከተቀበረበት ሊነሣ አይችልም በሚል ሐሳብ ከሞት መነሣቱ ለመቀበል አሻፈረኝ ያለ ሰው ነበር።

ታሪኩም እንዲህ ነው። ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ሐዋርያትን ተሰብስበው በነበሩበት ዝግ ቤት ውስጥ ገብቶ በመካከላቸው ተገኝቶ ሲያነጋግራቸው ከሐዋርያት አንዱ የሆነው ቶማስ ከእነርሱ ጋር አልነበረም ከእነርሱ ጋር ስላልነበረም እነርሱ ክርስቶስን እንዳዩት ሁሉ እርሱም ሊያየው አልቻለም ነበር። ኋላ ቶማስን ሲያገኙት ክርስቶስን እንዳዩትና እንዳነጋገራቸው ቢነግሩት የሞተ ሰው ሊነሣ አይችልም በሚል ሐሳብ የነገሩትን ቃል አላምንም ብሎአቸዋል። ክርስቶስ ዳግመኛ አሁንም በዝግ ቤት ውስጥ ለሐዋርያት ሲገለጽላቸው ቶማስም አብሮአቸው ነበር። ክርስቶስም ወደ ቶማስ ተመልክቶ እጁን እንዲያመጣና የተቸነከረው እጁንና እግሩን፣ በጦር የተወጋውንም ደረቱን፣ ዳሰሰ እርሱ ራሱ መሆኑን እንዲያረጋግጥና እንዲቀበል ሲጠይቀው ቶማስ ያን ሁሉ ራሱ አይቶ ስላረጋገጠ ክርስቶስን ጌታዬ አምላኬም ሲል ተቀብሎታል። ነገር ግን ቶማስ ክርስቶስን የተቀበለው በዚህ መንገድ ስለ ነበር ክርስቶስን አላስደሰተውም ምክንያቱም ያዩትን መቀበል ቁም ነገር የለውምና ነው። ቶማስ ክርስቶስን ያስደሰተው የነበረው ሐዋርያት ያዩትን ሁሉ በነገሩት ጊዜ ቃላቸውን አምኖ ተቀብሎ ቢሆን ነበር። እንደዚያ አድርጎ ቢሆን ኑሮ ክርስቶስም ያመሰግነው ነበር፤ ብፁዕ ነህ ይለውም ነበር። ነገር ግን ቶማስ የተቀበለው በዓይኑ ያረጋገጠውን ስለሆነ ምስጋናው ቀርቶበታል። ስለ እየኸኝ አምነሃል፤ «ሳያዩኝ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው» ብሎታል (ዮሐ.፳፥፳፱)።

እምነት የሚያስፈልገው በሃይማኖት ውስጥ ላሉ ቁም ነገሮች ብቻ አይደለም። ከዚያም ውጭ ለዚህ ለሚታየው ለሚዳሰሰው ግዙፍ ዓለም ስንኳ ሳይቀር እምነት ያስፈል ጋል። በዚህ በግዙፍ ዓለም እንኳ ያለ እምነት መኖር ብዙ ያስቸግራል የፈለግነው ቤት ወይም መንገድ ሲጠፋብን የአካባቢውን ሰው በቀን ወይም መንገዱን እንዲያሳየን እንጠ ይቀዋለን። የሚጠየቀውም ያውቀዋል ስለሚያውቀውም በቀናነት ይነግረናል በሚል እምነት ነው። ነገር ግን እንደሚያ ውቀው ካላመንን ወይም እንደሚያውቀው ብናምንም እንኳ ፈቃደኛ ሁኖ እንደሚያሳየን ካላመንን አንጠይቀውም። ምክንያቱም ከእርሱ የሚፈልገውን ነገር ካላገኘን ልንጠ ይቀው አስፈላጊ ሆኖ አይታየንምና ነው።

ከእርሱ የምንፈልገው ነገር እንደምናገኝ ካላመንን ነገሩን እንዲያደርግልን መጠየቁ ለእኛ ትርጉም አይኖረውምና ነው። ጓደኞቻችንም እኛ የማናውቀው እርሱ ግን የሚያውቀው አንድ ነገር ቢኖርና ስለዚያን ነገር ለማወቅ ጉጉት ቢኖረን እጥብቀን እንጠይቀዋለን ነገር ግን የምንጠይቀው እውነቱን እንደሚነግረን አምነን እንጂ ሊዋሸን አይችልም ብለን እርግጠኞች መሆን አንችልም። ይሁንና እውነቱን ይነግረናል፤ አይዋሸንም፤ አያታልለንም፤ ብለን አምነን



www.ethiopianorthodox.org

ቃሉን እንሰማለን። ሰምተንም እውነቱን ነው የነገረን ብለን እንቀበለዋለን። ከመጀመሪያው ይዋሽናል ብለን ከተጠራጠርን ግን ልንጠይቀው የሚያስፈልግበት ምክንያት አይኖርም። ምክንያቱም የሚለንን ሰምተን ካልተቀበልነው፤ ካላመንነው በስተቀር መጠየቃችንና የሚለውን መስማታችን ለእኛ ትርጉም አይኖርምና ነው። የማያምን ሰው፤ ጥርጣሬ ያለው ሰው፤ ከሰው ቤት ሄዶ ከራሱም ቤት ጥምር ምግብ ቀርቦለት እንኳ የቀረበለትን ምግብ ለመመገብ በጣም ይጨንቀዋል። ምን እንዳለበት አውቆ ነው የምበላው ብሎ ተነሥቶ ሊሄድ ይችላል። በዚህም ጦሙን ከመዋሉና ራሱን ከመጉዳቱም በላይ ምግቡን አሰናድቶ ያቀረበለትንም ሰው ያሳዝነዋል። ተጠራጣሪ የሆነ ሰው ከመኪናም ላይ ተሳፍሮ አይሄድም ቢገለበጥስ፤ ብሎ ይፈራልና። የሚጠራጠር ሰው ትዳሩም አያተርፍም፤ ብከስርስ ብሎ ይፈራልና። ከተጠራጠረ ሲታመም ለምርመራ ወደ ሐኪም ዘንድ አይሄድ፤ መድኃኒቱን እምጥቶ የሚሰጠው ዘመድ ወይም ወዳጅ ቢኖረው እንኳ ወይ በጄ ብሎ አይቀበለውም፤ ወይ ተቀብሎ ይጥለዋል። በልቡ ምንም እያደርግልኝም ይላልና። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ከማንም ጋር መኖር አይችልም። በሰው ላይ እምነት ስለሌለው ሰውም እርሱን በጥርጣሬ ይመለከተዋል። ምን ዓይነት ሰው ነው? በማለት በእርሱም ላይ ክፉ ነገር የሚያደርስበት ስለሚመስለው ሰው እርሱን በጄ ብሎ አይጠጋውም ምስጢሩንም አይገልጽለትም «በሩቅ ካየው ይበቃዋል ከፊት ለፊቱ እየመጣም ከሆነ እርሱን ላለማነጋገርና ላለመጨበጥ ሲል መንገድ ቀይሮ ይሄዳል።

አንድን ነገር በጄ ብለው ለመቀበል ማየትና መዳሰስ ብቻ እንጂ ማስተማመኛ አድርገው የሚያስቡ የሚያዩ ሰዎች እጅግ አስቸጋሪዎች ስለሆነ ከእነርሱ ጋር መኖር የሚችል ሰው የለም አብሮት ቢኖሩም፤ የሚኖሩት አብሮአቸው ቢኖርም፤ የሚኖሩት ጭንቅ ጭንቅ እያላቸው ነው። ስለዚህም አብረውት የሚኖሩት ለአጭር ጊዜ ከመሆኑም በላይ ያ አጭሩ ጊዜም ይጠባቸዋል። ይህን ሰው መቼ በተገላገልነው በማለት እንደ ነፍሰ ጡር ሴት ከእርሱ የሚገላገሉበትን ቀን ያሰላስላሉ ያን ቀን እጅግ ይናፍቁታል። አንድን ሐሳብ ለመቀበል ብዙ ማረጋገጫ የሚሹ ካላየን፤ ካልዳሰስን፤ አይሆንም፤ የሚሉ ሰዎች እንኳንስ በሃይማኖት ጉዳይ ላይ ቀርቶ በዚህ በግዙፉ ዓለም እንኳ በሰላም አይኖሩም፤ ሕይወታቸው የጥርጣሬና የጭንቀት ሕይወት ይሆናል። እምነት ለዚህም ዓለም እንኳ አስፈላጊ ነው። ይህም ዓለም እንኳ ያለ እምነት አይኖርም በሁሉም ነገር የሚጠራጠር ሰው ሁሉንም ሰው የሚጠራጠር ሰው እንዴት ብሎ ኑሮው ይገፋለታል? በሁሉም ነገር ላይ ተጠራጥሮ የት ሊደርስ ነው? ለዚህ ሰው ኑሮ ሲያል አይሆንበትም ወይ? ከዚህ የባሰ የምድር ሲያል ከየት ሊመጣ ነው? እምነት በጣም አስፈላጊ ነው፤ ያለ እምነት አንዳችም ሥራ መፈጸም አይቻልም፤ ያለ እምነት ለወደፊት የሚሻል አንዳችም ዕቅድ መንደፍ አይቻልም፤ እምነት ለሰማይ ቤቱ የሚያስፈልገውን ያህል ለምድሩም ያስፈልጋል፤ አለማመን የሚዘጋው የሰማይን ቤት ብቻ አይደለም። የምድርንም ቤት ይዘጋል ሲያል ያለው በሰማይ ቤት ብቻ አይደለም ሲኦል በምድርም አለ። በረሀብ፤ በችግር፤ ለሚኖር ሰው ኑሮ ሲኦል የሚሆንበት ያህል ሁሉንም ተጠራጣሪ ለሚሆንም ሰው ኑሮ ከዚያ ያላነሰ ሲኦል ነው። እውነቱን ለመናገር አይተን ዳስሰን ማለትም አውቀን እርግጠኞች ሁነን ልንወጣው የማንችለውን ሥራ ጥምር የምንወጣው በእምነት ነው በማየትና በመዳሰስ በሚፈጸመው በዚህ ግዙፍ ዓለም ስንኳ ሳይቀር ያለ እምነት ብዙም መራመድ አስቸጋሪ ነው በዚህም ዓለም እንኳ ሳይቀር አውቀን ሳይሆን አምነን የምንቀበለው እያሌ ቁም ነገር አለ ለጊዜው አውቀን የተቀበልነው ሊመስለን ይችላል እርግጠኞች እንደሆንን አድርገን እናስብ ይሆናል ነገር ግን ቀረብ ብለን በዓይነ ልቡናችን ካጤነው ያ ሁሉ እርግጠኝነቱ አጠራጣሪ ይሆናል።

ለዚህ አንዳንድ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል ለምሳሌ ለአንድ ሰው እናትና አባቱ ለይቶ ለማወቅ ችግር እንደ ሌለበት እናስብ ይሆናል በእናት በአባቱ ቤት እያደገ እነርሱም ልጃችን ብለው በእንክብካቤ ይዘውት፤ ጎረቤት ሁሉ የእነርሱ ልጅ መሆኑን እያወቀ እርሱ ራሱም አባባና እማማ እያለ እየጠራቸው ይህን ሰው ወይም ልጅ እናትና አባቱ ይጠፉታል ብሎ ማሰብ የማይቻል ነው ብሎ የሚያስብ ሰው ይኖር ይሆናል ነገር ግን ነገሩ እንደዚህ ቀላል አይደለም። ይህ ሰው ወይም ይህን ልጅ እናትና አባቱን በትክክል የማያውቃቸው ሊሆን ይችላል እናትና አባቱ ናቸው የሚላቸው ሰዎች እርሱ እንደሚያስበው እናትና አባቱ ላይሆኑ ይችላሉ በእምነት እንደዚያ ናቸው ብሎ ካላሰበ በስተቀር ሴቷም እናትነቷ ወይንም አባትነቱ ሊያጠራጥር ይቻላል ሐሳቡን ከፍ ብለን እንጀምረው።

አንድ ሰው አባቱና እናቱ እነማን እንደሆኑ ሲጠየቅ አላወቃቸውም አይልም ተቀምጠው ወይም ቁመው ካሉት ሰዎች መካከል ወላጆቹ የታዩት እንደሆነ ለይቶ እንዲያሳይ ቢጠየቅ እነዚህ ናቸው ወይም እነዚያ ናቸው ወይም ለጊዜው ከዚህ የሉም ብሎ በልቡ ምንም ሳይጠራጠር ሊናገር ይችላል። ለእህቶቹና ለወንድሞቹም ይኸው ነው እነርሱንም አይቶ እንደሚያውቃቸው ያስባል። ነገር ግን ለጊዜው በዚህ ላይ ጥርጣሬ አይኑረው እንጂ እርሱ እንዳሰበው ላይሆን ይችላል ምናልባት እናትና አባቱ አድርጎ የሚያስባቸው ሰዎች ወላጅ እናቱና ወላጅ አባቱ ሳይሆኑ በሕፃንነት ዕድሜው ወላጅ እናቱ በስውር ከመንገድ ላይ ጥላው ወይም ከሰውየው ጋር ተመካክረው ከባዶ ቤት ትተውት ሄደው ሲያለቅስ የሰሙት በዚያ ቤት አግድመው የሚያልፉ ወንድና ሴት ነገሩ አጠራጥሮአቸው ተጠግተው ሲመለከቱት ገና ሕፃን በመሆኑ ወላጆቹ ጨክነው ጥለውት እንደሄዱና አውቀው ወደ ቤታቸው ወስደው ያሳደጉት ልጅ ሊሆን ይችላል። ባዕድ መሆናቸውንም ሸሽገውት ማለትም ወላጅ አባት ወላጅ እናቱ እንደሆኑ አድርገው በውሸት እንደዚያ እያሉ አሳድገውት ሊሆን ይችላል። የአካባቢው ሰው ከዚያ በፊት ከእነርሱ ጋር ያላየው ልጅ በማየቱ ምክንያት ጥርጣሬ እንዳይኖረውና ወሬ እንዳይናፈስ በማሰብም ያን ሕፃን ልጅ ይዘው ወደ አዲስ ሀገር ወይም ከተማ ሄደው ከዚያ ተቀማጭ ሊሆኑ ይችላሉ የቦታውም ሰው ልጃቸውን ይዘው የመጡ አዲስ ሰዎች ናቸው ይላል እንጂ የእነርሱ የራሳቸው ያልሆነ ልጅ ይዘው መጡ ብሎ አይጠራጠርም። ታዲያ ያ ሕፃን ከፍ ሲል እነዚያን ባዕድ ሰዎች አባቱና እናቱ ናቸው ብሎ እንደ ወላጆቹ አድርጎ ቢያስባቸውና አባባና እማማ እያለ ቢጠራቸው ለሰውም ወላጅ አባቱና ወላጅ እናቱ መሆናቸውን ቢናገር በእውነት ወላጅ እናቱና ወላጅ አባቱ ናቸው እንላለን በእርግጥ እንደዚያ አንልም ምናልባት ባዕድነታቸውን ወደ ኋላ ጊዜ ከደረስንበት ለዚያ ልጅ ባዕድ እንጂ ወላጆቹ ናቸው አንልም ራሱ ልጅ ግን ነገሩን ካልደረሰበት ወላጆቹ ናቸው የሚለውን ሐሳብ እንደያዘ ይኖራል።

ነገር ግን እንደዚያ ያስብ በዚህም እርግጠኛ ይሁን እንጂ እንደዚያ ብሎ ማሰብ ታሪኩ ሌላ መሆኑን አያስለውጥም። ታሪኩም እውነቱም እነዚያ ሰዎች ለእርሱ ባዕድ እንጂ እናትና አባቱ አለመሆናቸው ነው በትክክለኛም ሆነ በተሳሳተ መንገድ በእምነት የምንፈጽማቸው ብዙዎች ነገሮች አሉ። እነዚያም ነገሮች እኛ እንደምናስበው ላይሆኑ ይችላሉ በእምነት ስለምንፈጽማቸው ግን ለእኛ ጥርጣሬ አይፈጥሩብንም እምነት ወደሱም ሳይሄዱ በዚያው ባሉበት ቦታ ሁነው አንዳንድ ነገሮችን እንደሚያዩና እንደሚያደርጉ ዓይነት ማሰብ ማለት ስለሆነ ሄደው በአካል ከሚያዩት ይልቅ ሄደው በአካል ሳያዩት ካሉበት ቦታ ተቀምጠው በዓይነ ልቡና የሚያዩትና የሚፈጽሙት ይበዛል። እምነት ካለንበት ቦታ ስንንቀሳቀስ በዓይን ይመኙታል ከብዙ ቦታ ደርሰን የምንመለስበት ነጻ ትኬት ነው ይህን ነፃ ትኬት ከአለን ማንም ሊያገኘው ይቻላል ለሚያምን ሰው፤ እምነት ላለው ሰው፤ ታሪክ ጸሐፊዎች በመጽሐፍ የሚተርኩለትን ሀገርና ሕዝብ፤ ሥልጣኔውን አኗኗሩን ከቤቱ ተቀምጦ በመጽሐፋቸው የሚሉትን ሰምቶ በዓይነ ልቡናው ያን ሁሉ ሊያየው ይችላል። በዓይነ ልቡናው ተዘዋውሮም ሊጎበኘው ይችላል። የመልክዓ ምድር ምሑራንም ስለተለያዩ ሀገሮች ተራራዎች፤ ወንዞች፤ ሜዳዎችና፤ ሸለቆዎች፤ ሲያሚውተው የሚለውን ካመነ እርሱም ከቤቱ ሆኖ በዓይነ ልቡናው ያን ሁሉ ሊያየው ይችላል፤ የጠፈር ተመራማሪዎችም በጠፈር መንኮራኩር እማካይነት ካረፉበት ሩቅ የሰማይ አካል ላይ ሁነው ወይም በዙሪያው ሲሽከረከሩ ያዩትን ነገርና የሰሙትን ድምጽ ወደ መሬት ሲመለሱ ስለ ጉዞአቸው አንዳንድ ነገር ሲተርኩ ሰምቶ የሚያምናቸው ሰው እርሱም ከእነርሱ ጋር ሆኖ ያለ ወጪና ድካም አብሮአቸው በዓይነ ልቡና ቸው ያየዋል፤ የሚሰማም ከሆነ አብሮ ይሰማዋል። ነገር ግን እኔ ራሴ እስከ ቦታው ድረስ ሄጄ ራሴ በዓይኔ ካላየሁት በጆሮየም ካልሰማሁት፤ በእጄም ካልነካሁት፤ የሚባለውን ነገር አልቀበለውም የሚል ሰው እርሱ በዓይነ ልቦናው እነርሱ ያዩትን ሁሉ ነገር አብሮአቸው ማየቱ ይቀርበታል እርሱ የተለየ የጠፈር መንኮራኩር ሊሠራለትና ልምምድ አድርጎም ራሱ ሄዶ አይቶት እንዲመጣ ሊያደርገው የሚችል ማንም የለም። ያን ለማድረግ እጅግ ብዙ ወጪ ይጠይቃል የሚጠይቀውም ወጪ በሚሊዮን ሳይሆን በብዙ ቢሊዮን የሚቈጠር ገንዘብ ነው።

እምነት ሄደው ሊያዩት፤ ሂደው ሊሰሙት፤ ሄደው በእግር፤ ሊረግጡት ለማይችሉት ነገር ብቻ አይደለም የሚያገለግለው፤ ወይም የሚያስፈልገው፤ ለራሱ ለሚያዩትና ለሚሰሙትም እንኳ ቢሆን እምነት ያስፈልጋል እምነት ከሌለ ራሱ የሚያዩት ነገርም እንኳ ሊያጠራጥር ይችላል እምነት ከሌለ ራሱ የሚሰሙት ድምጽም አጠራጣሪ ሊሆን ይችላል ያለ እምነት ከጥርጣሬ (ከመጠርጠር) ነፃ ሊሆን የሚችል ምንም ነገር አይኖርም መጠራጠር ካለ ራሱን የሚያዩትም ነገር የውሸት ሊሆን ይችላል ብሎ ሊጠራጠሩት ይችላል፤ ራሱን የሚያዩትን ነገርና የሚሰሙትንም ድምጽ ጭምር መጠራጠር ይቻላል የምለው ያለ ምክንያት አይደለም። አንዳንድ ጊዜ የሌለም ነገር በሐሳብ ይታየናል፤ የሌለው ድምጽ ይሰማናል።

በዚህ ጊዜ ስላየነው ብቻ ወይም ስለሰማነው ብቻ እውነት ነው አለ ብለን በእርግጠኛነት መናገር አይቻልም። ያለ እምነት ስለሚያዩት ነገርና ስለሚሰሙትም ድምጽ እውነተኛነትም እርግጠኛ መሆን አይቻልም እምነት በሁሉም ነገር ላይ በምናየውና በምንሰማው ላይ ጭምር ተጠራጣሪዎች ከመሆን ያድነናል።

ስለዚህ እምነት የማያስፈልግበት ቦታ የለም። እምነት በሁሉም ነገር ያስፈልጋል በእምነትና በእውነት በሚያዩትና በሚሰሙት፤ እንዲሁም በውሸት እንዳዩትና እንደሰሙት በሚያስቡት ነገር መካከል ልዩነቱን በትክክል ለማስተመጥ በጣም አዳጋች ነው። ከዚያም የታየ ነገር አለ፤ ከዚህም የታየህ ነገር አለ፤ የትኛው የእውነት የትኛው የውሸት እንደሆነ እግዜር ይወቀው። ለእኛ ሁለቱም ያው ነው፤ ሁለቱም እውነት ነው፤ ሁለቱም እውነት መስሎ ይታየናል።

አንደኛውን ከሌላው በእርግጠኝነት የምንለይበትና የማይለይበት ዘዴ የለንም። ራሱ ምትሃት እያልን የምንቸገርበትም ዕይታ ይኸው ነው፤ ዕይታ ሁሉ ምትሃት ባይሆንም እንኳ ምትሃት ሁሉ ግን እይታ ነው ምክን ያቱም ዕይታ ያልሆነ (የማይታይ) ዕይታ ሊኖር አይችልምና ነው። ነገር ግን ችግሩ ያለው የውሸት ዕይታውን (ምትሃቱን) ከእውነተኛው ዕይታ (ምትሃት) ካልሆነው ዕይታ ከመለየቱ ላይ ነው። ማየት ራሱ እውነተኛውና ሐሰተኛውን አያስለየንም። ይሁንና በመሠረቱ እያየ ነውም የውሸት ሊሆን ቢችልም እንኳ (ማየትን) (ዕይታን) ስለዚያ ስለምናየው ነገር አንድ ነገር እውነተኛነት እንደ ማረጋገጫ አድርገን እንመለከተዋለን፤ በእምነት (አለበለዚያ ትልቅ ችግር ይገጥመናል ራሱን የምናየውንና የምንነካውን ከተጠራጠርን፤ ስለምናየውና ስለምንነካው ከተጠራጠርን፤ ስለምናየውና ስለምንነካው እንዴት እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን?

የቅርብ የራቀበት ሰው የሩቁ ሊቀርበው አይችልም። ስለሚያየውና ስለሚነካው ስለምድሩ የሚጠራጠር ሰው ስለሚያየውና ስለማይነካው ስለ ሰማይ ቤቱ እርግጠኛ ሊሆን አይችልም። የሚያየውን እሺረኝ ብሎ የማያየውን እቀበለዋለሁ፤ አምንበታለሁ፤ የሚለው ሰው ማንም ሊያምነው አይችልም። ያን የሚል ሰው ካለ ውሸታም መሆን አለበት (ዮሐ.፫፥፲፪)። ✚



www.ethiopianorthodox.org



# መግረሬ ፀር

ይህ ዓምድ መናፍቃንና አጽራረ ቤተክርስቲያንን የሚያጋልጡ ጽሑፎች የሚቀርቡበት፣ የእመቤታችን፣ የጻድቃንና የሰማዕታት አማላጅነት ተራዳኢነት የሚተነተንበት ይሆናል።

ከመልአከ ሰላም ኃይለ ኢየሱስ ከበደ

## ያለእምነት እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይቻልም

በመጀመሪያ ሃይማኖት (እምነት) የሚለውን እንመለከታለን።

ስንመለከተውም ሃይማኖት (እምነት) የሚለው ቃል በንባቡ ልዩነት ያለው ቢመስልም በአፈታት ልዩነት የሌለው አንድ ነው።

በምሥጢር ሲተነተን ግን ሁለትነት አለው፤

ሀ. ማመንን ሲሆን ይህ ማለት በረቂቅ ልቡና መሣልን፣ ማሰብን፣ ሐሳብን በማወቅ፣ ማረጋገጥን፣ መፍቀድን፣ መወደድን፣ ለቃሉ ታዛዥ፣ ለመንግሥቱ ተገዥ፣ መሆኑን ትውክልት (መመካትን) ተስፋዎን ተስፋ ማድረግን ሁሉ ያጠቃልላል። ይህ ማመን የሚለው ቃል ሲሆን፤

ለ. መታመን የሚል ቃል ደግሞ በልብ (በረቂቅ አእምሮ) ያመኑትን በአንደበት መመስከር መናገር፣ ማመስገን፣ ማምለክ፣ መስገድ፣ መገዛት፣ መገበር፣ ለቃሉ ታዛዥ ለመንግሥቱ ተገዥነትን በሥራ ሁሉ መግለጥ ማለት ነው። ሮሜ.፲፥፱።

ይህንንም ሐሳብ ቅዱስ ጳውሎስ ሲተነተነው «ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ እንደሆነ በአፍህ ብታምን እግዚአብሔርነቱም ከሙታን ለይቶ እንደ አሥነሳው በልብህ ብታምን ትድናለህ ያመነበት ልብ ይጸድቃል ያመነበትም አፍም ይከበራል»። ብሏል ልቦ አምላክ ዳዊትም በመዝሙር ፩፻፲፰፥፩ ገልጾታል።

ሐዋርያው ይሁዳም «ወንድሞቻችን ሆይ በሁሉም ተፋጠንኩ ስለሁላችን ሕይወት እጽፍላቸው ዘንድ ተግቼ እጅግ እጽፍላችኋለሁና ለክርስቲያን የተሰጠች ሃይማኖትን ተግባር ታደርጓት ዘንድ እማልዳችኋለሁ» ሲል ገልጦታል። ፪ኛም «ወንድሞቻችን እናንተ ግን በከበረች ሃይማኖት ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ፣ ወደ ዘለዓለም ሕይወት የሚወሰደውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ብትጠባበቁ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ» በማለት ጽፎልናል (ይሁዳ ፩ ቁጥር ፳)

እንግዲህ ሃይማኖት ከላይ የተናገረናቸው ነገሮች የሚገለጡበት የቅድስና ሥራ ሁሉ መሠረት ነው።

ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ በሌላው መልእክቱም «ያለ ሃይማኖት (ያለእምነት) እግዚአብሔር ደስ ሊያሰኙት አይቻልም። ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሰው እግዚአብሔር በመንግሥቱ እንዳለ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጣቸው አስቀድሞ ሊያምን ይገባዋል ሲል ተናግሮአል።

ሃይማኖት እምነት ለሚለው ቃል ይህንን ያህል ከተናገርን ትምህርት የሚለው ደግሞ ስለዚህ ነገር መማር ማወቅ ማለት ነው።

### ሃይማኖት ምንድነው?

በመጀመሪያ ሃይማኖት ማለት ምሥጢረ ጥበብ ማለት ነው።

፩. ለዚህ ዓለም ሠራዒ መጋቢ፣ አስተናባሪ፣ አስተዳዳሪ፣ ሠሪ፣ ቀጭ (በጐ ቢሠራ ዋጋ ከፋይ ክፉ ቢሰራ ሠሪ ቀጭ) አለው ብለን የምናውቅበት የምንረዳበት ማለት ነው። የጻድቅ ሰው ልቡና ሃይማኖትን ይማራል ብሎ ጥበበኛው ሰሎሞን እንደተናገረው (ምሳ.፲፰፥፳፰)።

፪. የአንድነት የሦስትነት ሃይማኖት የእግዚአብሔር ሕልውና ነው።

፫. የሥጋዌ ምሥጢር ማለት ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ሰውን የማዳኑ ምሥጢር ነው።

ይህንንም ፈረንጆች ዶግማ ይሉታል ቋንቋው የጽርዕ ቢሆንም በዓለም አቀፍ ደረጃም ይጠቀሙበታል። ይህም ሲተነተን በመጀመሪያ በቁጥር አንድ ላይ ያለውን ብንመለከት እግዚአብሔር ሃያ ሁለቱን ሥነ ፍጥረታት ፈጠረ ብንል ሰውንና መላእክትን ስሙን እንዲቀድሱ ክብሩን እንዲወርሱ ፈጠራቸው። የቀሩትን ፍጥረታት ለአንክሮ፣ ለተዘክሮ፣ ለምግበ ሥጋ፣ ለምግበ ነፍስ፣ ፈጠራቸው።

ይህንንም መጽሐፍ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ይልና ይተነትናል ፪ኛውን የአንድነት የሦስትነት (የሥላሴ ሕልውና) ስንመለከት ደግሞ እግዚአብሔር በአንድነት በሦስትነት ሲሰለስ ሲቀደስ የሚኖር አንድነት ሦስትነት ያለው አንድ አምላክ መሆኑን እናምናለን።

በአንድነቱ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ብለን ተናግረናል። ይህ እንግዲህ የባሕርይ አንድነቱ ነው በዚህ መልኩም ከዘፍጥረት ጀምረን ፹፩ መጻሕፍትን ብንመለከት የመጻሕፍቱን መልእክት ተሟልቶ እናገኘዋለን።

የሦስትነቱም ነገርም ብንመለከት በብዙ ቦታ እናገኘዋለን ለምሳሌ ያህል እንኳን ከብዙ ጥቂቱን ብናነብ «እግዚአብሔርም ሰውን በመልካችን በምሳሌአችን እንፍጠር አለ»፣ የሚል አንድ ነት ሦስትነት የተጠቃለለበት ሐሳብ እናገኛለን (ዘፍ.፩፥፳፮)።

እልፍ ብለንም ዘፍ.፲፩፥፮–፯ ባለው ቃል የከላደውያንን ቋንቋ ሲደባልቅ «ኑ» እንውረድ አንድ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን እንደባልቀው ይልና እግዚአብሔር ከዚያ በምድር ላይ ሁሉ በተናቸው፣ ከተማይቱንም መሥራት ተው» ይላል ይህም የአንድነት የሦስትነት ነገር አለበት።

አሁንም እልፍ ብለን ዘፍጥረት ፲፰፥፩–፲፭ ያለውን ቃል ብንመለከት አካል ከህልውና ተገልጾለት አብርሃም ከሥላሴ ጋር ያደረገውን ንግግር እናገኛለን። ቃሉም እንዲህ ይላል «በቀትር ጊዜም አብርሃም በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት ዓይኑንም አነሣና እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ፣ ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንኳን ደጃፍ ተነሥቶ ሮጠ። ወደ ምድርም ሰገደ፣ እንዲህም አለ፣ አቤቱ በፊትህ ሞገስን አግኝቼ እንደ ሆነ ባሪያህን አትለፈኝ ብዬ እለምንሀለሁ»። በማለት በፈቃድ አንድ መሆናቸውን ከተናገረ በኋላ በአካል ፫ መሆናቸውን ደግሞ ሲገልጥ «ጥቂት ውሃ ይምጣላችሁ እግራችሁን ታጠቡ በዚችም ዛፍ ሥር ዕረፉ፣ ቍራሽ እንጀራ ላምጣላችሁ ልባችሁንም ደግፉ፣ ከዚያም በኋላ ትሄዳላችሁ፣ ስለዚህ ወደባሪያችሁ መጥታችኋልና» ብሏል።

እነሱም የእሱን አነጋገር በማጽደቅ እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው በአንድ ፈቃድ በአንድ ቃል እንዳልህ አድርግ ብለው ፈቃደኛነታቸውን ከገለጹለት በኋላ ወደ ሣራ ፈጥኖ በመግባት ሦስት መሰፈሪያ ዶቄት ሠፍራ አውጥታ አንድ አድርጋ ለውሳ አንድ እንጀራ አድርጋ እንድትጋግረው አዘአል ይህም አንድነት ከሦስትነት፣ ሦስትነት ከአንድነት ተለይቶ እንደተገለጸለት ያስገነዝባል። ከዚህ ጋር ይህ ምክንያት ሆኖ ክርስቶስ የሚገኝበትን ንጹሕ ዘር ይስሐቅን እንደሚወልድ ሥላሴ ተስፋ የሰጡት በዚያው አንድነት ሦስትነት በተገለጸበት ቦታ ነበር።

ቀደም ብሎም በምዕራፍ ፫፥፳፪ ላይ የተናገረው ቃል አዳም ከእኛ እንደ አንድ ሆነ የሚል ነው ይህም ማለት ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል የአዳምን ባሕርይ አደርጋለሁ ብሎ ተስፋ መስጠቱ ነው። ይህም ቃል የአንድነት የሦስትነት መግለጫ ሆኖ እናገኘዋለን።

እንግዲህ አንዱ የሃይማኖት ምሥጢር እግዚአብሔርን በአንድነቱ በሦስትነቱ ማወቅ ሲሆን ፪ኛው መታወቂያውም ሥነ ፍጥረቱ ነው።

ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ «የማይታየው የማይለየው እግዚአብሔር በሥነ ፍጥረቱ ተለይቶ ይታወቃል ብሎ ተናግሮአል። (ሮሜ.፩፥፳)

በሐዲስ ኪዳንም «አነ ውእቱ ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት» የሚለውን ቃል የአንድነት የሦስትነት ባለቤት እኔ ብሎ ተርጕሞታል ፪ዮሐ.፩፥፱።

እንግዲህ እንደ ዮሐንስ አተረጓጐም የጽድቅና የሕይወት መንገድ አንድነቱን ሦስትነቱን ማወቅ ነው ማለት ነው።

እርሱም ራሱ «እኔንስ ብታውቁ አባቴንም ባወቃችሁት ነበር» ብሏል። ገልጦም «በወልድ ያመነ የዘለዓለም ሕይወት አለው» ብሎ አስትም ሮአል። (ዮሐ.፲፬፥፯–፰፤ ዮሐ.፫፥፴፭–፴፮)።

ስለዚህ የአንድነት የሦስትነት ሃይማኖት የጽድቅ መንገድ መሆኑን መረዳት ክርስቲያናዊ ግዴታችን ነው።

ቀደም ብሎም ዮሐንስ ወንጌላዊ በመጀመሪያው ምዕራፍ የጻፈው ቃል «ለሰው ሁሉ የሚያበራ እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር በዓለምም ነበር ዓለሙም በእርሱ ሆነ ዓለሙም አላወቀውም። የእርሱ ወደሆነው መጣ፣ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ» ሲል ጽፎአል (ዮሐ.፩፥፱–፲፫)።

ሃይማኖት (እምነት) ይህንን ሁሉ መልእክት ያጠቃለለ ነው ምክንያቱ ካላመኑ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን አይቻልም የእግዚአብሔር ልጅ ካልሆኑም የመንግሥቱ ወራሽ መሆን አይቻልም። ስለዚህ አንድነቱን ሦስትነቱን፣ ሥጋዌውን (ሰው) መሆኑን፣ ሥጋ መልበሱን፣ መሞት መነሣቱን፣ ማመን እውነተኛ የጽድቅ መንገድ መሆኑን ማወቅ መረዳት ግድ ነው። ለሁሉም የአንድነት የሦስትነት ባለቤት አንድነቱን፣ ሦስትነቱን ይግለጥልን አሜን። ✣





www.ethiopianorthodox.org

# ከ ወ ጣ ቱ ለ ወ ጣ ቱ

## በሕይወቴ ዘመን የሚያስደስተኝና የማልረሳው ትዝታየ

የብዕር ትኝት በመምህር ዕንቁባሕርይ ተከሥተ



ለዛሬ ከውጣቱ ለወጣቱ እንግዳ አድርገን ያቀረብንላችሁ ወጣት ገሊላ ዘገየ ትባላለች።

ገሊላ የተወለደችው በደብረ ዘይት ከተማ ሲሆን ቄሬ ያለችው በምዕራፈ ቅዱሳን አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት ነው።

ገሊላ ዘገየ በሰንበት ት/ቤት ከ፲፱፻፹፪–፲፱፻፺፫ ዓ.ም በሰንበት ትምህርት ቤት በማገልገል ላይ ነች። በዚሁ ሰንበት ት/ቤት አሁን በሊቀ መንበርነት በመምራት ላይ ናት።

ገሊላ ዘገየ ቀልድ የማታበዛ ቁም ነገረኛ ናት።

ገሊላ ከሊቀ መንበርነት በተጨማሪ የደቡብ ክፍለ ከተማ የወጣቶች ሕብረት ዋና ፀሐፊ ሆና በማገልገል ላይ ነች።

ለሁሉም ለወጣቶች ብዙ የምት ለን ስለ አለ በጥሞና እንከታተል። መልካም ንባብ።

ገሊላ ዘገየ ትባላለች የተወለ ደችው በ፲፱፻፸፱ ዓ.ም ነው በደብረ ዘይት ከተማ ወደ ሰንበት ት/ቤት እንዴት ገባሽ ብየ ጠይቄያት ነበር።

ገሊላ ስትመልስልኝ ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት የገባሁት በፊትም እድገቴ በቤተ ክርስቲያን ስለ ነበር በቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን አገለግል ነበር፤ በተጨማሪ ወደ አዲስ አበባ ተቀይረን በመጣን ጊዜ፤ በምዕራፈ ቅዱሳን አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እና አቡነ አረጋዊ ገዳም ሰንበት ትምህርት ቤት በ፲፱፻፹፪ በሰኔ ወር መፀ ሻ ላይ ነው የገባሁት አገባቤም ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ስመጣ የነበረኝ አመለካከት ሰንበት ተማሪ መሆን የሚችለው ቅዱስ የሆነ ሰው መስሎ ይሰማኝ ስለነበረ በጊዜው ደግሞ በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎች በአገልግሎ ታቸው ደስ ይሉኝ ስለ ነበር በአካባቢው ቁጭ ብዬ ስከታተል፤ አሁን በደብረ ዘይት ናዝሬት ቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን በዲቁና በማገልገል ላይ ያለው ዲያቆን በእድሉ ሰንበት ትምህርት ቤት እንድገባ ጋበዘኝ፤ በዕለቱ ጉባኤውን ተከታተልኩ ያው በዚያ ገብቼ ቀረሁ በማለት ትገልጻለች።

የሰንበት ት/ቤት እንቅስቃሴ የወጣቱ መንፈሳዊ ሕይወት ምን ይመስል ነበር ብየ ላቀረብኩላት ጥያቄም:-

ገሊላ ስትመልስ በዚያን ጊዜ ጥሩ እንቅስቃሴ ነበረው የአባላት ብዛት ውሱንነት ቢኖርም ለጊዜው የነበረው የመንፈሳዊ ትምህርት አሰጣጥ ጥሩ ነበር፤ ነገር ግን ብዙም አልቆየም አንዳንድ ችግሮች ነበሩ በዚያ የተነሣ ሰንበት ትምህርት ቤቱ ለተወሰነ ጊዜ አገልግሎቱ ያቆመበት ጊዜ ነበር፤ ከዚያ በኋላ በአዲስ መልኩ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ተባለ በዚያ መሠረት እንዲቀጥል ሆነ።

እንግዲህ አሁን የደረሰበት ደረጃ ስናየው እጅግ በጣም ከበፊቱ በከፍተኛ ደረጃ ሰንበት ትምህርት ቤቱ በመንቀሳቀስ ላይ ነው።



ወጣቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ በማድረግ ላይ ያለ ሰንበት ትምህርት ቤት ነው ብላኛለች።

ወደዚሁ ሰንበት ትምህርት ቤት ከገባሽ ስንት ዓመት ይሆንሻል ብዬ ላቀረብኩላት ጥያቄ። ገሊላ በሰንበት ትምህርት ቤቱ አባል ከሆንኩኝ ፲፪ ዓመት ሆኖኛል ስትል ነግራኛለች።

በሥራ አመራር ሊቀ መንበርነት አገልገለሻል? ብዬ ጠይቄያት ነበር ገሊላ ስትመልስ አዎ በመጀመሪያ በንዑስ ክፍል፤ በሥነ ሥርዓት፤ በመ ዝሙር ክፍል በኪነ ጥበብ ካገለገልኩ በኋላ ከ፲፱፻፹፯ ዓ.ም ጀምሮ ለአራት ዓመታት በጸሐፊነት አገልግያለሁ። ከ፲፱፻፺ ዓ.ም እስከ አሁን በሊቀ መንበርነት በማገልገል ላይ ነኝ ያለሁት ብላኛለች።

ገሊላ አንቺ በጾታሽ ሴት ነሽ በሰንበት ት/ቤት የሚማሩ ወጣቶች ደግሞ ትኩስ ኃይል ናቸው። ስለዚህ በሊቀ መንበርነት በመትስሪበት ጊዜ ወጣቶች አንታዘዝም በማለት ያሸገሩሽ ይኖራሉ ብየ ጠይቄያት ነበር።

ገሊላ ስትመልስ (ሳቅ እያለች) በመሠረቱ በሰንበት ትምህርት ቤቱ በነበረን ሕይወት ውስጥ ተማሪውም በደብሩ ያሉ ካህናትም እጅግ አድርጌ የማመሰግናቸው ምንም ሴት እንዳመ ሆኔ መጠን የገጠመኝ ነገር ይኸ ነው የምለው ነገር ባይኖርም በሥራየ ላይ በማበራታት አለቆችም ራሳቸው በዚህ ባለንበት መንፈሳዊ ሕይወት እንድን በረታ አስተዋጽኦ አድርገውልናል። በተለይ ደግሞ ሰንበት ተማሪዎች አንድ ቀን እንኳን አስቸግረውኝ አያ ውቁም። በጥሩ ሁኔታ ነው ሳገለግል የኖርኩት። ትላለች።

ገሊላን ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት በመግባትሽ ያገኘሽው ጥቅም ምንድነው ብዬ ጠይቄያት ነበር።

ገሊላ (በአግራሞት) ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት በመግባት ብዙ ጥቅም አግኝቼአለሁ። ሰንበት ትምህርት ቤት ከገባሁት ጊዜ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያኔን ማንነት፤ የእኔን ምንነት፤ እንዴት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አማኝ ልሆን ቻልኩ። የሚለውን በአጠቃላይ ስለ ቤተ ክርስቲያኔ ምሥጢር በሚገባ አንድ በአንድ ሰንበት ትምህርት ቤቴ ነው ያስተማረኝ።

የእግዚአብሔር ቃል እንዳውቅ ያደረገኝ እዚህ ደረጃ እንድደርስ ያበ ቃኝ ከሰንበት ትምህርት ቤት ብዙ ቁም ነገርን ተምሬአለሁ ትዕግሥትን፤ ራስን መግዛት፤ አስተዋይነትን፤ መቻልን፤ ፍቅርን...ብቻ ዘርዝሬ አልጨርሰውም።

እጅግ ብዙ ከሰንበት ትምህርት ቤቴ ተምሬአለሁ በመንፈሳዊ ሕይወቴ በኩል ብዙ ጥቅም አግኝቼበታለሁ ትላለች።

ገሊላ የሕግ ተማሪ መሆንሽን ሰም ቼአለሁ ለምን የሕግ ክፍል ልትመ ርጪው ቻልሽ ብዬ ላቀረብኩላት ጥያቄ:-

ገሊላ ስትመልስ ሕግን ለመማር የራሴ ምርጫ አልነበረም የእኔም ምርጫ ኮምፒዩተር ሳይንስ ለመማር ነበር፤ በተሰጠው ምደባ መሠረት በዚሁ ትምህርት እንዳገለግል ነው የደረሰኝ። በደረሰኝም መሠረትም ትምህርቴን በሚገባ እማራለሁ በተጨማሪም የማጠናከርያ ትምህርቶችን ኮርሶችን በአፍሪካ ቤዛ ኮሌጅ እየወሰድኩኝ ነው። አሁን የሦስተኛ ዓመት ተማሪ ነኝ ስትል ትገልጻለች።

ገሊላ ከዚህ በተጨማሪ የደቡብ ክፍለ ከተማ የወጣቶች ኅብረት ዋና ጸሐፊነት ነች። ገሊላ ስለ ወጣቱ ኅብረት ስትገለጽ እንዲህ ትላለች። የደቡብ ክፍለ ከተማ የወጣቶች ኅብረት መመሥረት ለደቡብ ክፍለ ከተማ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በአዲስ አበባ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት በምሥራቅ በምዕራብ፤ በሰሜን፤ በደቡብ ተከፋፍለው እየተንቀሳቀሱ ነው። የደቡብ ክፍለ ከተማ የወጣቶች ኅብረት መመሥረት ጥቅሙ።

፩. የሰንበት ትምህርት ቤት በተናጠል ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረግ ላይ ናቸው።

፪. በተጨማሪ ደግሞ በየክፍለ ከተማው እንዲደራጅ መምሪያው ማድረጉ በጣም ጥሩ ሥራ ነው ብየነው የማምንበት፤ ምክንያቱም ሰንበት ትምህርት ቤቶች በኅብረት ደግሞ ጥሩ ሥራ ይሠራሉ ብየ ስለማምን ነው። በዚህ በደቡብ ክፍለ ከተማ እስከ አሁን ድረስ ሰፋ ያሉ እንቅስቃሴ ተደርጓል። አሁንም በመንቀሳቀስ ላይ ነን። ለወደፊቱም ሰንበት ትምህርት ቤቶች ተቀራርበው ድክመታቸውን አንዱ ለአንዱ በከፍተኛ ደረጃ ያለው በዝቅተኛ ደረጃ ላለው ማበረታታት ልምዱን እንዲያካፍለው በተቻለ ተደጋግፎ ጥሩን ሥራን ለመሥራት ከፍተኛ አሰተዋጽኦ ያደርጋል ብየ አምንበታለሁ ትላለች።

እስከ አሁን ድረስ በተደረገው እንቅስቃሴ ምን ያህል መቀራረብና የልምድ መለዋወጥ ተደርጓል? ብየ ላቀረብኩላት ገሊላ ስትመልስ ይህን እንኳን ከእኔ ይልቅ ስለጠቃሚነቱ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ቢጠየቁ የበለጠ መልስ ይሰጡሃል በማለት ቋጭታዋለች።

ሌላው ለገሊላ ያቀረብኩላት ጥያቄ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምርያ የዜማ ሊቃውንት ሰብስቦ በማዕከላዊ ከየደብሩ የተውጣጡ ወጣቶች ረዘም ላሉ ጊዜያት መዝሙር በማስተማር ላይ ይገኛል በዚህ በማዕከላዊ የሰለጠኑ ወጣቶች በየአካባቢው በሚገኙ ወጣቶች ምን



www.ethiopianorthodox.org

ያህል ተሳትፎ አላችሁ? ምን ያህል ውጤት ያስገኝ ይመስልሻል? ብዬ ላቀረብኩት ጥያቄ:-

ገሊላ አሁን የጠየቀኝ ጥሩ ጥያቄ ነው ወጣቱ እያየ ነው ይመስለኛል በሰንበት ትምህርት ቤታችን በከፍተኛ ችግር ይጠቀስ የነበረው የመዝሙር ችግር ነበር በሊቃውንት የተዘጋጀ ዜማ እና መዝሙር ያለመኖር ጉዳይ ነው። ይኸውም ያስከተለው ችግር ሰዎች የመሰላቸው መዝሙር ነው ብሎ መቀበል፣ ያልመሰላቸው ደግሞ አይደለም ብለው መኮነን ነበር። በአሁኑ ደረጃ ግን ያ ሁሉ የለም ምክንያቱም መዝሙር የሚተላለፈው ከአንድ ምንጭ ነውና እሱም በሊቃውንት የተዘጋጀው ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምርያ በመሆኑ በዚሁም ከፍተኛ ጥቅም አግኝተንበታል። የቅዱስ ያሬድ ዜማ ለይተን እንድናውቀው ሆነናል። በወጣቱ በኩልም ከፍተኛ የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ እና መሻሻል እየታየ ነው ሁሉም ወደ ያሬዳዊ ዜማ እየመራ ነውና። ምክንያቱም ያ የነበረው የዜማ መለያየት በሙሉ ማለት ይቻላል ተወግዷል። ከዚሁ የሚጠናው በአጠቃላይ በሰንበት ትምህርት ቤቶች ተግባራዊ እየሆነ ነው።

ምክንያቱም በጉባኤ ተገናኝተን ስንዘምር አንድ ዓይነት ዜማ አንድ ዓይነት ግጥም ነው የምንዘምረው ይኸ ደግሞ የመምርያው ውጤት ነው።

እኔ የምናፍቀው ትላለች ገሊላ ብዙ ዓመት የተደከመበት መዝሙር በካሴት ተቀድቶ ለምዕመናን በአጭር ጊዜ እንዲሰራጭ ነው።

ገሊላን መልኳም ይሁን መጥፎ የገጠመሽ ገጠመኝ ካለ ብየ ጥያቄያት ነበር። ገሊላ ከገጠመኞች ውስጥ ማንሳት የምፈልገው በዚሁ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እያለን በሰንበት ት/ቤት በአድራሽ ችግር ምክንያት ለዘጠኝ ወራት ከደጅ ተምረን ነበር፤ በዚህ ወቅት የሰንበት ትምህርት ቤታችን ፲፮ኛው ዓመታዊ በዓላችን ደረሰ ያው በቤተ ክርስቲ ያናችን እንደሚታወቀው ብዙ የሰንበቴ አድራሾች አሉ፤ ዓመታዊ በዓላችን ከውጭ አናከብርም ብለን ደብሩ እናስፈቅዳለን ደብሩ ስናስ ፈቅድ ደብሩ ይፈቀድልናል። ኮሚቴ ዎች ግን አይፈቅዱልንም ውጪ አናከብርም ብለን ቁልፍ ገንጥለን ገባን። በዕለቱ ሰዎች አልነበሩም ተነግሩዋቸው የሰንበቴው ሊቀ መንበር ይመጣሉ እኛ የዚያን ጊዜ መድረኩን እየሠራን እያለ በፖሊስ ተከበናል ስንጠየቅ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ይዞታ ነው። ስለዚህ ትክክል ሥራ ነው የሠራነው አልን። ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተወሰድን ለመጀ መሪያ ጊዜ ነው ፖሊስ ጣቢያን ያየሁት በጣም ፈርቼ ነበር እዛም መንገላታት ደርሶብናል። ከዚያ በኋላ ግን በዋስ ተለቀን ሀገረ ስብከቱም በከፍ ተኛ ሁኔታ ደብዳቤ ጽፎልን ልንድን ችለናል። ይኸ ከማልረሳው ትዝታየ ነው።

ሌላው ደብረ ዘይት በነበርኩበት ጊዘ ፍኖተ ሰላም የሚባል ትምህርት ቤት ነው የምማረው ወደ ደብረ ዘይት አካባቢ ታውቀው እንደሆነ አንድ ዛፍ አለ፤ በዚያ ዛፍ ባዕድ አምልኮ የሚፈጸምበት ነበር በዚያ አካባቢ ስናልፍ ልጆች ነበርን በዛፍ ሥር ዳቦ፤ ገንዘብ ተበትኖ ሳይ ጠበቅሁና ማንም ሳያይ ዳቦውን እስኪበቃኝ ድረስ በላሁና ያ ለባዕድ አምልኮ የተሰጠውን ገንዘብ በአጠቃላይ ሰብስቤ ለቤተ ክርስቲያን እና ለእኔ ቢጤዎች ሰጥቼአለሁ። ይህ በሕይወቴ ዘመን የሚያስደስተኝና የማልረሳው ትዝታየ ነው በማለት ትዝታዋን ገልጻልኛለች።

በመጨረሻ ለገሊላ ያቀረብኩላት ጥያቄ በሰንበት ት/ቤት ውስጥ እና በዓለም ላሉ ወጣቶች የምታስተላልፈው መልእክት ካለ ብየ ነበር።

ገሊላ በሰንበት ት/ቤት ላሉ ወጣቶች በሰንበት ት/ቤት በምንመላለስበት ጊዜ የተወሰነ ጊዜ ደርሰን የምናቋርጥ ሳይሆን ጽናት እንዲኖረው ያስፈልጋል።

ሌላው አገልግሎታቸው በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ብዙ እሚደከሙ ብዙ እሚለፉ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ናቸው። ምናልባት ከእኔ ሰንበት ትምህርት አንጻርም ሳየው ወጣቶች ለቤተ ክርስቲያን ብዙ ሲለፉ አያለሁና ጥሩ ነው፤ ሊበረቱበት ይገባል። በሰንበት ት/ቤት በሕይወቱ ሊኖሩበት ይገባል። ተማሪ መሆን ብቻ ሳይሆን በሰንበት ት/ቤት በሚገኘው ሕይወት ሊኖሩበት ይገባል።

ሌላው በዓለም ውስጥ ላሉ ደግሞ በዓለም መኖር እና በቤተ ክርስቲያን መኖር ከፍተኛ ልዩነት እንዳለው በሕይወቴ ስለተማርኩኝ ከዓለም ወደ ቤተ ክርስቲያን ተመልሰው በተለይ በሰንበት ት/ቤት ታቅፈው ቤተ ክርስቲያናቸውን እያገለገሉ ቢኖሩ ከሁሉ በላይ የእግዚአብሔርን ቃል እየሰሙ ጥሩ ደረጃ ይደርሳሉ ብዬ አምናለሁ።

በተለይ በአሁኑ ሰዓት ቀሳፊ የኤድስ በሽታ ብዙ ወጣቶችን እየቀሰፈ ይገኛል እና የእግዚአብሔር ቃል የሚለው «ልጄ ሆይ ውሃና እሳት አቅርቤልሃለሁ እጅህን ወደ ፈቀድ ኸው ስደድ» ነውና ዓለሙ እሳት ሆኖ እየፈጀን ስለሆነ ወደ ቤተ ክርስቲያን ተመልሰን ቅዱስ ቃሉን ሰመተን በሕይወት ጸንተን እንድንኖር ነው የማስተላልፈው። በዚህ ቀሳፊው ኤድስ የተያዙ ወገኖቻችን ደግሞ በእምነት ሆነው ወደ ቤተ ክርስቲያን ከቀረቡ በእግዚአብሔር ቸርነት እንደሚፈወሱ ስለማምን፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን ቀርበው እግዚአብሔርን እንድንለምን መልእክቴን ሳስተላልፍ ከዚሁም ጋር ዘመኑ የሰላም፣ የፍቅር የአንድነት እንዲሆንልን ምኞቴን እገልጻለሁ። አሚን። ✣

# ምሕዋረ ፀሐይ

ከያሬድ ፈንታ ወልደዮሐንስ
የቅዱስ ጳውሎስ ከ/መንፈሳዊ ት/ቤት መምህር

ዘመነ ማቴዎስ ፲፱፻፺፫ ፯ሺህ ፬፻፺፫ ዓ.ዓ

«የዓመተ ምሕረትህን ዙር ትባርካለህ፤ ምድረ በዳ ተራሮችም ይረካሉ፤ ኮረብታዎችም ልምላሜውን እንደ ዝናር ታጥቀው ደስ ይሰኛሉ።» መዝ.፷፬፥፲፪

ምሕዋረ–ፀሐይ ማለት ጊዜያትን በዐውደ ዕለት፤ በዐውደ ወርኅ፤ በዐውደ ዓመት ከፍሎ፤ መድበና ቀምሮ ከፍጥረት እስከ ዳግም ምጽአት ያለውን የዘመን አቈጣጠር መንገድ የሚያመለክት ሥርዓት ነው። ዐውደ ዕለት ማለት ሰባት ቀን፤ ዐውደ ወርኅ ማለት ፴ ቀን፤ ዐውደ ዓመት ማለትም ፫፻፷፭ ቀን ነው።

ሙሴ ዓመተ አዳምን መሻሻ በማድረግ የማየ አይኅን ታሪክ ሲጽፍ እንዲህ ይላል። በኖኅ ዕድሜ በስድስት መቶ ዓመት በሁለተኛው ወር ከወሩም በ፲፯ኛው ቀን ማየ አይኅ ዘንም ፩፻፶ ቀን ከቆየ በኋላ ውሃው ጐደለ። መርከቢቱም በሰባተኛው ወር ከወሩም በ፲፯ኛው ቀን በአራራት ተራራ ላይ ዐረፈች ይላል። (ዘፍ. ፯፥፲፩፣ ፰፥፫–፬)

ሁለተኛው ወር የተባለው ግንቦት ሲሆን ሰባተኛው ወር ደግሞ ጥቅምት ነው። ከግንቦት ፴ ቀን ፲፯ ሲቀነስ ፲፬ ይተርፋል። ከሰኔ እስከ መስከረም ያለው ቀን ሲቈጠር ፩፻፳ ይሆናል። በዚህ ሁሉ ላይ ከጥቅምት ፲፯ ቀን ቢደመርበት ፩፻፶ ቀን ይሆናል ይህ በዐውደ ወርኅ ሲቀመር አምስት ወር ይሆናል። የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት ዐውደ ወርኅ ፴ ቀን ነው የሚሉት ይህን ሙሴ የጻፈውን ያምስት ወር ቀመር መሠ ረት በማድረግ ነው። ዐውደ ዕለት ሰባት ቀን ነው የሚሉትም ሃያ ሁለቱ ሥነ ፍጥረት የተፈጠሩባቸው ሰባቱ ዕለታትን መሠረት በማድረግ ነው።

የፀሐይ ዐውደ ዓመት ፫፻፷፭ ቀን ነው ብለው የወሰኑበት ምክንያትም እንዲህ ነው። «ወገብረ እግዚአብሔር ክልኤተ ብርሃናተ ዐበይተ ዘየዐቢ ብርሃን ከመ ይምልክ መዓልተ፤ ወዘይ ንእስ ብርሃን ከመ ይምልክ ሌሊተ ምስለ ከዋክብት» (ዘፍ.፩፥፲፮) ተብሎ እንደ ተጻፈው፤ ፀሐይ ምግብናውን ለመፈጸም በአሥራ ሁለቱ ወሮች የሚታይባቸው አሥራ ሁለት ኅዋኅወ ፈለክ አሉ። «እስመ ረሰዩ ጉልቈ አውራኂሆሙ ዐሠርተ ወክልኤተ ኅዋኅወ ፈለክ ዘፈጠሮሙ እግዚአብሔር ልዑል ወሤሞሙ ውስተ ጠፈረ ሰማይ እንዲል (አቡሻክር፥ አንቀጽ ፬)

ስለዚህ ፀሐይ በአሥራ ሁለቱ ኅዋኅወ ፈለክ አርእያና አምሳል በተሠሩ አሥራ ሁለቱ ወሮች እየተመላለሰ የሚያበራበት ጊዜም እንዲህ ነው። በደቡብ ዋልታ በሚገኘው መዠመርያው ኖኅተ ፈለክ (የፈለክ ደጃፍ) በጥር ወር በ፴ መዓርጋት ልክ ፴ ቀን ያበራል። ይህም ጥንተ ማኅፈድ ይባላል። «አሠርቱ ወክል ኤቱ ማኅፈዳተ ፀሐይ» እንዲል መጽሐፈ ምሥጢር።

በሁለተኛው ኖኅተ ፈለክ በየካቲት ወር፤ በሦስተኛው ኖኅተ ፈለክ፡ በመጋቢት ወር፤ በአራተኛው በሚያዚያ፤ በአምስተኛው በግንቦት፣ በ7ኛው ኖኅተ ፈለክ በሰኔ ወር በ፴፣ በ፴ መዓርጋት (ዲግሪዎች) ልክ ፴ ቀን ያበራል።

ከጥር እስከ ሰኔ ፮ ወር ነው። በስድስቱ ወሮች ያበራበት ቀን ብዛት ፩፻፹ ይሆናል።

ዳግመኛም ፀሐይ ከጥር እስከ ሰኔ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ባበራበት ሥርዓት መሠረት እንዲሁም ከሰሜን ዋልታ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ዙሮ በእያንዳንዱ ኖኅተ ፈለክ በሚገኙት ፴ መዓርጋት ልክ ከሐምሌ እስከ ታኅሣሥ ባሉት ወሮች ፴፣ ፴ ቀን ያበራል። ከሐምሌ እስከ ታኅሣሥ ፮ ወር ነው። በስድስቱ ወሮች ያበራበት ቀን ብዛት ፩፻፹ ነው።

ስለዚህ:-

ከጥር እስከ ሰኔ ያበራበት ቀን ብዛት . . . . . ፮ X ፴=፩፻፹

ከሐምሌ እስከ ታኅሣሥ ያበራበት ቀን ብዛት ፮ X ፴=፩፻፹

ድምር ፫፻፷

፫፻፷ ቀን ይሆናል።

በዚሁም ውስጥ ከያንዳንዱ ወር የሚተርፉ የጊዜ ክፍልፋዮች አሉ። እነዚህም ሲደመሩ ፫፻፲፭ ኬክሮስ ይሆናሉ። ይህ ድምር በ፷ ኬክሮስ ሲቀመር ፭ ቀን ከ፲፭ ኬክሮስ ይሆናል። ይህ በ፫፻፷ ቀን ላይ ሲደመር ፫፻፷፭ ቀን ከ፲፭ ኬክሮስ ይሆናል። የፀሐይ ዐውደ ዓመት ፫፻፷፭ ቀን ከ፲፭ ኬክሮስ ነው የሚባለውም ስለዚህ ነው።

ከቀዳማይ አዳም እስከ ዳግማይ አዳም ያለው ዘመን በፀሐይ ዐውደ ዓመት ሲሰፈርና ሲቈጠር ፭ ሺህ ፭፻ ዓመት ይሆናል። ይህም ዓመተ ፍዳ፤ ዓመተ ፋሲካ ዘመን ብሉይ ይባላል።



www.ethiopianorthodox.org

ከጌታችን ልደት ወዲህ ያለው ዘመን ሲቈጠር ፲፱፻፺፫ ዓመት ይሆናል። ይህም ዓመተ ምሕረት፣ ዓመተ ሥጋዌ ዘመነ ሐዲስ ይባላል። ዓለም ከተፈጠረ ዠምሮ እስከ ዛሬ ያለው ዘመን ቢቈጠር ፯ ሺህ ፬፻፺፫ ዓመት ይሆናል ይህም ዓመተ ዓለም መዋዕለ ዓለም ይባላል። ፯ ሺህ ፬፻፺፫ ዓመት በ፭፻፴፪ ዐቢይ ቀመር፣ በ፲፱ ንኡስ ቀመር ሲቀመር ፲፬ ዐቢይ ቀመር፣ ፪ ንኡስ ቀመር ሆኖ ፯ ዓመት ይተርፋል። ፯ቱ ዓመት ዓመተ አበቅቴ ይባላል። ከ፯ቱ ዓመት አንድ ሲቀነስ ፮ ወንበር ይገኛል። በተገኘው ወንበርም የዘመኑ አበቅቴና መጥቅዕ ይታወቃሉ። አበቅቴ ማለት ተረፈ ዓመት ማለት ሲሆን በተገኘው የዓመቱ አበቅቴ ሠርቀ ሌሊትና ሠርቀ ወርኅ ይታወቃል ጥንተ አበቅቴ ፲፩ ነው። በተገኘው ፮ ወንበር ተባዝቶ ለ፴ ሲካፈል ፪ ወር ሆኖ ፮ ይተርፋል። ይህ የዘንድሮ አበቅቴ ነው። መጥቅዕ አዋጅ የሚነገርበት ነጋሪት ወይም መለከት ማለት ነው። የተገኘው መጥቅዕ ከዕለታት ተውሳክ ጋር እየተደመረ መባጃ ሐመርን ያስገኛል። መባጃ ሐመር ማለት አጽዋማት በዓላት የሚውሉበትን ቀን የሚያመለክት ሐረግ ነው። ጥንተ መጥቅዕ ፲፱ ነው።

ይህ በተገኘው ፮ ወንበር ተባዝቶ ለ፴ ሲካፈል ፪ ወር ሆኖ ፳፬ ይተርፋል። ይህ የዘንድሮ መጥቅዕ ነው። ስለዚህ የ፲፱፻፺፫ ዓ.ም አበቅቴ ፮፣ መጥቅዕ ፳፬፣ ወንጌላዊው ማቴዎስ፣ ጥንተ ቀመር ፯፣ ጥንተዮን ፮ ዕለተ ዮሐንስ ፪ ይሆናል።

በኢይወርድና በኢየዓርግ ሕግ መሠረት የሚወጡ አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበት ቀን ሁል ጊዜ የሚታወቀው በፀሐይና በጨረቃ ጥምር አቈጣጠር መንገድ ነው። ለምሳሌ ጾመ ነነዌ፣ ትንሣኤ የመሳሰሉት ሁሉ ማለት ነው። በመባቻ መንገድ ሥርዓት የሚወጡ አጽዋማትና በዓላት ግን በፀሐይ አቈጣጠር መንገድ ብቻ ነው። ለምሳሌ ጾመ ነቢያት፣ ልደት፣ ጥምቀት፣ የመሰሉ ሁሉ ነው።

ዘንድሮ ልደተ አበቅቴ ማክሰኞ ነሐሴ ፴ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም ውሏል። ከነሐሴ ፴ ቀን ፳፱ ሲቀነስ ፩ ቀን ይተርፋል። በ፩ ቀን ላይ ፭ ጳጉሜን ሲደመርበት ፮ ቀን ይሆናል። በ፮ቱ ቀን ላይ ከመስከረም ፲፰ ቀን ሲደመር ፳፬ ቀን ይሆናል። ይህ የጨረቃ መስከረም ወር ነው። የጨረቃ ወር አንድ ጊዜ ፳፱ ቀን፣ አንድ ጊዜ ፴ ቀን ይሆናል የሚባለውም ስለዚህ ነው። የጨረቃ ጥቅምት መስከረም ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ይብታል። የጨረቃ ጥቅምት በባተበት ረቡዕ መስከረም ፳፬ ቀን በዓለ መጥቅዕ ይውላል። የረቡዕ ተውሳክ ፬ ነው። በዚሁ ላይ ፳፬ መጥቅዕ ሲደመር ፳፰ ይሆናል። ይህ የ፲፱፻፺፫ ዓ.ም መባጃ ሐመር ነው። በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም መስከረም ሰኞ ጥር ማክሰኞ ይብታል። ጥር በባተ በ፳፰ኛው ቀን ጾመ ነነዌ ይገባል። የካቲት በባተ በ፲፪ኛው ቀን ሰኞ ዐቢይ ጾም ይያዛል። መጋቢት ፱ እሑድ ደብረ ዘይት፣ መጋቢት ፴ ቀን እሑድ ሆሣዕና፣ ሚያዝያ ፭ ኀሙስ በዓለ ፍሥሕ ይውላሉ። ስቅለት ሚያዝያ ፮ ዓርብ፣ ትንሣኤ ሚያዚያ ፯ እሁድ፣ ረክበ ካህናት ግንቦት ፩ ረቡዕ፣ ዕርገት ግንቦት ፲፮ ቀን ኀሙስ፣ ጰራቅሊጦስ ግንቦት ፳፮ እሁድ ሲውሉ ጾመ ሐዋርያት ግንቦት ፳፯ ቀን፣ ሰኞ ጾመ ድኅነት ግንቦት ፳፱ ቀን ረቡዕ ይገባሉ።

የምድርን ትልሚን አርካው፣ መከርዋን፣ አዝመራዋን አብጀው። ጠብ ጠብ እያለ ዝናሙ ለስስ ብሎ ሲወርድ ደስ ብሏት ትበቅላለችና። መዝ.፷፬፥፲። ✣

## እሥርቆት

ሃሌ ሉያ ዮም በዘዝከር ሐሳበተ ሕጉ ወትእዛዛቲሁ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ወሐሳበተ አዝማን ዓለም ወዓመታት፤ ወሠርቀ አውራኅ ዘሌሊት ወዘመዓልት እንዘ ሀሎን በዘመን ቅዱስ ማቴዎስ ወንጌላዊ ቡሩክ ያብጽሐነ እስከ ዘመን ቅዱስ ማርቆስ ዜናዊ አሜን።

ስብዓ ወአርባዕተ ምእት ተሰዓ ወሠለስተ ዓመተ ኮነ ዓመት ዓለም፤ ወእምኔሁ ኀምሳ ወኀምስተ ምእት ኮነ ዓመት ፍዳ ዓመት ኲነኔ፤ ዐሠርቱ ወተስዓቱ ምእት ተሰዓ ወሠለስተ ዓመተ ኮነ ዓመት ሥጋዌ፤ ዮም በዛቲ ዕለት ሠረቀ ለነ ወርኃ መስከረም ቡሩክ ያብጽሐነ እስከ ወርኃ ጥቅምት ሰላመ እግዚአብሔር አሜን።

ሰሙኑ ሠርቀ ሌሊት፤ ዐሡሩ ወሰኑይ ሠርቀ ወርኅ አሚሩ ሠርቀ መዓልት ኮነ በዛቲ ዕለት አቡነ ዘበሰማያት...

# የኢትዮጵያ ንግሥት የሕንደኬ ጃንደረባ ክርስትናን የተቀበለበት ቦታ በቅድስት ሀገር

በታሪክ እንደተረጋገጠው ኢትዮጵያ ከ፪ ሺህ ፭፻፵፭ ዓመት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ጀምሮ ነጻ ሕዝብና ነጻ መንግሥት ያሏት ሀገር ናት፣ የዚህም ታሪክ መነሻ የካም ልጅ ኩሽ የወለደው ሳብታ በኢትዮጵያ የነገሠበት ዘመን ነው። ሳብታ ከጥፋት ውሃ በኋላ ከ፪ ሺህ ፭፻፵፭ እስከ ፪ ሺህ ፭፻፲፭ ቅልክ ለ፴ ዓመታት በኢትዮጵያ ነግሦአል።

ኢትዮጵያ በተከታታይ በመርዋት በካም ዘሮች ነገሥታት የተለያየ ስም ነበራት፣ ለምሳሌ:- የካም የበኩር ልጅ የኩሽ ዘሮች ስለሰፈሩባት «የኩሽ ምድር» ተብላ ትጠራ ነበር። እንደገናም በሳባ የሳባ ምድር፣ በሰብታ አቢሲኒያ በመባል ተጠርታለች (ዘፍ.፲፥፮–፯)። ከሁሉም በኋላ ለዚች ሀገር ኢትዮጵያ የሚል ስም ተሰጣት። በትውፊትና በታሪክ እንደሚነገረው የካም በኩር ልጅ ሁለት ስሞች ነበሩት፣ እነዚህም ፩ኛው ኩሽ ፪ኛው ኢትዮጲስ ነበሩ። አቅኚዎች በአባታቸው ስም «ኢትዮጵያ» ብለዋታል። ሁለተኛው «ኢትዮጵያ» የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ጠይም ማለት ነው። ይህም የሕዝቡን ኅብረ መልክዕ ያመለክታል።

በ፪ ፻፹፭ ቅልክ መጽሐፍ ቅዱስን ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ የተረጎሙ ሰብዓ ሊቃናት በዕብራስጥ «ኩሽ» የተባለውን ስም ሁሉ ኢትዮጵያ በማለት ለውጠውታል። ስለሆነም ምድረ ኩሽ እየተባለች ትጠራ የነበረችው ሀገር ኢትዮጵያ የሚለውን ስሟን አጽንታ እስካሁን ትጠራበታለች።

ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ምንም እንኳ ኅብረ ቀለምን ቢያመለክት በዚህ ስም የሚጠራ ጥንትም ሆነ ዛሬ ሌላ ሀገር ባለመኖሩ የሚያመ ለክተው የዛሬዋን ኢትዮጵያ ብቻ ነው። ከዚህ በላይ ባጭሩ እንደ ተገለጠው የኢትዮጵያ አቅኚዎች «በትውልዱ ጻድቅና ፍጹም ሰው የነበረው አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገው፣ በእግዚአብሔርም ፊት ሞገስን ያገኘው የኖኅ» የልጅ ልጆች ስለነበሩ በሕገ ልቡና እየተመሩ አያታቸው ኖኅ ያመልከው የነበረውን አንድ አምላክ ማምለክን ሳያቋርጡ እስከ ፩ ሺህ ፲፫ ዓመት ቅልክ ቆዩ።

ከ፩ ሺህ ፲፫–፱፻፹፪ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ የነበረችው የኢትዮጵያ ንግሥት ማክዳ (ንግሥተ ሳባ) በታሪክ የሰማችውን የሰሎሞንን ጥበብና ዝና ለማየትና በዘመኑ የነበረውን የኢትዮጵያን ሥልጣኔ ለማስተዋወቅ፣ የብሉይ ኪዳንንም እምነትና ትምህርት፣ ሥርዓቱንም ከመሠረቱ ለመረዳት ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም መሄድዋ በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ፲፥፩–፲፪ በዜና መዋዕል ካልእ ፱፥፩–፲፪ ተመዝግቦ ይገኛል። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ንጉሥ ሰሎሞን ለኢትዮጵያ ንግሥት ማክዳ «የወደደችውን ሁሉ ሰጣት» የሚል አረፍተ ነገር ስለሚገኝ ከሌላው ስጦታ ሁሉ ጋር በምድረ ጋዛ የጓዝ ማሳረፊያ የተለየ ቦታም በርስትነት እንደ ሰጣት በኢትዮጵያ ነገሥት ታሪክ ታትቶአል። ንጉሥ ሰሎሞን የከበረ ገጸ በረከት ከዓለም ዙሪያ ያመጡለት ለነበሩ ታላላቅ መሪዎች በበኩሉ ከሚያደርጋቸው ልዩ ልዩ ስጦታዎች አንዱ ቦታ ነበር። ለምሳሌ የጢሮስ ንጉሥ ኪራም የተለያዩ ገጸ በረከቶችን ባመጣለት ጊዜ ሰሎሞን በገሊላ ውስጥ ሃያ ከተሞችን ሰጥቶታል። (፩ነገስ.፱፥፲–፲፬)።

በዚህ መሠረት ለንግሥተ ሳባ ከላይ የተጠቀሰውን ቦታ እንደሰጣት የታመነ ነው።

መድኃኒታችንም በቅዱስ ወንጌል «የዓዜብ ንግሥት በፍርድ ቀን ተነሥታ ከዚህ ትውልድ ጋር ትፋረዳለች፣ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና» በማለት ኢትዮጵያ ቀደም ብላ እምነተ ኦሪትንና ሥርዓቱን መቀበልዋን መስክሮላታል (ማቴ.፲፪፥፵፪) ንግሥተ ሳባ በኢየሩሳሌም ቆይታዋ ቀዳማዊ ምኒልክን ፀንሳ ተመለሰች ምኒልክም ተወልዶ ካደገ በኋላ የአባቱን አገር ኢየሩሳሌምን ጎብኝቶ ሲመለስ ካህናተ ኦሪትን ከጽላተ ሙሴ ጋር እስከ ሰሎሞን ድረስ የተጻፉትንም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ይዞ መጥቷል።

ከዚያም ጊዜ ጀምሮ የብሉይ ኪዳን እምነት ከትምህርቱ፣ ከሥርዓቱና ከመዓርገ ክህነቱ ጋር ወደ ኢትዮጵያ ገብቷል። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትም ወደ ጥንታዊው የኢትዮጵያ ቋንቋ ወደ ግእዝ መተርጎም የጀመሩት ያን ጊዜ ነበር።

ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን እምነትን እንደ ተቀበለች የሚያስረዳ ታሪክ ብቻ አይደለም። እስከ ዛሬ ድረስ በሕዝቡ ዘንድ የሚታዩት ትውፊቶችም ዋና ማስረጃዎች ናቸው።

ለምሳሌ:-

- ኅርመተ መባልዕት (የምግብ ልዩነት)
- ግዝረት በስምንተኛ ቀን
- የዜማ መሣሪያዎች
- ሰንበትን ማክበር
- ክብረ ታቦት ወዘተ. ከብሉይ ኪዳን

እምነት ሥርዓት ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። ከዚህም ጋር በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ የነበራትና ዛሬም ያላት የቦታ ይዞታ ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀገሮች ሁሉ ቀድማ የብሉይ ኪዳን እምነት ባለቤት ከሆነችው ከኢየሩሳሌም ጋር የረዥም ጊዜ የእምነትና የታሪክ ግንኙነት እንደ ነበራት የሚያስረዳ ነው።

ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ፵፭ ጊዜ በላይ የተጠቀሰች ስትሆን ከክርስትና እምነት በፊት በአንድ አምላክ ታምን እንደነበርም ብዙ ጊዜ ተጠቅሳለች። ኢትዮጵያውያን ሁል ጊዜ በቃል የሚጠቅሷቸውና እጅግ የተወደዱ ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው።

«ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» (መዝ.፷፯፥፴፩)

«በፊቱ ኢትዮጵያ ይሰግዳሉ» (መዝ.፸፩፥፱)

«የእስራኤል ልጆች ሆይ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?» (አሞጽ.፱፥፯)

«ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱኝ የተበተኑት ሴቶች ልጆቼ ቍርባኔን ያመጡልኛል» (ሶፎ.፫፥፲)

ኢትዮጵያ እስካሁን ባጭሩ ለመግለጥ እንደ ተሞከረው ከ፪ ሺ.ህ ፭፻፵፭ እስከ ፱፻፹፪ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በሕገ ልቡና፣ ከ፱፻፹፪ ቅልክ እስከ ፴፬ ዓ.ም ደግሞ በሕገ ኦሪት እየተመራች አምልኮተ እግዚአብሔርን ስትፈጽም ኖራ በ34 ዓ.ም ወደ ክርስትናው እምነት ተሸጋገራለች።

ኢትዮጵያ የክርስትናን እምነት የተቀበለችው በመጀመሪያው ምእት ዓመት በ፴፬ ዓ.ም ወንጌላዊው ቅዱስ ፊልጶስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ የኢትዮጵያ ንግሥት የሕንደኬን ጃንደረባ ስለ ክርስቶስ አስተምሮና አሳምኖ ባጠመቀው ጊዜ ነው። የኢትዮጵያ ንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣን የነበረው ይህ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሕጽው (ጃንደረባ) ተብሎ ተጠርቷል። በትውፊት ግን መልከጼዴቅና ባኮስ የተሰኙ ሁለትስሞች አሉት። አንድ ሰው በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ባሉ ስሞች መጠራትም የተለመደ በመሆኑ ይህ ሰው «ጃንደረባው» መልከ ጼዴቅ ወይም ባኮስ እየተባለ ይጠራል። ጃንደረባው ወደ ክርስትና እምነት የተመለሰው ከአረማዊነት ሳይሆን በቀጥታ ከብሉይ ኪዳን እምነት ነበር። ይህንም መረዳት የሚቻለው በራሱ ቋንቋ በግእዝ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መካከል የነቢዩ ኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ በመገኘቱ ነው።

ጃንደረባው የብሉይ ኪዳን እምነት ተከታይ ብቻ አልነበረም። እንደ ሕጉም የእምነቱንም ሥርዓት የሚፈጽም ሰው ነበር። «በዓመት ሦስት ጊዜ በበዓለ ናእት፣ በበዓለ ሐምሳ፣ በበዓለ መፀለት ወንዶች ልጆችህ ሁሉ በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት እርሱ በመረጠው ስፍራ ይታዩ፤ በእግዚአብሔርም ፊት ባዶ እጃቸውን አይታዩ» (ዘዳግም ፲፮፥፲፮) በተባለው ትእዛዝ መሠረት ጃንደረባው ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም እየሄደ ለእግዚአብሔር ይሰግድ ነበር። ስለዚህም እንደ ተለመደው በበዓለ ሐምሳ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ሥርዓተ አምልኮቱን ፈጽሞ ወደ ሀገሩ በሚመለስበት ጊዜ ይህን ታላቅ ጸጋ ሊያገኝ ችሏል።

የኢትዮጵያዊው ጃንደረባና የቅዱስ ፊልጶስ ታሪክ በቅዱስ መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል። ታሪኩም ባጭሩ እንደሚከተለው ይነበባል። «የእግዚአብሔር መልአክ ፊልጶስን ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው መንገድ ሂድ አለው። እርሱም ተነሥቶ ሄደ። እነሆም የኢትዮጵያ ንግሥት የሕንደኬ አገልጋይና ጃንደረባ የነበረ በገንዘብዋም ሁሉ የሠለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር። ሲመለስም በሰረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር። ያነበውም የነበረው ክፍል ይህ ነበር:- ‹እንደ በግ ወደ መተራድ ተነዳ፣ የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል እንዲሁ አፉን አልከፈተም፤ በውርደቱ ፍርዱ ተወገደ፤ ሕይወቱ ከምድር ተወግዳለችና፣ ትውልዱንስ ማን ይናገራል?› (ኢሳ.፶፫፥፯) ፊልጶስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ወደ ሰረገላው ቀረበና ‹የምታነበውን ታስተውለ ዋለህን?› አለው። ጃንደረባውም ‹የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል?› አለው። ከዚህ በኋላ በጃንደረባው ጋባዥነት ፊልጶስ በሠረገላው ላይ ተቀመጠ፤ ፊልጶስም አፉን ከፈተ፤ ከዚህም መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ጌታችን



www.ethiopianorthodox.org

ስለ መድኃኒታችን ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት። በመንገድም ሲሄዱ ውሃ ወደ አለበት ቦታ ደረሱ፤ ጃንደረባውም ‹እነሆ ውሃ፤ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድን ነው?› አለው።

ፊልጶስም ‹በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶአል› አለው ጃንደረባውም ‹ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ› አለ። ሰረገላውም ይቆም ዘንድ አዘዘ፤ ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውሃው ወረዱ፤ አጠመቀውም፤ ጃንደረባውም ደስ ብሎት መንገዱን ሄደ» (የሐዋ.፰፥፴፮–፴፱)

ይህ በግብረ መንፈስ ቅዱስ የተመሠረተው፤ አስደሳችና እውነተኛ ታሪክ ኢትዮጵያ ከምሥራቃውያንና ከምዕራባውያን ከሌሎችም የአፍሪቃ ሀገሮች ቀድማ ከአይሁድ ቀጥላ ክርስትናን በመጀመሪያው ምእት ዓመት መቀበሏን ያረጋግጣል። ትውፊትና ታሪክ እንደሚያስረዱትም ቅዱስ ፊልጶስ ያጠመቀው ጃንደረባ በሐዋርያት ዘመን ወንጌልን ለኢትዮጵያ መስበኩ ታምኗል።

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አባት እየተባለ የሚጠራው አውሳብዮስ ሕጽው ከተጠመቀ በኋላ ወደ ሀገሩ ተመልሶ ወንጌልን ስለመስበኩ የሚከተለውን ጽፏል።

«መልእክተ እድገና በየቀኑ ሩቅ ወደ ሆኑት ሀገሮች ሁሉ እየተስፋፋ ሳለ ፈቃደ እግዚአብሔር በሴት (ንግሥት ሕንደኬ) ትመራ ከነበረችው ሀገር ከኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች አንድን አመጣ። ይህ ሰው ከእስራኤላውያን ቀጥሎ ከወንጌላዊው ቅዱስ ፊልጶስ የመለኮታዊውን ቃል ምሥጢር በአስተርእዮ ለመቀበል ቀዳማዊ ነበር። ከዓለም ምእመናን ቀዳምያት (የመጀመሪያ ፍሬ) ነበር። ይህ ሰው (ጃንደረባው) ወደ ሀገሩ ተመልሶ ሕይወት ሰጭ የሆነውን የክርስቶስን በሰዎች መካከል መመላለስ የምታሳውቀውን ወንጌል ለመስበክ የመጀመሪያው ሰው እንደ ሆነ ታምኗል። በእርሱም ምክንያት «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» የሚለው ስለ ኢትዮጵያውያን እውነተኛ እምነትና እምልኮት የተነገረው ትንቢት ተግባራዊ ፍጻሜን አግኝቷል። (አውሳብዮስ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፪ኛ መጽሐፍ ፲፫)

ሌሎች የሐዲስ ኪዳን መተርጉማንም «ደስ ብሎት ወደ ሀገሩ የተመለሰው ጃንደረባ የተገኘውን አዲስ ደስታ ለርሱ ብቻ እንደማ ያደርግ ሮማጦኞች ነን።» በማለት ስለ ጃንደረባው ሰባኬ ወንጌልነት የሰጡት መስክርነት ዘወትር ይነበባል። (The Daily Study Bible By William Barcily The Acts of the Apostles 8:26-40)

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትም ጃንደረ ባው ወደ ሀገሩ ተመልሶ ለወገኖቹ ወንጌልን እንደ ሰበከና ክርስትናን እንዳስተዋወቀ ስለ ጃንደረባው በደረሱት ድርሰት ገልጠዋል። ይህም እንደሚከተለው ይነበባል:-

«በርስትህ በኢትዮጵያ በአትራቢያዋ በኖብያ፤ በአሉድያ፤ ዳግመኛም እስከ ናፓታና ሰባ ድረስ ወንጌልን ለመስበክ የዞርህ የሕንደኬና የሕዝብዋ ሹም ሆይ! በአፍራቅያ ችግር እንዳይኖር ጠብታት እያልህ ወደ ጌታህ ጸልይ» (ስለ ሕጽው መዝሙር)

በዚህ አረፍተ ነገር መሠረት ጃንደረባው ለኢትዮጵያ ሰባኬ ወንጌል ብቻ ሳይሆን ስለ አፍሪቃ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር የምልጃ ጸሎት ማቅረብ የሚችል ቅዱስ እንደሆነ ይስተዋላል።

በተጨማሪም እነዚሁ ብሔራውያን ሊቃ ውንት:- ኢትዮጵያውያን የቅዱስ ፊልጶስን ትምህርትና ስብከት ከጃንደረባው ሰምተው ክርስቶስን ማመናቸውን ሲገልጡ እንዲህ ብለዋል።

«...መጥምቁና የወንጌል ሰባኪው ሐዋርያ ፊልጶስ ሆይ! ኢትዮጵያውያን ትምህርትህን ከብልሁ ጃንደረባ ሰምተው ለድንግል ማርያም ልጅ ይሰግዳሉ...» (ስለ ሕጽው መዝሙር)

በዚህም አገላለጥ መሠረት ጃንደረባው በመንፈስ ቅዱስ ከተላከለት አስተማሪው ከቅዱስ ፊልጶስ የተማረውን ትምህርት ለኢትዮጵያውያን በማስተማሩ ዳዊት በመዝሙሩ ፸፩፥፱ «በፊቱም ኢትዮጵያ ይሰግዳሉ» ሲል የተናገረው ትንቢት እንደፈጸመ ይታያል።

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ» ብሎ እምነቱን በመግለጡና በማረጋገጡ «ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በሚያምን ሁሉ እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል፤ እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራል» (፩ዮሐ.፬፥፲፭) የሚለው አምላካዊ ተስፋ የተፈጸመለት እውነተኛ አማኝ ነበር።

ሕጽው የተንተየ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን በምታጠምቅበት ጊዜ ትጠቀምበት ለነበረው ሥርዓተ ተአምኖ ጀማሪ መሆኑ ይነገርለታል። ሥርዓቱም የሚከተለው ነው።

አጥማቂው:- «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምናለህን?»

ተጠማቂው:- «አዎ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ»

ይህ ሥርዓት ከወንጌላዊው ፊልጶስና ከጃንደረባው ንግግር ጋር ስለሚተባበር ከዚሁ እንደተወሰደ ይታመናል (የሐዋ.፰፥፴፯)

ወንጌላዊው ፊልጶስና ጃንደረባው በምን ቋንቋ እንደ ተነጋገሩ የግብረ ሐዋርያት አንባቢዎች ሁሉ ለማወቅ እንደሚፈልጉ ግልጥ ነው። ድርጊቱ የተፈጸመው በ፴፬ ዓ.ም በተከበረው በበዓለ ሐምሳ ሰሞን እንደሆነ በሐዲስ ኪዳን ተገልጦአል። ስለዚህ ወንጌላዊው ፊልጶስ በበዓለ ሐምሳ ዕለት ከቅዱሳን ሐዋርያት ጋር ስለነበር መንፈስ ቅዱስ በሀገሩ ሁሉ ቋንቋ የመናገር ስጦታን መቀበሉ የታመነ ነው። ስለሆነም ጃንደረባው በራሱ ቋንቋ በግእዝ መጽሐፈ ኢሳይያስን በሚያነብበት ጊዜ ፊልጶስ ሊሰማውና ሊያነጋግረው ችሏል። ስለዚህ ፊልጶስና ጃንደረባው የተነጋገሩበት ቋንቋ የኢትዮጵያ ቋንቋ ግእዝ ነበር።

ከጃንደረባው ቀጥሎም ቅዱስ ማቴዎስ በኢትዮጵያ ወንጌልን መስበኩ በጥንት የቤተ ክርስቲያን ጸሐፊዎች በእነሩፊኖስና ሶቅራጥስ ተመስክሮአል።

ከዚህ በኋላ በ፫፻፴ ዓ.ም በትውልዱ ጢሮሳዊ፤ በዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የነበረው ቅዱስ ፍሬምናጦስ በኢትዮጵያ ንጉሥ በኢዛና ፈቃድና ትእዛዝ ወደ እስክንድርያ ተልኮ በ፳ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ በቅዱስ አትናቴዎስ ጳጳስነት ተሹሞ ተመለሰ ያን ጊዜም በጃንደረባው ተሰብኮ የነበረው የክርስትና ሃይማኖት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ሆነ። ቤተ ክርስቲያኒቱ በመንበረ ጵጵስና ተቋቁማ ከጊዜ ወደ ጊዜ ዕድገትዋን እያሳየች ዛሬ ካለችበት ደረጃ ደርሳለች።

ኢትዮጵያ በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌም ያላት ታሪክ ከዚህ በላይ በቅደም ተከተል እንደ ተነገረው ሲሆን ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የተጠመቀበት ምንጭ በፍኖተ ጋዛ እንደሚገኝ በግብረ ሐዋርያት በ፰፥፳፮–፵ ተጠቅሶአል። ይህንም ምንጭ ክርስቲያኖች የፊልጶስ ምንጭ እያሉ ሲጠሩት በአካባቢው የሚኖሩ ዐረቦች ደግሞ «ዐይን ዲሩ» ብለው ይጠሩታል። ኢትዮጵያ ከምሥራቃውያንና ከምዕራባውያን ሁሉ በፊት ክርስትናን የተቀበለችበት ታሪካዊ ቦታ ምንጩ ያለበትና አካባቢው ስለሆነ ከጥንት ጀምሮ ኢትዮጵያውያን አባቶች በዚህ ቦታ ላይ ገዳምና ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት ሲያስቡና ሲመኙ ኖረዋል።

በዚህ መሠረት ይህን የታሪክ ፈለግ በመከተል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፤ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፤ ወእጨጌ ዘመንበረ ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ኢትዮጵያ በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌም ያላትን የታሪክ ይዞታ ለመጠበቅ፤ ለማጠናከርና ለማስፋፋት በየጊዜው ጥረት ከማድረግ ተቆጥበው አያውቁም።

ከዚህም ጥረታቸው የተነሣ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ባኮስ በተጠመቀበት በፍኖተ ጋዛ በሚገኘው ቦታ ላይ በጃንደረባው በባኮስና በወንጌላዊው ፊልጶስ ስም ገዳምና ቤተ ክርስቲያን፤ በምድረ እስራኤል የሚኖሩ የኢትዮጵያውያን ልጆችም የሚማሩበት ትምህርት ቤት ለመሥራት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የሚፈልግ መሆኑን ገልጠው ለእስራኤል መንግሥት ባለሥልጣኖች ባቀረቡት ተደጋጋሚ ጥያቄ መሠረት ጃንደረባው የተጠመቀበት ትክክለኛ ቦታ የት ላይ እንደሆነ በቅድሚያ መጠናት ይገባዋል የሚል መልስ በእስራኤል መንግሥት ባለሥልጣኖች መስጠቱ የሚታወስ ነው። ከዚህ በኋላም ጥናቱ ቀጥሎ የፊልጶስ ምንጭ በመባል የሚታወቀው ጃንደረባው ባኮስ የተጠመቀበት ትክክለኛ ቦታ (EIN-HANIYE) በግለሰብ ይዞታ መሆኑ ተረጋግጦአል። ይህንኑ ቦታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የራስዋ ይዞታ ለማድረግ ከግለሰቡ እጅ ከመግዛት በቀር ሌላ አማራጭ እንደሌለ ተገንዝባለች። ቦታውን ለመግዛትም በሀገሩ ሕግ መሠረት የገንዘቡ መጠን በእኃዝ ተወስኖ ለመክፈል ተስማምታለች።

ስለዚህ በቅድስት ሀገር ውስጥ በፍኖተ ጋዛ የሚገኘው ጃንደረባው ባኮስ የተጠመቀበት የቅድስና ቦታ ከኢየሩሳሌም ቀጥሎ ከምሥራቃውያንና ከምዕራባውያን፤ ከሌሎችም የአፍሪካ አህጉር በመቅደም በክርስትና ሃይማኖት ቅድምናዋን በጉልህ የምታስመሰክርበት ስለሆነ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ በጥብቅ ሊያስብበትና ድጋፍ ሊሰጥበት የሚገባ ነው። ግዴታውም መሆን አለበት። የዚህም ቅዱስ ቦታ የታሪክ ይዞታ ብሔራዊ እንጂ ግላዊ ባለመሆኑ አንድ ክፍልን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊሳተፍበት ይገባዋል። የቦታው ይዞታ አፍሪቃዊ ስለሆነ እንኳን ኢትዮጵያዊ የሆነ የአፍሪካ ተወላጅ የሆነ ጥቁር ሕዝብ ሁሉ ሊያስብበትና የሚችለውን ርዳታ ሁሉ ሊያደርግ ይገባዋል።

እንግዲህ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፤ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፤ ወእጨጌ ዘመንበረ ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ቀደም ብሎ እንደተገለጠው አሳባቸውና ጥረታቸው ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ተሳክተውላቸው ቦታውን ለመግዛት ከባለ ይዞታው ጋር ባደረጉት ስምምነት መሠረት የተጠየቀውን ከፍተኛ ገንዘብ ለማሟላት የቤተ ክርስቲያኒቱን ተከታዮች ምእመናንን በማስተባበር ላይ ይገኛሉ።

ስለዚህ ይህች ጥንታዊትና ታሪካዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በፍኖተ ጋዛ በሚገኘው ጃንደረባው በተጠመቀባት ቦታ ላይ ለመሥራት ስላቀደችው ገዳም፤ ቤተ ክርስቲያንና ትምህርት ቤት በጎ ፈቃድና ፈላጎት ካላቸው የወዳጅ አገሮች አበያተ ክርስቲያናት፤ በጎ አድራጊ ድርጅቶችና ግለሰቦች ሁሉ ርዳታና ድጋፍ መጠየቅ ግዴታና አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ✝

# ዘሠኑ ጽጌ



ተንሥኢ ንግሥ ሕፃን ወእሞ ወሑር ውስተ ምድረ–እስራኤል እስመ ሞቱ እለ የኃሥሥዋ ለነፍስ ዝ ሕጻን።

«የሕፃኑን ነፍስ የሚሹ ሞተዋልና ተነሣ ሕፃኑን፤ እናቱንም ይዘህ ወደ ምድረ እስራኤል ተመለስ። ማቴ.፪፥፳። ይህንን ቃል ከማተታችን በፊት ለዚሁ ቃል መነሻ የሆነን የዘመነ ጽጌ ታሪክ በአጭሩ እንመልከት።

ዘመነ ጽጌ የሚባለው በአንደኛው ክፍለ ዓመት በዘመነ መጸው ውስጥ የሚገኝ ከመስከረም ፳፮ እስከ ኅዳር ፮ ቀን ያለው ጊዜ ነው።

ጽጌ ማለት አበባ (ውበት፤ ደም ግባት) ማለት ሲሆን ጸገየ ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ (የወጣ) ቃል ነው።

ዘመነ ጽጌ ዝናምና ወጨፎ፤ ዶፍና ጐርፍ፤ መብረቅና ነጐድጓድ፤ የሚፈራረቁበትን የክረምት ወራት አልፎ ሣር በል የሆኑ የቤትና የዱር እንስሣት ለምለም ሣር ነጭተው በደስታ የሚቦርቁበትና የሚፈነጩበት፤ ምድር በአበቦች ተውባ (አጊጣ) ደመናው ከሰ ማይ ተወግዶ ሰማይ በከዋክብት አሸብርቆ የሰው ልጆችም ይህንን በማየት እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ደስ የሚሰኙበት የአበባ ወቅት ነው።

ይህንኑ በውስጡ ፵ ቀናትና ፮ ሳምንታትን ያለው ዓቢይ የምሥጋና ወራት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት፡-

፩. የዘመናት ባለቤት እግዚአብሔር (መዝ.፷፬፥፲፩–፲፫) ዘመነ ክረምቱን አሳልፎ የደስታና የመልካም ምኞት መግለጫ በሆኑ አበቦች ወደ አሸበረቀው አዲስ ዓመት በማድረሱ የቅዱስ ያሬድ የክብር መገለጫ በሆኑ ሊቃውንት «ኃለፈ ክረምት፤ ቆመ በረከት ተሠርገወት ምድር በሥነ ጽጌያት»፤ ክረምት አለፈ፤ በረከት ተተካ፤ ምድርንም በአበቦች አስጌጠች እየተባለ የሚመሰገንበት፤

፪. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ

ወደ ግብፅ መሰደዳቸውና በስደት መከራ ማየታቸውን የምናስብበት ከድንግል ማርያም በረከት የምናገኝበት፤ ፈጣሪያችንን የምናመ ልክበት ነው። በዚሁ ወቅት የሚዘመረውና የሚነበበው የእግዚአብሔር ቃልም፡-

ሀ. በመጀመሪያ ሳምንት፡- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሙሽራና በጐ መዓዛ ባለው የገነት አበባ – ማር.፪፥፲፱፤ ዮሐ.፫፥፳፱፤ ማቴ.፱፥፲፭።

ቅድስት ድንግል ማርያምና ቤተክርስቲያን በሙሽሪትና ሠናይ መዓዛ ባለው ገነት መኃ.፬፥፰–፲፭።

ለ. በሁለተኛው ሳምንት፡- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መዓዛ ቅዱሳን ስለመሆኑ፤ «መዓዛሆሙ ለቅዱሳን ከመ ጽጌ ደንጐላት»

የቅዱሳን መዓዛ እንደ ሱፍ አበባ ነው። «እንዲል ቅዱስ ያሬድ (መዝሙር ዘጽጌ)

ሐ. ሦስተኛው ሳምንት፡- እግዚአብሔር በሥነ ፍጥረቱ ገናና ሥራና፤ በቸርነቱ ስለመ መስገኑ «ሰማየ ወምድረ ዘአንተ ፈጠርከ፤ ጸሐየ ወወርኃ ዘአስተዋደድከ፤ በከዋክብት ሰማየ ዘከለልከ ወበጽጌያት ምድረ አሠርጎከ ወመኑ መሐረ ዘከማከ» እንዲል ቅዱስ ያሬድ

መ. አራተኛው ሳምንት፡- ወርኃ ክረምቱን አሳልፎ የተዘሩትን አዝርዕት፤ የተተከሉትን አትክልት የምድረ በዳውን ዕፀዋት ሁሉ ለአበባና ለፍሬ ስለማብቃቱ፤

ሠ. አምስተኛው ሳምንት፡- ሰማይን በከዋክብት ምድርን በአበቦች ስለማስጌጡ ዘፍ.፩፥፲፮፤ «አሠርገወ ሰማየ በከዋክብት ወምድረ በሥነ–ጽጌያት» (ድጓ)

ረ. ስድስተኛው ሳምንት፡- ንጉሥ ሰሎሞን ጌዚያ ሁሉ ክብሩ የአንዲት አበባ ያህል አለመዋቡ ማቴ.፮፥፳፱፤ መክ.፪፥፬–፲፩። እያሰብን የምናመሰግንበት ነው።

ስለ ወርኃ ጽጌ ምንነትና በወርኃ ጽጌ ስለሚፈጸመው መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲት እንደሆነ በአጭሩ ተገልጿል።

በማቴዎስ ወንጌል ም.፪፥፳ ላይ «የሕፃኑን ነፍስ የሚሹ ሞተዋልና ተነሣ፤ ሕፃኑን እናቱም ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ተመለስ» ይላል። ይህንን ቃል የተናገረው መልአከ እግዚአብሔር ሲሆን የቃሉ ተቀባዩም ቅዱስ ዮሴፍ ነበረ። በተጠቀሰው ምዕራፍ ቁጥር ፲፫ እንደምናነበው የጌታ መልአክ በሕልም ለዮሴፍ ታይቶ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ፤ ሕፃኑን እና እናቱንም ይዘህ ወደ ግብጽ ሽሽ ብሎት ነበረ።

ቅዱስ ዮሴፍም ሕፃኑንና እናቱን ይዞ ወደ ምድረ ግብጽ ተሰደደ (ሸሸ) በግብጽ አገር ፫ ዓመት ከ፮ ወር ከተቀመጠ በኋላ ነበር «ሕፃኑን እናቱንም ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ተመለስ (ሂድ) የሚል ትዕዛዝ የደረሰው።

ቅዱስ ዮሴፍ ሕፃኑንና እናቱን ይዞ ለምን ወደ ግብጽ ሄደ (ተሰደደ)?

ግብጽ በሰሜን አፍሪቃ የምትገኝ ከክርስቶስ ልደት በፊት አምልኮተ ጣዖት የተስፋፋበት አገር ነበረች። የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍም በወንድሞቹ ምቀኝነት ለግብጻውያን ነጋዴዎች በ፴ ብር ተሸጦ (ዘፍ.፴፯፥፲፪–፴፮)

በፈርዖን ቤተ መንግሥት እግዚአብሔር በሰጠው ልዩ ጥበብ ተወዳጅነት በማግኘቱ በአሁኑ አነጋገር የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር የሆነባት። (ዘፍ.፵፩፥፴፯–፵፰) አባቱ ያዕቆብ ከእነልጆቹ በረሐብ ምክንያት ተሰዶ ሥጋዊ ሕይወቱን ያተረፈባት። ከግብጻውያን ነገሥታት አምባገነናዊ አገዛዝ የእስራኤል ልጆች በባርነት ፍዳቸውን ያዩባት። እግዚአብሔር «እግዚአብሔርን አላውቅም እስራኤልንም አልለቅም» ባለው ልበ ደንዳናው ፈርዖን ላይ ከንዱን የዘረጋባት አገር ናት። (ዘፍ.፵፰፥፩–፳፩፤ ፵፮፥፩–፯፤ ዘጸ.፩፥፲፩፤ ፰፥፳–፳፱)።

አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን የማ ይሆኑትን እንሆናለን፤ በማለት የእግዚ አብሔርን ትዕዛዝ በመዘንጋት፤ የፈጣሪያ ቸውን ትዕዛዝ ተጻራሪ በመሆን ከማህበረ እጋንንት በመደባለቅ፤ ምሳሌ የሌለው ብርሃናዊ መንግሥታቸው ተነጥቀው ሕይወታ ቸውን በሞት ተለውጦ፤ በሐፍረትና ፍርሐት ተውጠው፤ በሥቃይ እሳት እንደ ሻማ እየቀለ ጡ የሰቀቀን ጽዋ እየጨለጡ የወረደባቸውን የመከራ ዶፍ በመሳቀቅ የቅጠል ግልድም በመታጠቅ ከቅጠል ውስጥ ተሸሸገው (ዘፍ.፫፥፩–፲፪) ስለ ነበረ፤ ቸርነት የባሕርዩ የሆነ እግዚአብሔር፤ «ልጅ ልጃቸው ተወልዶ እነርሱን ያሳተ እባብ ተብሎ የተገለጸው ሰይጣን (ዘፍ.፫፥፩) ሄኖክ ራሱን ቀጥቅጦ ካሉበት የመከራ ጉዞና የጨለማ ኑሮ ነጻ እንደሚያወጣቸውና ወደ ነበሩበት ቦታ እንደሚመልሳቸው በተናገረው የማይለወጥ ቃሉ እነሆ የማዳን ዘመኑ ሲደርስ ከድንግል ተወለደ። ገላ.፬፥፬፤ ሉቃ.፪፥፬–፯።

ፈጣሬ ሰማያት ወምድር የስደተኞች ተስፋና መጠጊያ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በማዕከለ ምድር በቤተልሔም ዘይሁዳ ሲወለድ እንስሳት ከደስታ ብዛት የተነሣ ሲዘሉ፤ እረኞች እና መላእክት በኅብረት እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ፤ በእኩይ ቀናት አዳምና ሔዋን ከፈጣሪያቸው ያስኮበለለ ሰይጣን በቅንዓት ነድዶ በምቀኝነት ተቃጠለና ለጥፋት (መልምሎ) አሰልጥኖ ያስቀመጠው አውሬው ሄሮድስ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በምቀኝነት እንዲነሣሣ አደረገ።

የአንቲፓቴር ልጅ ታላቁ ሄሮድስ ከ፴፮ ዓ.ም ጀምሮ ጻድቁ ዮሴፍ ሕፃኑንና እናቱን የዞ ወደ ግብጽ እስከ ተሰደደበት ጊዜ ድረስ የሮም ቄሣር የአውግስጦስ ወኪል በመሆን የይሁዳን ምድር ገዝቷል። ፈርሶ የነበረው የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስም ለገናናነቱ ሲል እንደገና አሠርቷል። በ፴፮ ዓመት መንግሥቱ የሚወዳት ባለቤቱና ከአብራኩ የተገኙ ለመንግሥትነት የደረሱ ልጆቹን አሳርዷል (አስገድሏል)።

ሄሮድስ የይሁዳ አገር ንጉሥ በነበረ በ፴፪ ዓመተ መንግሥቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም ዘይሁዳ ተወለደ በዚያም ጊዜ የከዋክብት ተመራማሪዎች የሆኑ ሰብዓ ሰገል ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ ሀገር ሰላም መስሏቸው ከንጉሡ ሄሮድስ ቤተ መንግሥት ገቡና ለንጉሡ እጅ ነሥተው የመጡበትን ምክንያት ሲገልጹ «የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ ዓይተን ልንሰግድለት መጥተናል» አሉት።

ሄሮድስም «የአይሁድ ንጉስ የሚለውን ቃል ሲሰማ ወኔው ተናደ፤ በሰይጣናዊ ቅናት ነደደ፤ ምክንያቱም እሱ በሚያስተዳድረው አገር ሌላ ንጉስ ተወልዶዋልና። ሰብዓ ሰገልን ሲያሰናብት ስለ ሕፃኑ በጥንቃቄ መርምሩ ባገኛችሁትም ጊዜ እኔ ደግሞ መጥቼ



www.ethiopianorthodox.org

እንድሰገድለት ንገሩኝ አላቸው» ይህ አባባል የጨና አይደለም ቀደም ሲል የግብር አባቱ ዲያብሎስ አዳምና ሔዋን ሲያባብል «ከበላችሁ እንደ አምላክ ትሆናላችሁ» ብሎ ያሳታቸው መሆኑን ያውቃል። እና ሰብዓ ሰገል ተመልሰው ከነገሩት ምን እንደሚያደርግ በልቡ ያሰበው እለ። ሰብዓ ሰገል በኮከቡ እየተመሩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አለበት ቦታ ደርሰው በጉልበታቸው በፊቱ ተደፍተው እመለኩት። ሰገዱለት ሳጥናቶቻቸውም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅና ዕጣን ከርቤም አቀረቡለት።

ሄሮድስ ግን የሕነርሱ መምጣት ሲጠባበቅ በመልአከ እግዚአብሔር አማካይነት ወደ ሄሮድስ እንዳይመለሱ ማስጠንቀቂያ ስለ ተነገራቸው ሳይመለሱ በዚያ አድርገው ወደ ሀገራቸው ሄዱ። ከዚህ በኋላ ሄሮድስ ሰብዓ ሰገልን እንደ ተሳለቁበት ባየ ጊዜ በቤተልሔም አውራጃ የነበሩትን ሁለት ዓመትና ከዚያም በታች የሆናቸው ሕፃናት ሁሉ አስገደለ። ማቴ.፪፥፲፮።

ነገር ግን ሰይፍ የተሳለበት ሕፃን፦ ከእናቶቻቸው ጉያ እየተነጠቁ በታረዱት ፩፻፵፬ ሺህ ሕፃናት መካከል አልነበረም። ያልታደለው ሄሮድስ የአይሁድ ንጉሥ የተባለው ክርስቶስ ለማስገደል እንቅልፍ አጥቶ በእረመኔነት የሐሳብ ማዕበል ሲናኝ «መልአክ በሕልም ለዮሴፍ ተነሳና ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ይዘህ ወደ ግብጽ ሂድ» ባለው መሠረት በስደት ላይ ነውና።

እዚህ ላይ መገንዘብ የሚያሻን ነገር አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሄሮድስ እርሱን ለመግደል የሚያስብ መሆኑን የማያውቅ ሆኖ አይደለም። ምክንያቱም ልብንና ኩላሊትን የሚመረምርና የሚያውቅ አምላክ ነውና ሕዝ.፲፩፥፫፤ ኢሳ.፵፮፥፲።

ነገር ግን የመላእክትን አገልግሎትና ጥበቃት ለሰው ልጆች ለመግለጽና የመጣበትን የማዳን ሥራ ለመፈጸም ነው። ተመርምሮ የማ ይደረስበት በገናናነቱና በኃያልነቱ ድካመት የሌለው ኢሳ.፱፥፮፤ ኢሳ.፵፥፳፰–፳፱፤ የነገሥታት ንጉሥ የገዥዎች ገዥ። ዳን.፪፥፵፯፤ ራእ.፲፯፥፲፬፤ ፲፱፥፲፮። ለዘለዓለ ማዊነቱ ፍጻሜና ጥንት የሌለው መዝ.፹፱፥፪ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ግብጽ የተሰደደው የሄሮድስ ሰይፍ በመፍራት ሳይሆን ራሱ በነቢያት አድሮ ያናገረውን የተስፋ ቃል ይፈጽም ዘንድ ነው።

ይኸውም፦

፩. ከቅድስት ድንግል ማርያም እንደሚወለድ (ኢሳ.፯፥፲፬)

፪. በቅድስት ሀገር በቤተልሔም አውራጃ እንደሚወለድ (ሚክ.፭፥፶፪)

፫. ቀዳማዊ አዳምን ወደ ቀድሞ ቦታው ለመመለስ ወደ ግብጽ እንደሚሰደድ (ሆሴ.፲፩፥፩) በትንቢት ተነገሮዋልና።

፬. በግብጽ የነበሩ ጣዖታትም ለማጥፋት ነው።

ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ እንኳንስ ለራሱ ይቅርና ለወዳጆቹ ሲል ያደረገውን መለኮታዊው ሥራ በእኛ አእምሮ የማይታሰብ በእኛ እንደበት ተነግሮ የማያልቅ ቢሆንም የተወሰነውን እንመልከት።

ለወዳጁ ለአብርሃም ሲል ፈርዖንና ቤተሰቡን በመቅሰፍት የቀጣ፤ (ዘፍ.፲፪፥፲፯)።

ለወዳጆቹ እሥራኤላውያን ብሎ ፈርዖንና ጋሻ ጃግሬዎቹ በተለያዩ መቅሰፍት የቀጣና የፈርዖን ሕልፈተ ሕይወት በባሕረ ኤርትራ እንዲሆን ያደረገ ዘጸ.፲፬፥፳፯–፴፩።

ለባለሟሉ ኢያሱ ሲል የገባዖንን ሰዎች ወደው እስኪጠሉ ድረስ በበረድ ቀጥቅጦ ያጠፋ ኢያሱ ፲፥፲፩።

በኤልያስ ምክንያት የአካዝን የጦር ሠራዊት በእሳት ያቃጠለ ፪፥፲፩7 ፩፤ ፱፥፲፫።

በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣ አምስት ሺህ ሰዎችን የመገበ ማር.፮፥፶፫።

በከርሠ መቃብር አራት ቀን የሆነው ሟቹ አልዓዛርን ከሞት ያስነሣ ዮሐ.፲፩፥፩–፵፮።

አዳምን በምቀኝነት ገመድ ከገነት ጉትቶ ምድረ ኩነኔ ያወረደ ዲያብሎስን «መኑ ውእቱ ዝንቱ ሥጋ ለቢሶ ዘሞአኒ» «ማነው እርሱ ሥጋን ተዋሕዶ ያሸነፈኝ» እስከሚል ድረስ ራሱ ራሱን የቀጠቀጠ አምላክ ነው።

የታሠሩትን የሚፈታ (፩ጴጥ.፫፥፲፱) በሰይጣን የተማረኩትን የሚመልስ። (ማር. ፩፥፩–፲፫) በነቢያት አድሮ ትንቢት የሚናገር (ኢሳ.፩፥፮–፯፤ ሉቃ.፬፥፲፯) ለአርባ ዘመን መና ከደመና፤ ውሃ ከዓለት በማስገኘት እሥራኤላውያንን የመገበ (፩ቆሮ.፲፥፩–፭)። በደሙ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምንከተለውና ለምናምነው ክርስቲያኖች የስደትን አስከፊነት አውቀን ፈተና በሚያጋጥመን ጊዜ «በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ኃዘንን ቢታገሥ ምስጋና ይገባዋልና ኃጢአት አድርጋችሁ ስትጐሰሙ ብትታገሡ፤ ምን ክብር አለበት? ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ብትታገሡ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል። የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና እርሱም ኃጢ አት አላደረገም፤ ተንኰልም በአፉ አልተገ ኘበትም፤ ሲሰድቡት መልስ አልተሳደበም፤ መከራም ሲቀበል አልዛተም» ብሎ ሐዋርያው እንደተናገረው (፩ኛጴጥ.፪፥፲፱–፳፫) መከራውን በመፍራት ሃይማኖታችን እንዳንክድ ይልቁንስ በሃይማኖታችን ምክንያት ግፍና መከራ ሲደርስብን ወደሌላ ሀገር መስደድ እንዳለብን ሲያስገነዝበን በአንዲቱ ከተማም መከራ ቢያሳዩአቸው ወደ ሌላይቱ ሽሹ ይላል ማቴ.፲፥፳፫። ይህንንም በተግባር ለማስተ ማርና አርአያነቱን ለማሳየት ሲል ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ ወደ ግብጽ ተሰደደ።

ነቢዩ ኢሳይያስ በም.፲፱፥፩–፪ እነሆ እግዚአብሔር በፈጣን ደመና እየበረረ ወደ ግብጽ ይመጣል የግብጽም ጣዖታት ከፊቱ ይርቃሉ በማለት እንደ ተናገረው የዓለም ሁሉ የድህነት ምክንያት የኃጥአን ተስፋ የጻድቃን ሕይወት የሆነችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሦስት ዓመት ተመንፈቅ በግብጽ በረሃ በስደት ስትንከራተት ኑራለች።

የዳዊት ልጅ ጠቢቡ ሰሎሞን «ይህች እንደማለዳ ብርሃን የምትጐበኝ እንደ ጨረቃ የተዋበች እንደ ፀሐይም የጠራች፤ ዓላማ ይዞ እንደ ተሰለፈ ሠራዊት የምታሥፈራ ማን ናት» መኃ.፮፥፲–፲፩ በማለት የፀሐይ ብርሃን ማልዳ ሲወጣ ከጠፈር በታች ያለው ፍጥረት ሁሉ ደስ እንደሚለው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከአዳም ዘር ከኢያቄም እና ከሐና እንደምትወለድ እርሷም የዓለም ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ በድንግልና እንደምት ወልደው ተገልጾላት እንደ ጨረቃ የተዋበች እንደ ፀሐይ የጠራች እያለ ንጽሕናዋን እየገለጸ ከእግዚአብሔር የተሰጣትን ክብርና ግርማ ሞገስ እያደነቀ ሲመሰክር ይታያል።

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በሉቃ. ፩፥፳፮–፳፰

ቅድስት ኤልሳቤጥ ሉቃ.፩፥፵፪ «ከሴ ቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ የማኅጸንሽም ፍሬ ብሩክ ነው በማለት ሲያወድሷት እናነባለን።

ቅዱስ ያሬድም «ይእቲ ተዓቢ እምኪ ሩቤል ወተፈደፍድ እምሱራፌል መንክር ወመድምም ዕበያ ወክብራ ለድንግል ጽሕፈት ውስተ ወንጌል ወይ.በ ርዕሳኒ አክሊል በትዕ ምርተ መስቀል» «የድንግል ማርያም ክብርዋ የጌታ መንበር ከሚሸከሙ ከሱራፌል፤ ከኪሩቤል ክብር ፈጽሞ የበለጠ ነው። ምክንያቱም በኪሩቤል፤ በሱራፌል ሲኖር በጸጋ ነው በድንግል ማርያም ግን በማኅጸንዋ አድሮ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሱዋ ነፍስ ነስቶ ስለተወለደ ክብሯ ከመላእክት ክብር የበለጠ ዕፁብ ግሩም ነው በራስዋም በመስቀል አም ሳል የተሠራ አክሊል አላት እያለ ክብርዋንና እማላጅነትዋን ገልጿል»።

ከዚህም ሌላ ራሱዋ ቅድስት ድንግል ማርያም «እነሆ ከዚያ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል (ሉቃ.፩፥፵፱) ስትል ከእግዚ አብሔር የተሰጣትን ክብር መስክራለች። በዚህም በነገደ ሴት፤ በነገደ ካም፤ በነገደ ያፌት ስትመሰገን ትኖራለች በሉቃ.፩፥፳፰ «እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው» የሚለው የመልአኩ ቃል ስናስብ እግዚአብሔር እንደማይለያት የእግዚአብሔር የክብር መገለጫ እንደሆነች እናምናለን። እግዚአብ ሔር የመረጠውና ያከበረው ማንም ማዋረድ እንደማይችል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ.፲፫፥፯ በሚገባ አስረድቷል።

ባለውለታችን እናታችን ምን ጊዜም ንዕድ ክብርት ነች እግዚአብሔር ለእርሷ የሰጣትን ክብርና የገባላትን የማማለድ ቃል ኪዳን እንኳንስ አጋንንት መላእክትም ቢሆኑ ሊቀንሱ አይችሉምና ነው።

ስለዚህ ዋስ ጠበቃችን ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች የሆነችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናትና በፍጹም ልቡና ሁነን «ፍትሕኒ እማእሰሩ ለሰይጣን እሙ ለመድኀን ወለተ ብርሃን» ማለት የብርሃን ልጅ የመድኀን እናት እመቤቴ ሆይ ከሰይጣን እሥራት ፍችኝ፤ ቅድስት ሆይ ለምኝልን እያልን ዘወትር በእማላጅነትዋ ልንማጸን ይገባናል።

«የአብ ጸጋ፤ የወልድ ቸርነት፤ የመንፈስ ቅዱስ አንድነት፤ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት፤ የመላእክት ጥባቆት፤ የነቢያት፤ የሐዋርያት የጻድቃን የሰማዕታት የአበው ፍቅር በእኔና በእናንተ ላይ ለዘለዓለሙ ጸንቶ ይኑር» ✣



# እስትጉቡእ

(እስትጉቡእ - ፕርቅም፤ የተቀመመ፤ የተሰባሰበ ማለት ነው)

## አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ኮከበ ኢትዮጵያ ወአርማንያ

በግርማ ኤልያስ

ዘመን አራት አልፎ እምነተ ክርስትና በኢትዮጵያ በተስፋፋ ማግስት ከወጣኒ ክህነት ሊቀ ጳጳሳት ከሣቴ ብርሃን አባ ሰላማ ጀምሮ እስከ ዘመናችን ድረስ ሐዋርያዊው ተልዕኮአቸውን ያለማወላወል በፍጹም እምነትና ቈራጥነት ዘመናቸውን በሞላ በመማር በማስተማር በመስበክና በማጥመቅ አብያተ ክርስቲያናትን በመትከልና ገዳማትን በማስፋፋት ታላቅ ሥራ ሠርተው ካለፉ ከታላላቆቹ የኢትዮጵያ ቅዱሳን መካከል አንዱ ርዕሰ ቅዱሳን አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ለመሆኑ በመላው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ገድሉና ተአምራቱ ተዘግቦ ይገኛል አቡነ ኤዎስጣቴዎስ በ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ በምሥራቅ ትግራይ በእንደርታ አውራጃ በዕራዕ ወረዳ ልዩ ስሟ ድርባ አቡነ አሳይ ከተባለች ቀበሌና በወይራና በጽድ ዛፎች በተሸፈነች እዋልያ ከተባለች ትንሽ ጉጥ አገር ክርስቶስ ሞአ እና ሥነ ሕይወት ከተባሉ ደጋግ ባላባቶች ተወለደ።

አቡነ ኤዎስጣቴዎስ በብዙ ስዕለትና ልመና የተወለደ የባለፀጎች ልጅ ስለሆነና እና ከመወለዱ በፊትም በቅዱስ ሚካኤል ብሥራተ ቃል የተወለደ ስለ ነበር በ፵ ቀኑ በአቡነ አሳይ ገዳም ክርስትና ተነስቶ ማእቀበ እግዚእ የሚል ስም ወጣለት ክርስቶስ ሞአና ባለቤቱ ሥነ ሕይወት በስዕለትና በብሥራተ መልአክ የወለዱት ልጃቸው ማዕቀበ እግዚእ አራሽ ገበሬ እትራፊ ነጋዴ፤ ተዋጊ ወታደር እንዲሆን ባለመፈለጋቸው እንደ ቅዱሳን አጐቶቹ እንደነ አባ ዳንኤል ዘደብረ ማርያም ቆርቆር ዘገርዓልታ ገዳም መሥራችና የብዙ ቅዱሳን ገርዓልታ አባት እንዲሆን በማሰብ ገና በሕፃንነቱ ከዕራዕ ወረዳ ወደ ገረዓልታ ደብረ ማርያም አምባ አውጥተው በጾምና በጸሎት ተወስነው በሰማይና በምድር መካከል ካለው ገደላማና ተራራማ ገዳም አቡነ ዳንኤል ውስጥ ከሚኖሩት ቅዱሳን ጋር ወስደው ቀላቀሉት።

አቡነ ዳንኤል ዘገርዓልታ የሥነ ሕይወት ታላቅ ወንድም ስለ ነበሩ ማዕቀበ እግዚእን በደስታ ተቀብሉ ከፊደል ጀምሮ ንባብ ዳዊትና ሥርዓተ ቅዳሴን ከአስተማረው በኋላ በዘመኑ ወደ ነበረው ጳጳስ ወስዶ ማዕረገ ዲቁና እንዲቀበልና ገዳሙ ደብረ ማርያምን በዲቁና እያገለገለ ሲኖር በተከታታይም ትርጓሜ ብሉያትንና ሐዲሳትን፤ መጻሕፍተ ሊቃውንትን ሁሉ ከአጐቱ ከአቡነ ዳንኤል ዘንድ በጥንቃቄና በትዕግሥት እየተማረ ሳለ ያለ እድሜው ያለ ጊዜው ጾምን፤ ስግደትን አረጋዊያን ማኅሌታዊያን ድኩማን መርዳትን አዘውትሮ ይወድ ነበር። በዚህ ገዳም ውስጥ የራሱ የሆነ የጸሎትና የስግደት ቦታ ከአለት ፈልፍሎ በማነጽ ገዳማዊ ገድሉን ቀጠለ ማዕቀበ እግዚእ ገና ፲፫ ዓመት ሳይሞላው መንፈስ እግዚአብሔር መነኮሳዊ ለመሆን ገፋፋውና አጐቱ አቡነ ዳንኤልን አስፈቅዶ በአጐቱ እጅ በደብረ ማርያም ገዳም መነኮሰ፤ በመነኮሰበት ገዳም በደብረ ማርያም መነኮሲያም ዲያቆንም ሆኖ ሲያገለግል እድሜው ወደ ፴ ዓመት ሲጠጋው በዘመኑ ወደ ነበረው ጳጳስ ሄዶ መዓርገ ክህነት ተቀበለ።

እነታትሎም እድማያተ ኢትዮጵያን በይበልጥም እድማያተ ትግራይን እየዞረ ወንጌለ ክርስቶስን ሲያስተምር እግረ መንገዱንም አዳዲስ ገዳማትን እየመሠረተ በምግባር፤ በሃይማኖት፤ በትምህርትና በትዕግሥት፤ በጾሎትና በስግደት የሚመስሉትን ደቀ መዛሙርቶች እየመረጠና እያስተማረ ብዙ ቅዱሳንን አፈራ በዚህ መንገድ አስተምሮና አመንኵሶ ቀቅድስና ካበቃቸው ቅዱሳን መነኮሳት መካከል ዋና ዋናዎቹ አባ አብሳዲ፤ አባ መርቆሬዎስ፤ አባ ማትያስ፤ አባ በኪሞስ፤ አባ ገብረ መስቀል፤ አባ ጴጥ ወንጌል፤ አባ ገብረ እየሱስ፤ አባ ማትያስ፤ አባ ገብረ ኢየሱስ አባ ማትያስ ምቁረ ልሳን ዘግብጽ፤ አባ ፊቂጦር፤ አባ ማርቆስ፤ አባ ማቴዎስ የተባሉ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ እነዚህ ቅዱሳን መነኮሳት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ወደር የሌለው ሐዋርያዊ ተልዕኮ ፈጽመው በሞላ ኢትዮጵያ ተሰራጭተው ብዙ ሐይት የማይነጥፍ የእባይ ምንጭ ሆኖ እንደ ኖረ ሁሉ ደቂቀ ኤዎስጣቴዎስም በደረሱባቸው አህጉራተ ኢትዮጵያ ሁሉ አዳዲስ ገዳማትን እየመሠረቱ ምን ጊዜም የማይነጥፍ መንፈሳዊ ትምህርት የሚሰጥባቸው ታላላቅ ገዳማትንና አድባራትን መሥርተው አልፈዋል።

አቡነ ኤዎስጣቴዎስ በሕይወት ዘመኑ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ከመሠረታቸው ታላላቅ እና ጥንታውያን ገዳማቶቹ መካከል ሰባት ዓመት የኖረበት ደብረ ፀራቢ ዘእንደርታ፤ ሰባት ዓመት የኖረበት ገዳም ዘአቡር ዘመንበርታ፤ ሰባት ዓመት የኖረበት ገዳም ሽማና ዘእንደርታ፤ ሰባት ዓመት የኖረበት ገዳም ማይ ቈርቈር ዘሰሐርቲ፤ አስር ዓመት የኖረበት ገዳም ደብረ በርበሬ ዘአምባ ሠናይቲ፤ ሰባት ዓመት የተቀመጠባት ገዳመ ደብረ ማርያም ዘቈሃይን ሲሆን በነዚህ ገዳማት በኖረበት ዘመናት ሁሉ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ቅዱሳን መነኮሳትን አስተምሮና አመንኵሶ ለቅድስና ካበቃ በኋላ በአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ ከተላከው ግብፃዊ ጳጳስ አቡነ ያዕቆብ እስከነ ደቀ መዛሙርቶቹ እስከ ምዕዋ ድረስ ሄዶ ከተቀበለ በኋላ ስለ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት ምስጢረ ሥላሴ ሥርዓተ ሃይማኖት ተነጋግረው ልብ ለልብ በመግናኘታቸውና ከጳጳሱ ጎን ለጎን በበቅሎ ተቀምጦ ሲጓዝ የተመለከቱ አብረውት ይኖሩ የነበሩ መነኮሳት ገና ለገና ጳጳሱ ኤጲስ ቆጶስ ያደርገዋል ብለው በመስጋታቸውና ቅናትና ምቀኝነት ስለ አደረባቸው በጠባብዋ ጉጅ ውስጥ እንዳለ በድንጋይ ቀጥቅጠው ሊገድሉት ሞከሩ።

ነገር ግን ገና ሳይወነስ አብሳሪ ልደት ሆኖ ወላጆቹን ያጽናና የነበረ ረዳኤ ምንዱባን ቅዱስ ሚካኤል በራእይ ተገልጾ መነኮሳቱ በዛሬው ሌሊት በድንጋይ ቀጥቅጠው ሊገድሉህ መክረውብሃልና ከቤትህ እንዳታድር ብሎ ምክሩን ስለ ገለፀለት በመልአኩ ምክር እየተመራም ከዚያች ጠባብ ጉጆ ወጥቶ በአፀደ ቤተ ክርስቲያን ተሰውሮ ሲጸልይና ሲሰግድ አድሮ ሌሊቱ ሲነጋ ወደ ገዳሙ ቢመለስ መነኮሳቱ እነሱ መነኮሳት እሱን አገኘነው ብለው ባዶ ጉጆ በድንጋይ ሲቀጠቅጡ ስላደሩ ጉጆዪቱ ተደርምሳ በድንጋይ ክምር ተሞልታ አገኛት ከዚህ በኋላ በመነኮሳቱ ድርጊት እጅግ በጣም አዝኖና ተበሳጭቶ ከነዚህ ጋር ከመኖርስ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ሄዶ ቅዱሳት መካናትን ተሳልሞ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶ ያደገበት ሀገረ ናዝሬትን፤ ቤተ ልሔምን፤ መካነ ቀራንዮን፤ ጎልጎታን ተሳልሞ መላ ሕይወቱን እዚያው በማገልገልና በጌታችን መቃብር አጠገብ ተቀብሮ መቅረትን ስለወሰነ ከምርጥ አርድእቶቹ መካከል ዋና ዋናዎቹን አባ ማትያስ፤ አባ በኪሞስ፤ አባ መርቆሬዎስ፤ አባ ገብረ እንድርያስ፤ አባ ገብረ ኢየሱስ፤ አባ ቀዘሞዝ፤ አባ ቴዎድሮስ፤ አባ ፊቅጦር፤ አባ ጴጥ ወንጌል፤ አባ ገብረ መስቀል፤ አባ ማትያስ፤ አባ ዮሐንስ፤ አባ ተወልደ መድኅን የተባሉትን መነኮሳት አስከትሎ ከመጨረሻይቱ ገዳሙ ደብረ ማርያም ዘቈሃይን ተነስቶ ጉዞውን ወደ ኢየሩሳሌም ቀጠለ።

አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዝ በዚያን ጊዜ ሳልሳይ ግብጽ ተብሎ የሚጠራው ሀገረ ኑብያ የዛሬው ሱዳን የኢትዮጵያ ክፍል ሀገር ስለ ነበር ከኢትዮጵያ ተሾሞ የሄደው ሰብአ ናብ የተባለው ኢትዮጵያዊ አገረ ገዢ እስከነ ደቀ መዛሙርቱ በክብር ተቀብሎ በማስተናገድ በወቅቱ እረማውያን ወላቶች ተንስተውበት ስለ ነበር ወደ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ዘንድ ቀርቦ ወላቶቹን ልወጋ ወደ ጦርነት መሄዴ ነውና አባት ሆይ ድል አድርጌ እንድመለስ ጸልይልኝ ብሎ በመማፀን በአቡነ ኤዎስጣቴዎስ እጅ ተባርኮና ተመርቆ ወላቶቹን ለመውጋት ሄደና በጸሎቱ ድል አድርጎ በመመለሱ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ሥርዓተ ቅዳሴ ሲፈጽም እጅግ የሚያጠብቡት አንድ የኒቂስ ከርስከርስት በገፀ በረከት መልክ ሰጠውና አቡነ ኤዎስጣቴዎስም ሰጦታውን ተቀብሎ ከደቀ መዛሙርቶቹ ጋር ጉዞአቸውን ወደ ኢየሩሳሌም ቀጠሉ።

አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ከዚያ በፊት ኢየሩሳሌምን ሁለት ጊዜ ደርሶ የተመለሰ ሲሆን የአሁኑ ጉዞው ለሦስተኛ ለመጨረሻ ጊዜ የሚያደርገው ጉዞ ነበርና ብዙ ወራት በምድረ በዳ ከተጓዙ በኋላ ብሔረ ግብፅ ገዳመ አስቄጥስ የተባለ ገዳም ደርሰው ለጥቂት ወራት እረፍት አድርገው ሲቀመጡ አቡነ ኤስጣቴዎስ ወደ ኢየሩሳሌም ከመጓዙ በፊት ፵ ቀንና ፵ ሌሊት በጾምና በስግደት ተወስኖ በገዳመ አስቄጥስ ሰባኤ ገባና በአርባኛው ዕለት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በራእይ ተገልጻ በአርማንያ ያሉችውን ቤተ ክርስቲያኔን የሚያገለግላት አጥታ ብቻዋን ተቀምጣለችና ወደ አርማንያ እንድትሄድ ብላ ከነገረችው በኋላ ተሰወረች።

«ወአስተርአየቶ እግዝእትነ ማርያም ወትቤሎ ዝንቱ ገዳመ አስቄጥስ ዕጻሆሙ ለመቃርስ ወለዮሐንስ ከማ ወአንተስ ፍቁርየ ወፍቁረ ወልድየ ሖር ብሔረ አርማንያ ኅበ ቤተክርስቲያንየ እንተ ተሐንፀት በስምየ»

አቡነ ኤዎስጣቴዎስ በገዳመ አስቄጥስ እያለ ይህንን የመሰለ ራእይ ካየ በኋላ ለደቀ መዛሙርቶቹ የራእዩን ምስጢር ገለጸላቸውና ከግብጽ ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ሲደርሱ በዘመኑ የኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ ከነበረው ጋር ተገናኝተው ስለ ሃይማኖት ጉዳይ ከተነጋገሩ በኋላ ሙላደ ክርስቶስ ቤተልሔምን፤ መካነ ቀራንዮን፤ መቃብረ ክርስቶስ ጐልጐታን እየዞረ ከተሳለመ በኋላ በፈለገ ዮርዳኖስ ተጠምቀው እሱና ደቀመዛሙርቶቹ ወደ አርማኒያ ለመሄድ ሲነሱ ባሕረ ኢያሪኮ ደረሱና ከኢየሩሳሌም ወደ አርማኒያ በመርከብ መንገደኞችን የሚያሻግር መርከበኛ አገኝተው ከኢትዮጵያ የመጣን ምንም ገንዘብ የሌለን መናንያን ነን ብለው በመግለጽ በነፃ እንዲያሳፍራቸው ቢጠይቁት መርከበኛው ያለ ገንዘብ አላሳፍርም ብሎ አሻፈረኝ አላቸው።

አቡነ ኤዎስጣቴዎስም በእምነቱ የፀና ንፁህ ቅዱስና ቈራጥ መንፈሳዊ አባት ስለ ነበር የለበሳትን የቆዳ አጽፍ በባሕረ ኢያሪኮ ላይ በመዘርጋት እሱና አስራ ሁለት ተማሪዎቹ በአጽፍ ላይ ተቀምጠው ሁለት መላእክት በግራና በቀኝ ባሕረ ኢያሪኮን እየቀዘፉላቸው ደሴተ አርማኒያ ላይ በታነፀችው የቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ላይ ደረሱ።

«ወነሥአ አባ ኤዎስጣቴዎስ ልብሰ አጽፎ ወዓፀፎ ፫ ዕፅፈተ ወአተቦ በትዕምርተ መስቀል ከቡር ወሰፋሐ ልብሶ ውስተ ባሕር ወወጽአ ላዕሌሁም ስለ አርዳኢሁ ወመጽኡ ፪ መላዕክት ከመ ይሕድፉ ሎቱ ሀየንተ ናትያት ፩ በፀጋሙ ወ፩ በየማኑ»

በዚህ መሠረት አባ ኤዎስጣቴዎስና ደቀ መዛሙርቱ ፲፱ ቀንና ሌሊት በአጽፉ እየተንሳፈፉ በአርማንያ ደሴት እንደ ደረሱ ከቆጵሮስ ሊቀ ጳጳሳት ጋር ተገናኝተ ስለ ሃይማኖት ጉዳይ ከተወያዩ በኋላ እመቤታችን በራእይ ከገለፀችለት ደሴተ አርማንያ ገብቶ ፲፬ ዓመት ከተቀመጠ በኋላ በ፹ ዓመቱ መስከረም ፲፰ ቀን ከዚህ ዓለም በሞት ተለየና በደሴተ አርማንያ ተቀበረ።

አቡነ ኤዎስጣቴዎስ በአርማንያ አገር ከተቀበረ በኋላ ባሕረ ኢያሪኮን ሲሻገሩ ስጥሞ ከቀረው የማነ ብርሃን በስተቀር ሌሎቹ ተከትለውት የሄዱት ደቀ መዛሙርቶቹ መስቀል፤ መጽሐፈ ሲኖዶስና ስዕለ አድኅኖ እየያዙ ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ ተመልሰው አባታቸው አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ቀደም ሲል አስተምሮ ባመነኮሳቸው ገዳም ውስጥ ተበታትነው ተቀምጠዋል።

በዚህ መሠረት አቡነ አብሳዲ የተባለው ደቀ መዝሙሩ በደብረ ማርያም ቈሐይን ገዳም መንበር ጠባቂ ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ሳይሄድ ቀርቶ ነበርና ሌሎቹ ደቀ መዛሙርቶቹ ግን ከላይ ከፍ ብለን በጠቀስናቸው አባ መርቆሬዎስ በደብረ ድማህ ዘሰራየ፤ አባ በኪሞስ በደብረ ፀራቢ፤ አባ ገብረ እየሱስ በሽማና ዘእንደርታ፤ አባ ገ/መስቀል በደብረ ሳይላ ሰሐርቲ፤ አባ ማትያስ ዘዓዲ ሐቅ በሃማሴን፤ አባ ገ/ኢየሱስ በገዳመ ድብሳን አምባ ማርያም ዘእንፍራንዝ፤ አባ ተወልደ መድኅን በገዳመ ሃምባር ጉድባ ዘሽሬ፤ አባ ጴጥ ወንጌል በገዳመ ዘአቡር መንበርታ፤ ተቀምጠው ገዳሞቻቸውን በማስፋፋትና በማስተማር በመቶ የሚቆጠሩ ታላላቅ የኢትዮጵያ ገዳማትን የመሠረቱ አበው መነኮሳትን አስተምረው አመንኩሰው ለታላቅ መንፈሳዊ ክብር አብቅተዋል።

እስከ ዛሬ ድረስም በትግራይ፤ በኤርትራ፤ በጉንደር፤ በጐጃም፤ በወሎ፤ በሸዋ እስከ ዝዋይ ሐይቅ ድረስ ተሠራጭተው የሚገኙ ገዳማት የርዕሰ ቅዱሳን አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ገዳማት በአቡነ ተክለ ሃይማኖት የበላይነት እየተረሱ የመጡ ቢሆንም በምሥራቅ ጐጃምና በጣና ሐይቅ ገዳማት አካባቢ ግን የአቡነ ኤዎስጣቴዎስን ገድል የሌለበትና ወርሃዊ በአሉንም ሆነ ዓመታዊ ክብረ በአሉን የማያከብርና የማያስታውስ ገዳምና ገዳማዊ አይገኝም በዚሁ መሠረትም የኢትዮጵያ ገዳማት ቤተ ተክለ ሃይማኖትና ቤተ ኤዎስጣቴዎስ በመባል ይታወቃሉ። ✣

www.ethiopianorthodox.org